# የሰማያት ፍሬ

# DOWN WITH HEAVEN



በኢያን ባርክለይ

ትርጉም:-አፈወርቅ አቻሜ

# የሰማያት ፍሬ

ደራሲ :- ኢያን ባርክለይ
ተርጓሚ :- አፈወርቅ አቻሜ
አርታይ:- ደረጀ በቀለ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 1998 ዓ.ም.

# የሰማያት ፍሬ

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው

Down with Heaven

Living out the Fruit of the spirit

By Ian Barclay

ከሚለው መጽሐፍ ነው።

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም
እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RPTR-23 3M

## ምስጋና

መጻሐፉን በማረምና በማስተካከል ለረዱኝ ለወንድሜ አቶ ብርሃኔ እቻሜ እና ለወንድም ተድላ ሲማ እንዲሁም መጽሐፉን በኮምፒውተር ጽሕፈት ለተባበረችኝ ለወ/ሮ ትእግስት ለገሰ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# ማውጫ

ገጽ


- የመንፈስ ፍሬ ........................ 5
- ፍቅር አሥራ አንደኛው ትዕዛዝ ................ 8
- በደስታ አገልግሉት ...................... 15
- የሰላምህ መሣሪያ አድርገኝ .................. 23
- የመልካም ሥነ ምግባር ቁንጮ ................. 30
- ቀንበሬ ልዝብ ነው ....................... 37
- ኢ-ታአማኒያዊ በጎ ተግባር .................. 44
- ስደጉም ሆነ ስክፉ ....................... 50
- ዝቅ ባለ ክብር ......................... 56
- ራስን መግዛት .......................... 61




# የመንፈስ ፍሬ

በቅርብ ጊዜ ቤተሰባችን "ብሬሞር ሃውስ" የሚባል አንድ ጥንታዊ ህንፃ ጎብኝቶ ነበር። የግቢውን በር አልፎ ስሚገባ ሰው አስቀድሞ የሚታየው ትእይንት አስገራሚ ነው። በተለያዩ እጽዋት የተሸፈነው ግንብ ለዐይን ማራኪ ነው፤ በግንቡ ትይዩ ደግሞ ዕድሜ የጠገቡ ያማሩ ዛፎች ፍሬያቸውን አንዠርግገው ተስትረዋል። በዛፎቹ ውበት የተደነቁት ልጆች ዓይነታቸውን ለማወቅ በጥያቄ ይወተውቱን ነበር። መልሱ ግን እንደ ጥያቄያቸው ቀላል ነበር። ወቅቱ ቀዝቃዛው የነሐሴ ወር ስለነበር አረንጓዴዎቹ የበሰሉ ፍሬዎች በዛፎቹ ላይ ተንዠርግገዋል። እና ፍሬዎቹን በመመልከት የዛፎቹን ዓይነት ነገርናቸው።

እንደገናም ደግሞ የአውደዓመት ክብረበአላችንን ባከበርንበት "አዲሱ ደን" በተባለው ስፍራም ከዚህ ቀደም ያላወቅናቸውን ዛፎች በፍሬያቸው ልንለይ ችለን ነበር። በክረበዓል ጎጂችን ውስጥ ሆነን እንኳን በርካታ ዛፎችን ከፍሬያቸው ዓይነት ለይተን አወቅናቸው። በለስ በበለስ ዛፍ ላይ ፖምም በፖም ዛፍ ላይ መብቀሉ ይህ የተፈጥሮ ህግ ነው። ተፈጥሮም ለማንም አዳልታ ይህን የእውነታ መመሪያዋን አትቀይርም።

ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን፣ ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ ያደርጋል፣ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል" (ማቴ 7፥16-17)።

የክርስትና ሕይወት ተለይቶ ከሚታወቅባቸው መንገዶች አንዱ የመንፈስ ፍሬ ነው። ሰዎች ስለሰዎች የሚሰጡት ምስክርነት፣ አባል የሆኑበት ቤተአምነት፣ በቤተክርስቲያን ያላቸው የአገልግሎት ስፍራ

ስለስዎቹ መንፈሳዊ ሕይወት የሚናገረው እንዳች ነገር የለውም። እውነተኛና የተጨበጠ ማስረጃ ማግኘት ለሚፈልግ በመንፈስ የተዘራውንና እያደገ ያለውን ፍሬ አተኩሮ ሊመለከት ግድነው። የብርቱካን ፍሬ የብርቱካንን ዛፍ እንደሚያሳየን እንዲሁ ደግሞ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃትና ራስን መግዛት (ገላ 5+22) በቀላሉ የክርስትናን ሕይወት አጥርተው ያሳያሉ።

የመንፈስን ፍሬ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ለመተግበር ፈጽሞ የማይቻል ነገር ቢመስልም ከአዲስ ኪዳን አማኝ በእጅጉ የሚጠበቅ ነው። የዚህ ፍሬ በሕይወታችን መገለጥ የጠንካራ እምነታችን፣ የባርኮታችን፣ ከጌታ ጋር ያለን ቅርበት፣ የበሰለ መንፈሳዊ ሕይወት ወይም በእምነታችን ላይ ያለን አክራሪ አመለካከት ውጤት አይደለም። ይልቁንም በሕይወት ቅርብ የሆነ የዕለት ዕለት የክርስትና ሕይወት ምልልስ ውጤት ነው።

በእርግጠኝነት ለመናገር፣ ዛሬ ዓለም በእኛ ልታይ የምትፈልገው ይህን እጅግ ቅርብ የሆነ የክርስትና ሕይወት ነው። ዓለም በቤተክርስቲያን ላይ ነቀፌታዋንና ውግዘቷን የምታሰማው ይህን በተግባር ሊታይ የተገባ ሕይወት ከሕይወታችን ፈልጋ በማጣቷ ነው። ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት የውሃትና ራስን መግዛት የክርስትና ሕይወት የመታወቂያ አርማዎች ተጠራጣሪዋም ዓለም በጎርጥ እያስተዋለች ከሕይወታችን ልታየው የምትሻው ነው።

ከዚህ በማስከተል ያቀረብኩት በአማኙ ሕይወት ውስጥ ሊታይ የሚገባው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሲሆን አሳቡም መሠረታዊና በቀላል መንገድ የተብራራ ነው። ጣፍጦ እንደሚነበብም ተስፋ አደርጋለሁ።



ዓለም ዛሬ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ፍሬን ማየት ትፈልጋለች፣ እግዚአብሔርም ይህን ለማየት ይናፍቃል። ይህ የሥንግስተ ሰማይን ሕይወት በምድር መኖር መስሎ ከታየን፣ መንገዱን "የመንግሥተ ሰማይን ሕይወት በምድር!" ብለን እንሰይመውና ሕይወቱን አሁን መኖር እንጀምር።

ኢያን ባርክለይ

# ፍቅር . . . የመንፈስ ፍሬ ነው

ገላትያ 5፥22

## ፍቅር ስለቱ ለንደኛው ትእዛዝ

ሳሙኤል ሩተርፎርድ በ17ኛው ክፍለ ዘመን የኖረ እንግሊዝ በሚገኘው የፓሪሽ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር። ሊቀጳጳስ አሸር የተባሉት ካህን ደግሞ ሳሙኤል በሚያገለግልበት መንደር ሲያልፉ፤ ከጉዞአቸው ተናጥበው በአገልጋዩ ቤት ለማረፍና የአገልግሎቱም በረከት ተካፋይ ለመሆን ፈለጉ። በአገልጋዩም ቤት መስተንግዶ ተደረገላቸው። ይሁን እንጂ ካህኑ ማንነታቸው እንዳይታወቅ ልብስ ተክኗቸውን ቀይረው እንደ ተራ እንግዳ ነበር የገቡት። እራት ከተበላ በኋላ ቤተሰቡ የዕለቱን ቃል ለመስማት በተሰበሰበ ጊዜ ሩተርፎርድ ጳጳሱን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው። "እንጠብቃቸው ዘንድ የሚገቡ ስንት ትእዛዛት ተሰጥተውናል?" ጳጳሱም ፈርጠም ብለው "አሥራ አንድ" ሲሉ መለሱ። ሳሙኤል ሊያርማቸውና አሥር እንደሆኑ ሊያስረዳቸው ቢሞክርም እንግዳው ግን አሥራ አንድ እንደሆኑ ሸንጣቸውን ገትረው ተሟገቱ። ከዚህም አልፈው ኢየሱስ ክርስቶስ (በዮሐ 13፥34) የተናገረውን ዋቢ ጠቅሰው ሞገቱት።

በማግስቱ እሁድ፤ ሳሙኤል ሩተርፎርድ እንደልማዱ ጥዋት ተነስቶ በጫካው ውስጥ ይንጎራደድ ጀመር። መንገደኛውም ጫካው ውስጥ ጸጥ ባለና በተመነጠረ ቦታ ላይ ሆኖ በመላው እንግሊዝ ላይ ትልቅ የበረከት ዝናብ ይወርድ ዘንድ በጸሎት እግዚአብሔርን ሲለምን አገኘው። ሳሙኤል ሩተርፎርድም ሳያውቅ መንፈሳዊውን መሪ በቤቱ እንዳስተናገደ አወቀ። በመጨረሻም ሊቀ ጳጳሱ በዚያው ቀን በሚደረገው በማለዳው አገልግሎት እንዲሰብኩ ተስማሙ። የአስራ አንደኛውን ትእዛዝ መልእክትም "አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ!" በሚል ርዕስ አቀረቡት።

አዲሱ ትእዛዝ በአዲስ ኪዳን በቅድስና ሕይወት እንድንመላለስ ያስተምረናል። ስለዚህ ፍቅር የመጀመሪያው የመንፈስ ፍሬ መሆኑ አያስገርምም። መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ ወደ ሕይወታችን የሚያመጣው ችሎታ (አቅም) ከዚህ በፊት በህይወታችን ባላየነውና ባልተለማመድነው አስደናቂ ሁኔታ ሌሎችን የመውደድ ብቃትን ነው።



### አዲስ ፍቅር

የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች በዘመናቸው በነበረች ዓለም ውስጥ ስለፍቅር ተተርከላቸዋል፣ ስለፍቅር ብዙ ሰምተዋል፣ አውቀዋልም። ይሁን እንጂ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ለእነርሱ ከገለጸላቸው የፍቅር ምንነት ሚስጥርና እውቀት አንጻር፤ ቀድሞ ያወቁትና የሰሙት ሁሉ ባዶ ተረት ነበረ። ልክ ሲ.ኤስ.ሊዊስ እንደተናገረው ዓለም እውነተኛ የፍቅር ልብ በሌላቸው ደረት የለሾች (የልብ ቋት አልባዎች) የተሞላች የሽንጋዮች መኖሪያ ነች።

ስለዚህም ነበር የቀደሙት ክርስቲያኖች ስለ ፍቅር ሲጽፉ አስቀድሞ ዓለም ስለምንነቱ ከሰጣቸው ትርጉም የተለየ ሌላ አዲስ ቃል መፈለግ ያስፈልጋቸው። የግሪክ ቃላት ባጠቃላይ ይህንን ፍቅር ለመግለጽ በቂ አልነበሩም። አንዱ ቃል ፍቃደ ሥጋዊ ትርጉም የያዘ ሲሆን ሌላው ተፈጥሮአዊ ስሜትን የሚገልጽ ሶስተኛው ደግሞ የወንድማማችነትን ፍቅር የሚያሳይ ነው። ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሙበት ግስ ነበር እንጂ ስም አይደለም። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ግሱን ወሰዱና ይህን አዲስ ፍቅር የሚገልጽና ሰዎችን ከፍቃደ ሥጋዊ ፍቅርና ከተፈጥሮአዊ ስሜት ጋር የማያደናግር ሌላ አዲስ ስምን ፈጠሩ።

### ፍቅር ለዚህ ዓለም እንግዳ ነው

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ያሰቡት የፍቅር ዓይነት ለዚህ ዓለም እንግዳ ነበር። ዮሐንስም በመጀመሪያው መልእክቱ እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፤ "አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ" ወይም "አብ ምን ዓይነት ፍቅር እንደሰጠን" (1ዮሐ 3፥1)። ምን ዓይነት የሚለውን ቃል በአዲሶቹ ትርጉሞች ብዙ ጊዜ እናየውም። ነገር ግን በዋነኛው የግሪክ ቃል ትርጉሙ ፍጥረታዊ ያልሆነ፣ አለም ከዚያ በፊት ያላየችውና ያላወቀችው፣ ያልተለማመደችውም አዲስና እንግዳ መሆኑን ይገልጽልናል። በክርስቲያኑ ሕይወት ውስጥ ፍቅር ከተፈጥሮ ማንነቱ የተገኘ (የፈለቀ) ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ የተዘራ፣ የበቀለና ያበበ ለዚህ ዓለም ፍጹም እንግዳ (አዲስ) የሆነ ነው።

ይኸው ፍቅር መለኮታዊ እና "በመንፈስ ቅዱስ በልባችን የፈሰሰ" ነው (ሮሜ 5፥5)።

### ገና ጠላቶች ሣለን ተወደናል!

የሰው ተፈጥሮአዊ ፍቅር በራሱ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። አንድ የሚማርከውን ነገር ሲያገኝ ይወደውና ይፈልገዋል። መለኮታዊ ፍቅር ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነው። የማይወደደውንና የማይማርከውን

የመውደድ ችሎታ አለው። ይኸኛው የመውደድ ችሎታ እግዚአብሔር እኛን የወደደበት ፍቅር ነው፣ ምክንያቱም፤ እግዚአብሔር እኛን የወደደን ገና ጠላቶቹ ሣለን፤ በአካላዊ፣ በሞራላዊና በመንፈሳዊ ጉዳዮቻችን ሁሉ ዘቅጠን፤ የሚማርክና የሚወደድ ምንም ነገር ሳይገኝብን እንዲሁ ነው። መንፈስ ቅዱስ ይህንን ፍቅር በእኛ ላይ መግለጥ በሚጀምርበት ጊዜ፣ እኛም ደግሞ ጠላቶቻችንን መውደድ እንጀምራለን።

## ፍቅር ቸርነትን ያደርጋል

የመለኮት ፍቅር አንዱ ባሕርይ መስጠት እንጂ መቀበል አይደለም። ይህንም እግዚአብሔር ለኛ ባለው ፍቅር እንደገና እናያለን። ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ይነግረናል ". . . እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐ 3፥16)። መንፈስ ቅዱስ በህይወታችን መለኮታዊ ፍቅሩን እንዳፈሰሰ ምልክት ከሚሆኑ ነገሮች አንዱ ከመቀበል ይልቅ በመስጠት ከመጠየቅ ይልቅ ለሌሎች በማድረግ ደስ መሰኘት መጀመራችን ነው።

በአራተኛው ክፍለ ዘመን ሲኖፕ ከምትባል ከተማ ወጣ ብሎ ፎካስ የሚባል ክርስቲያን ይኖር ነበር። መንገደኞችም አዘውትረው በበሩ ያልፉ ነበር። እርሱም ወደ አትክልቱ ቦታ መጥተው እንዲያርፉና ወደ ከተማ ተበረታትተው ይገቡ ዘንድ ይጋብዛቸው ነበር። ባገኘው አጋጣሚም እምነቱን ለመንገደኞቹ ያካፍል ነበር።

በንጉሠ ነገሥት ዲዮክሌሺያን አገዛዝ ጊዜ ክርስቲያኖች ሁሉ እንዲገደሉ ትእዛዝ ተላለፈ። "የሲኖፑ ፎካስ" የሚለው ስምም በዳኞቹ የስም ዝርዝር ውስጥ የመጀመሪያው ነበር። ሕግ አስከባሪዎቹ በረጅም ጉዞና በፀሐይ ሐሩር ደክመው ሲኖፕ ከተማ ሲደርሱ ፎካስ እንደልማዱ እንግዶቹን ወደ አትክልት ስፍራው ጎራ ብለው ያርፉ ዘንድ ጋበዛቸው። በምን ጉዳይ ወደ ሲኖፕ እንደመጡም ጠየቃቸው። የሕግ አስከባሪዎቹ ዋና አዛዥ ፍካስ የሚባለውን ክርስቲያን እንዲገድሉ ከሮም ትእዛዝ እንደተሰጣቸው ገልጾ የሚገኝበትን እንዲነግረው ጠየቀው።

"በደንብ አውቀዋለሁ" አለ ፎካስ። "ከዚህ ሩቅ አይደለም፣ አንተና ሰዎችህም እዚሁ እደሩና ጥዋት ወደ ቦታው አደርሳችኋለሁ" አላቸው።

ከሮም የመጡት ሰዎች እንደተኙም ፎካስ በጣም ወደሚወደው የአትክልት ቦታው ሄደ። ልክ ጥዋት ሊነጋጋ ሲል የሚቀበርበትን ትልቅ ጉድጓድ ቆፈረ። ጎህ ሲቀድም ሮማውያኑን ወታደሮች ቀስቅሶ እርሱ ፍካስ መሆኑን ነገራቸው። ሰዎቹ በጣም ተገርመው እንደዚህ ዓይነቱን



ደግነት የፈጸመላቸውን ሰው ሊገድሉ እንደማይችሉ ተናገሩ። "ኦ፣ እባካችሁ አድርጉት አለ ፎካስ። እኔ ክርስቲያን ነኝ፣ ሞት ለኔ ምንም አይደለም፣ ነገር ግን እናንተ የታዘዛችሁትን ካልፈጸማችሁ ችግር ውስጥ ትገባላችሁ። ስለዚህ ለራሳችሁ አስቡ። ግዴታችሁንም ፈጽሙ! ለእናንተ ያለኝ ፍቅርና ስሜት አይቀየርም" አላቸው።

ግድያው ተፈጸመ፣ ሬሳውንም በሥርዓት አድርገው አትክልት ቦታው ውስጥ ለራሱ ወደቆፈረው መቃብር አወረዱት። ለመንገደኞች የሚሰጥ ከዚህ በላይ የሆነ ፍቅር የለም፣ ምክንያቱም ያለው ሁሉ ተሰጥቷልና።

## ፍቅር በኑሮ የሚገለጽ ነው

አንዳንዴ ክርስቲያኖች የመልእክታቸውን እውነታ በሚኖሩት ኑሮ ይክዱታል፣ ይህ የማይታበል ሐቅ ነው። የኤተን ርዕሰ መምህር ገጣሚው ሼሊ ወጣት ወንድ ተማሪዎችን እንዲህ ይላቸው ነበር፣ "በጎ አድራጊዎች ሁኑ፣ ካልሆናችሁ ግን እስከተሆኑ ድረስ ትገረፋላችሁ።"

በታሪክ የኢንኪዊሰሺን ወቅት ተብሎ በሚታወቀው፣ ካቶሊኮች ሃይማኖታቸውን የሚቃወም ሁሉ ለማጥፋት በተነሳሱ ጊዜ ስፓኞች መካከለኛው አሜሪካ ውስጥ አንድ የኢንካዎች መሪ ማርከው ያዙ። የኢንካዎቹ መሪ ወገኖቹ ክርስትናን ተገደው እንዲቀበሉ እጅና እግራቸውን ጠፍሮ ይዞ ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች በሚስብና የእጅ ጣቶችን እየጨፈለቀ በሚያሰቃይ መሳሪያ እንደሚሰቃዩ ያውቃል። የማረኩት ሰዎችም ክርስቲያን እንዲሆን በመጠየቅ መንግስተ ሰማይ እንደሚገባም ተስፋ ይሰጡታል፣ ካልሆነ ግን ወዲያውኑ እንደሚገድሉት ገሃነምም እንደሚጠብቀው ያስፈራሩታል። እርሱ "ክርስቲያን አልሆንም። እናንተን ከመሰሉ ሰዎች ጋር መንግስተ ሰማይ ከምሄድ፣ ከሕዝቤ ጋር ወደ ገሃነም ብሄድ እመርጣለሁ ብሎ" መለሰላቸው።

የምንናገረው ነገር ከምንኖረው ኑሮ ጋር ስለማይጣጣም ብዙዎች ክርስቲያን ያልሆኑት ጓደኞቻችን ለወንጌል ምስክርነታችን የሚሰጡን መልስ የኢንካዎቹ መሪ እንደመለሰው ዓይነት ነው።

እውነተኛ ፍቅር ማንም ይሁን ማን ጎረቤትህን እንድትወድ ያደርጋል። ምንም ያህል የክርስትናን እምነት የሚቃወም ሰው ቢሆን እንኳ ሕይወቱንና ንብረቱን እንዳታጠፉ ያደርጋል። ይህን ለማድረግ ፍቅርን ከልብ ውስጥ መንጭቆ ጥሎ ወደጠለቀ የጥላቻ አዘቅት መስመጥ ማለት ነው።

## ፍቅር ከእምነት በላይ ጉልበታም ነው!

የመለኮታዊው ፍቅር ትልቁ ተፈላጊነት በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው። በቤተክርስቲያን የፍቅር መቀዝቀዝ መንፈሳዊ ሐይሏን ያባክነዋል። በዓለም ዙሪያ የሚጠቀሙበትን ትልቁን ግሬደር የሰራው አር.ጂ.ሊቶርኒዮ የመካኒክ ዋና ጠላት መፋተግ መሆኑንና ይህም የመሣሪያውን ግማሽ ኃይል በቀላሉ ያጠፋዋል (ያዳክመዋል) ብሏል። እንደ ክርስቲያንነቱ ደግሞ "መፋተግ (ግጭት) በመሣሪያ ላይ ይህን ካደረገ፣ ስለዚህ በሰዎች ላይ ትልቅ ጉዳት ያደርሳል" ይል ነበር።

የመፋተግን እሉታዊ ምሳሌ ለማየት ክረምት ላይ ወደ አልሞቀ ክፍል ስንገባ የመስኮቶቹ የውስጠኛው ክፍል በጣም ብርዳማ ሆነው እናገኛቸዋለን። በረዶውን ለማጥፋት በኃይል ስንፈገፍገው በረዶዎቹ ቶሎ ቶሎ እንደገና ይፈጠራሉ። እዛው ክፍል እሳት ለኩሱና እዩት በረዶው ቶሎ ይቀልጥና ይጠፋል።

ስለዚህ መፋተግ የቤተክርስቲያንን ኃይል ማባከን (መቀነስ) ብቻ ሳይሆን የቅዝቃዜ መንፈስን አጠንክሮ የቤተክርስቲያንን ሕይወት ያጠፋል። ትንሽ ሞቅ ካለ ልብ የሚወጣ መለኮታዊ ፍቅር ግን በቤተክርስቲያን የሚገኘውን የመንፈሳዊ ቅዝቃዜን በረዶ ሊያቀልጥ ይችላል። ኦገስቲን የተባሉ ሰው እንዳሉት "የአንዱ የፍቅር መንፈስ ሌላውን በእሳት ያቀጣጥላል። "

## ፍቅር የሕይወት ዘመን ጉዞ ነው

መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወታችን የሚያመጣው ፍቅር ለተፈጥሮአዊው የሰው ልብ እንግዳ መሆኑን አይተናል። ይህንን ፍቅር እኛ ልንፈጥረው የምንችለው አይደለም። ነገር ግን ጥሩ ሆኖ እንዲበቅል ሁኔታዎችን ልናመቻችለት እንችላለን።

በአንድ ወቅት ዲ.ኤል.ሙዲ "አንዳንድ ሰዎች አልፎ አልፎ ወደ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ይጓዛሉ" ብሏል። አባባሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ እዛው ክፍል ይኖራሉ ማለቱ ነበር። ስለዚህ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሰላሰን ግንኙነት ወደሚያሳየን ወደ 1ኛቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 እንጓዝ። በዚህ ክፍል መንፈስ ቅዱስ ስለፍቅር ምንነት አንጥሮ የሚያስተምረንን ጥቂት ነገሮች መረዳት ብንችል እንኳን! ፍቅር በህይወታችን ይለመልም ዘንድ አመች ሁኔታዎችን መፍጠር እንችላለን።

1. ፍቅር አይበሳጭም (ቁጥር 5)

   "**ፍቅር አይበሳጭም**" የሚለው ቃል ሳነብ የቀደሙት የእምነት አባቶች እንደኛው በነገሮች ሊፈተኑ ሊሰናከሉም የሚችሉ ሰዎች



   መሆናቸውን ስለሚያሳየኝ እደነቅበታለሁ። ኪንግ ጀምስ የተባለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ለተረጎሙት ወገኖች ነገሩ ጠጠር ያለባቸው ይመስላል። ለዚህም ነው ይህን ቃል ሲተረጉሙ "ፍቅር በቀላሉ አይበሳጭም" ያሉት። ነገር ግን "በቀላሉ" የሚለውን ቃል በቅድመ ቃሉ አውድ ውስጥ ፈልገን አናገኘውም። ብስጭትን በማስወገድ ፍቅር በህይወታችን እንዲገለጥ ሁኔታዎችን ልናመቻች እንችላለን። አንዱ እንዲህ አለ "ከተበሳጨሁ የሆነ ቦታ ላይ እንደተሳሳትኩ ወዲያው አውቃለሁ ምክንያቱም መበሳጨት አልነበረብኝም! "

2. ፍቅር በደልን አይቆጥርም (ቁጥር 5)

   "**በደልን አይቆጥርም**" ማለት ሰዎች ደግመው በሚሳሳቱበት ጊዜ ስህተታቸውን አይመዘግብም ማለት ነው። የአንድን ወጣት አሜሪካዊ ተማሪ ታሪክ እንመልከት። ይህ ተማሪ በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክኮ ስለ አንድ ኃጢአቱ ከተናዘዘ በኋላ በድጋሚ እንደማያደርገው ቃል ይገባል። ነገር ግን አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንደገና በጉልበቱ ተንበርክኮ፣ "እግዚአብሔር ሆይ ደግሜ አደረግኩት" አለ። በጣም ጥልቅ የሆነ ለማያዊ ጽምፅ "ያደረከው ምን ነበር" ሲል አስተጋባ። የእግዚአብሔር የይቅርታ ፍቅር ሙሉ ስለሆነ ተማሪው ቀድሞ የሰራውን ስህተት ፈጽሞ ረስቶት ነበር። ፍቅር እንዲያድግ ብቸኛ መሠረቱ የሌሎችን ውድቀትና ስህተት እንደ እግዚአብሔር መርሳት ብቻ ነው።

3. ፍቅር ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም (ቁጥር 6)

   ሊቀ ጳጳስ ክራንመር ሁልጊዜ የሚሉት አንድ አባባል ነበር፣ "ለጎዳህ ሰው ፈጥነህ ይቅርታ ካላደረክለት፣ ያንን ሰው እንደመልካም ጓደኛህ ሁሉ በአእምሮህ ውስጥ ለብዙ ዘመን ተሸክመኸው ትኖራለህ"። ሊቀ ጳጳሱ ከመገደላቸው ትንሽ ቀደም ብሎ፣ "ለጎዱኝና ክፉ ላሰቡብኝ ሰዎች ይቅር ብሎ ከመርሳትና ርኅራኄ ከማሳየት የበለጠ ደስታ በሕይወቴ ዘመን አላየሁም" ብለው ነበር።

4. ፍቅር ሁሉን ይታገሳል (ቁጥር 7)

   "**ይታገሣል**" የሚለው ቃል ትርጉሙ የዝምታ መጎናጸፊያን ማልበስ ወይም መሸፈን ማለት ነው። የታላቁን አሌክሳንደር ምስል የሳለው ሰዓሊ በአሌክሳንደር ግንባር ላይ ያለው ጠባሳ

እንዳይታይ የአሌክሳንደር የእጅ ጥሳ በግንባሩ ሳይ እንዲያርፍ አድርጓል። ፍቅር የሌሎችን ስሕተት ማጋሰጥ እይሆንሰትም።

የማይቆጣ፣ የማይናደድ፣ በክፉ ደስ የማይለውን ሕይወት ሰመምራት እርምጃን መጀመር እስራ እንደኛውን ትዕዛዝ ሰመፈጸም የቆረጠ ሕይወት ምልክት ነው።



# ደስታ . . . የመንፈስ ፍሬ ነው

ገላትያ ፭፥፳፪

## በደስታ አገልግሉት

“በምድር ላይ የምትኖሩ አሕዛብ ሁሉ” የሚለውን መዝሙር ሦስተኛ ስንኝ ባየሁ ጊዜ የተደነቅኩትን መደነቅ አልረሳውም። ዛሬ ድረስ በመዝሙር መጽሐፌ ውስጥ በደስታ አገልግሉት የሚሉት ቃሳት በጉልህ ተጽፈው ይገኛሉ። አግራሞቴ ታሳቅ ስሰነበር ቀሪዎቹን የመዝሙሩን ስንኞች ሰመዘመር እንኳን አልቻልኩም። ያኔ ገና አዲስ ክርስቲያን ነበርኩና በህይወቴ ብዙ ሊቀየሩ የሚገባቸው ነገሮች እንደነበሩ አውቅ ነበር። የደስታ መግለጫ የሆኑት እንደ ሣቅና ሃሴትን ማድረግ የመሳሰሉት የውስጤ ስፍራ መያዝ ነበረባቸው። ሲ.ኤስ.ሊዊስ “የመንግሥተ ሰማይ ዋናው ስራ ደስታ ነው” ብሰው የተናገሩትን እስተውየ ሰመረዳት ግን ገና በክርስትና ህፃን ነበርኩ።

### የመንግሥተ ሰማይ ዋና ሥራ

ደስታ በክርስትና ትምህርት እውነታ ላይ በተመሰረተ ልብ ውስጥ መኖር ያለበት ከመሆኑም በላይ፤ በየእለቱ የሕይወት እንቅስቃሴያችን ውስጥ መገለጥ ያለበትም ጉዳይ ነው። በሕይወታችን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የምንገኝና የምናልፍ ቢሆንም እንኳን፤ ደስታ የማያበራው የሕይወት ጨለማና የማያነቃቃው ድንዛዜ መኖር የለበትም። የመንፈስ ፍሬ የሆነው “ደስታ” የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳናችን ውስጥ 60 ጊዜ ተጽፎ እናገኘዋለን፤ እንዲሁም “መደሰት” የሚለው ከእርሱ ጋር የሚያያዘው ቃል ደግሞ 72 ጊዜ ተጽፏል። ይኸውም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ሶስት ደስታን ከሚገልጹ ቃሳት አንዱ ሲሆን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ስድስቱ የደስታ ቃሳት ግን የተለየ ነው። እነዚህ ሁሉ በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ስለሆነ ጥናታችን በዚሁ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ላይ መሠረት ቢያደርግ ስህተት አይሆንም። ስለዚህም የነህምያ መጽሐፍ ሰዚህ ቃል ጥናት ይሆነን ዘንድ በጣም ጠቃሚ የሆነ አስተዋጽኦ ያደርግልናል። እንዲህም ይላል፣ እግዚአብሔር በታላቅ ደስታ ደስ አሰኝቶአቸዋልና በዚህ ቀን ትልቅ መስዋዕት አቀረቡ፣ ደስታ አሳቸው፤ ሴቶቹና ልጆቹም ደግሞ ደስ አሳቸው፤ የኢየሩሳሌምም ደስታ ከሩቅ ተሰማ (ነህምያ 12፥43)።

በዚህ ጥቅስ ላይ "ደስታ" ስለሚለው ቃል መሠረታዊ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባህሪውን፤ ይሄውም "ታላቅ ደስታ" የሚለውን ሃሳብ ተመልክተናል። በክፍሉ እንደተገለጸው ሁሉ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችም ውስጥ "ደስታ" የሚለው ቃል ያቀፈው ሃሣብ ጠንከር ያለ ነው። ወሰንየለሽ ሃሴትን፣ ፍስሃንና የሚፍለቀለቅ ስሜትን የሚገልጽ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህን ቃላት የማይገኙለትን ደስታ "የማይነገር ሐሴት" ብሎታል (1ጴጥ 1፥8)። ሲ.ቲ.ስታድ የተባለ ቀደምት ሚሲዮናዊ ደግሞ የደስታ ቅዠት ሲል ይገልጸዋል።

ይኸው ደስታ ዛሬ ከክርስትና ኑሮአችን መጥፋቱ እውነት ነው። ስዎች ወደ ቤተክርስቲያን በሚያዩበት ጊዜ በደስታ የተሞሉ አማኞችን አይመለከቱም። ይልቁንም ብዙውን ጊዜ የሚያዩት ጎርደን ኧርነስት እንዳለው "ከህይወት ዋንጫ የመከራን ገፈት እያንጠፈጠፉ የሚጨልጡትን" ስዎች ነው። ኧርነስት ጎርደን ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት "ታምራቶች በኳይ ወንዝ" በተባለው መጽሐፍ "በጨለማውና ደስታ በሌለው የአማኞች መንደር ከመኖር ይልቅ አስጨናቂውን ገሃነም እመርጣለሁ" ማለቱ አያስገርምም። ዳሩ ግን የአማኝ ሕይወት ጨለማም፤ ደስታ የሌለውም አይደለም። ደስታ ወደ እማኝ ሕይወት በብዙ መንገድ ይመጣልና።

## ወንጌል፡- ጥሩ ስሜት፣ ደስተኛነትና ፍልቅልቅነት

በመጀመሪያ ደረጃ በእምነት ደስታ እንደሚገኝ ግልጽ ነው። ብዙውን ጊዜ በወንጌል እንደምናየው ስዎች ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያገኙት ይደስታሉ። ቀራጩ ዘኬዎስ ኢየሱስን ከማግኘቱ በፊት ደስተኛ ነበር ማለት አንችልም። ነገር ግን ከግንኙነታቸው በኋላ ደስ እያለው በቤቱ በእንግድነት ተቀበለው (ሉቃስ 19፥6)። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ብሉይ ኪዳንን በሚያነብበት ወቅት ፊሊጶስ መጥቶ እስኪያስረዳው ድረስ የሚያነበው አልገባውም ነበር። የፊሊጶስ እስተምህሮ ኢትዮጵያዊውን እንዲጠመቅና መንገዱን ደስ ብሎት እንዲሄድ ረዳው (ሐዋርያት ሥራ 8፥39)።

ኢየሱስን ማግኘት በራሱ ትልቅ የደስታ ምክንያት ነው። በ16ኛው ክፍለ ዘመን ይኖር የነበረው ዊልያም ታይንዴል የክርስትናን ወንጌል እንዲህ ገልጾታል፣ "ጥሩ ሐሜት እንዲሰማን የሚያደርግ፣ ደስ የሚያሰኝና ደስተኛ የሚያደርግ የምስራች ዜናን የሚያመጣ፣ የሰውን ልብ የሚያሞቅ፣ የሚያዘምርና፣ በደስታ የሚያስፈነጥዝ ነው።"

ሰዎች ወደ ክርስትና አምነት በሚሰወጡበት ጊዜ ምን እንደተሰማቸው ሲጠየቁ "ደስታ" በሚለው ግሩም ቃል ያጠቃልሉታል።



ሲ.ኤስ.ሲዊስ የራሱን ህይወት ታሪክ የፃፈበትን መጽሐፍ ርዕስ የሰየመው "በደስታ መደነቅ" ሲል ነው። ፀሐፊው በዚህ መጽሐፉ ውስጥ፤ ከክህደት ህይወት እንዴት እንደወጣ፣ ጌታ ኢየሱስንና ደስተኛ ነትን በአንድነት እንዴት እንዳገኘ ያብራራል።

ሕዳር 23 ቀን 1654 ምሽት ላይም ብለይስ ፓስካል ተመሳሳይ ግኝት ነበር ያገኘው። ከሁለት ሰዓታት በኋላ ያገኘውን ልምድ ሲገልጽም "ደስታ፣ ደስታ፣ የደስታ እንባ" የሚሉት ቃላት ያካተተ ነበር። ፓስካል በዚያን ሌሊት የጻፋቸው ቃላት በትንሽ ወረቀት ላይ ጽፎ በአንደኛው የኮቱ የውስጠኛ ክፍል ለቀረው የሕይወት ዘመኑ አስቀምጦት ነበር። ከመስወጡ በፊት ቀስስተኛና የዓለም ደስታና ፈንጠዝያ ሁሉ የሚያስጠላው ሰው ነበረ። ጌታን ካገኘ በኋላ ግን ጠቅላላው ሕይወቱ ተቀይሮ ደስተኛና ልዩ ሰው ከመሆኑ የተነሳ ይህ አስደናቂ የሆነ የሕይወት ለውጥ እህቱን ድንጋጤ ውስጥ ከትቷታል።

## ክርስትና - አስገራሚና ታላቅ የሆነ የደስታ ኑሮ ነው

ሁለተኛ፤ በክርስቲያን ሕይወት (ኑሮ) ውስጥ ደስታ አለ። የክርስቲያን ሕይወት ምን እንደሆነ ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ ላይ ሲገልፀው በእያንዳንዱ መግለጫው መነሻ ላይ "ብፁዓን" (የተባረከ) የሚሉት ቃላት ይጠቀም ነበር። ኢየሱስ ይህን ቃል የተጠቀመው በሚመጣው የወደፊት የሕይወት ተስፋ ስለሚያገኙት በረከት ሳይሆን፤ ደቀመዛሙርቱ በዚያን ስዓት ስለተቀበሉት የበረከት ልምምድ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ብፁዕ (የተባረከ) የሚለውን ቃል ሲጠቀም ምን ማለቱ እንደሆነ በዘመናችን ወዳለ የቋንቋ ስርዓት አምጥተን ግልጽ የሆነ ትርጉም ልንሰጠው አንችልም። ይሁን እንጂ ቃሉ የመንግሥተ ሰማይን ደስታ በምድር ላይ ከማወቅና ከመኖር ያነሰ ትርጉም እንደማይኖረው መገመት እንችላለን።

ስለዚህ ገጣሚው ሮበርት ብሮውኒንግ ብቻ አይደለም ስለ "አስገራሚና ታላቅ የሆነ የደስታ ኑሮ" የተናገረው። ኢየሱስም ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ይኸው ነበር። የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች በተለያዩ መከራዎች ውስጥ ቢያልፉም፣ አስገራሚውን ደስታ ያጣጣሙ ይመስላል። ሌሎች በችግርና በፈተና በሚያልፉበት ጊዜ ደስተኞች እንዲሆኑ ያበረታቷቸው ነበር። ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት (ያዕ 1፥2)። አነርሱ ራሳቸውም እንደዚህ ዓይነቱ ችግር ሲደርስባቸው ይደሰቱ ነበር፣ ምክንያቱም "ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ" (ሐዋ. ሥራ 5፥41)።

በአዲስ ኪዳን ዘመን የነበረው የተለመደ የጊዜው ሰላምታ፤ ለምሳሌ ሁለት ጓደኞች በሚገናኙበት ወይም ደብዳቤ በሚጻጻፉበት

ጊዜ የሚጠቀሙበት ቃል የመጣው ልክ ጳውሎስ በገላትያ "ደስታ" ብሎ የተጠቀመበት ዓይነት ቃል ነው:: ምንም እንኳን በዘልማድ "ሰላምታ" ተብሎ ቢተረጎምም በማያወላውል ሁኔታና በእርግጠኝነት እንዲህ ተብሎ ይነበባል፣ "ደስታ ከእናንተ ጋር ይሁን":: ያዕቆብ በመላው ዓለም ለተበተኑ ክርስቲያኖች በጻፈላቸውና ከአዲስ ኪዳን መልእክቶች ቀደምትነት ባለው በዚህ ጽሑፉ፤ የተስመደውን የሰላምታ ዘይቤ በማቅረብ ይጀምራል፤ "ደስታ ለእናንተ ይሁን!" ቀጣዮቹ የአዲስ ኪዳን መልእክቶችም ሁሉ ይህንኑ የያዕቆብን ሰላምታ በዘመናት መካከል ማስተጋባታቸው እውነት ነው::

## የደስታ አክሲል

ሦስተኛው፤ ሌሎችን ወደ ጌታ በማምጣት ደስታ ይገኛል:: ጳውሎስ ወደ ጌታ ያመጣቸውን ሰዎች የእርሱ ደስታና አክሊል መሆናቸውን ተናግሯል:: ምንም እንኳን አብዛኞቻችን እምነታችንን ለሌሎች ከማካፈል ብናፈገፍግም፣ ምናልባትም የምንመሰክርለት ሰው ዝንባሌ ቢኖረውና ወደ ጌታም ቢመጣ፤ ሰዎችን ወደ ጌታ በማምጣታችን በውስጣችን ሊታመን የማይችል ታላቅ የደስታ ስሜት ይቀጣጠላል:: ቀደም ብለን እንዳየነው በአዲስ ኪዳን ደስታና ወንጌል የማይነጣጠሉና ጠንካራ የሆነ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን እንረዳለን:: ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በምንመራበት ጊዜ ጠፍተው የነበሩት በመገኘ ታቸው እኛም አብረን ደስታቸውን እንካፈላለን::

## በመከራም ውስጥ ደስታ

በአዲስ ኪዳን ላይ በተመሰረተው ሕይወታችን የሚፍለቀለቅ ደስታ ሊገሰጥ አይችልም የሚለው ስሜታችን ሊከሰት የሚችለው በስጋዊ አስተሳሰባችን አማካኝነት ነው፤ ምክንያቱም ነገሮችን የምንመለከተው ከራሳችን ሁኔታና ከችግሮቻችን አንጻር ብቻ ነው:: አሁን ካለንበት የመከራ አዘቅት ካልወጣን፤ እንኳን ፍልቅልቆችና በፍሰሃ የተጥለቀለቅን ልንሆን በመጠኑም ደስተኞች አንሆንም ብለን እናስባለን:: በነህምያ (12፥43) ያለው ጥቅስ ጠቃሚ ጥናት የሚሆነን ለዚህ ነው:: ነህምያ በኖረበት ዘመን የነበሩት ከስደት የተመለሱ እስራኤላውያን እንዲህ በታላቅ ደስታ የተጥለቀለቁት በትልቅ ችግርና ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ነበር::

ነህምያ በፋርሳዊው ንጉሥ አርጤክስስ ቀዳማዊ የይሁዳ አለቃ ሆኖ ተሹሞ ነበር:: ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላ በከተማው ሁኔታ ነህምያ ተስፋ ቆረጠ:: ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት 43,000 አይሁዳውያን ከግዞት ተመልሰው ነበር፣ ቢሆንም በዚህ ረዥም ጊዜ ውስጥ ያካሄዱት የመልሶ ግንባታ ሥራ በጣም ትንሽ ነበር:: መቅደሱ ቢገነባም የከተማው



ዋና መከላከያ የሆነው ቅጥር እንደፈራረሰ ነበር:: በዚህም የተነሳ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች በተደራጁ ነጣቂዎች በየጊዜው ይሳደዱ ስለነበር ተስፋ በመቁረጥ ሁኔታ ላይ ነበሩ::

ከአንድ ሌሊት የማጣራትና ሁኔታዎቹን የማገናዘብ ሥራ በኋላ ነህምያ አብዛኛዎቹን እስራኤላውያን ቅጥሩን ለመገንባት እንዲረዱት አግባባቸው:: ምንም እንኳን ጠላቶቻቸው በተከታታይ ቢያስፈራሩዋቸውም፣ ሥራቸውን መስራት ግን ቀጠሉ:: እስራኤላውያኑ እያጉረመረሙም ቢሆን ቅጥሩን በሰባት ሳምንታት ውስጥ ሰርተው ጨረሱ::

ለቅጥሩ ዳግም ግንባታ ምረቃ ሕዝቡ በሸለቆው በር ተሰበሰበ:: ከዚያም በኋላ ቅጥሩን ለመዞር በሁለት ወገን ተከፍለው በታቃራኒ አቅጣጫዎች ጉዞ ጀመሩ:: ሁለቱ ወገኖች በተገናኙ ጊዜ በሌላ በር ወደ ከተማው ገብተው ወደ መቅደሱ አቀኑ:: ሕዝቡ በመቅደሱ በደረስ ጊዜም በዚያ ቀን ትልቅ መስዋዕት አቀረቡ፣ ደስም አላቸው:: በብዙ ችግርና መከራ ውስጥ ሆነው በእግዚአብሔር እርዳታ ቅጥሩን ሰርተው ጨረሱ:: ምንም እንኳን ችግሩ ባያልቅም ትልቅ ደስታ ግን ነበር::

## የሄሲሲዮን ቀናት

ሐሴት ከመዝናናትና ከምቾት ጊዜ ይልቅ በችግርና በመከራ ወቅት እንደሚገኝ የሚነግሩን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪካዊ መጻሕፍት ብቻ አይደሉም:: ይህ ነገር በችግር ውስጥ ባለፉ ሰዎችም ተነግሮናል:: ሰር ቶማስ ሞር በ1535 ዓ.ም. አንገቱን ወደ አንገት መቁረጫው ግንድ ካስገባ በኋላ በፊቱ ላይ በተደቀነው ሞት አልተሸነፈም፣ ይልቁንም ባለቤቱን "በእግዚአብሔር ደስ ይበልሽ" ብሎ አበረታትቶአታል::

"የሄሊሲዮን ቀናት" ብለን የምንሰይማቸው ቀናት፤ በምድር ላይ እጅግ ደስተኞች ሆነን የቆየንባቸው ቀኖችን ነው:: ሄሊሲዮን የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "እሣ በልወፍ" ማለት ነው:: ወፊቱ የኖረችው ወርቃማው ዘመን ተብሎ በሚጠራው የባህሩ ሞገድ ፀጥና እርጭ ብሎ በቆየበት ዘመን ነው:: በባህሩ ሞገድ ላይ ጎጆዋን ሰርታ ልጆቿንም ያለምንም ጭንቀት ታሳድግ ነበር:: እንደዚያ አይነቱ ዘመን ከኤደን ገነት ዘመን ወዲህ አልታየም ከእንግዲህ ወዲህም ሊታይ የሚችል አይመስልም:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የተረከልን የሚፍለቀለቅ ወሰን የለሽ ሀሴት ከዚያ ይልቅ ከሕይወታችን ሊፈልቅ ይችላል:: ያለ "ሄሊሲዮን ቀናት" ሀሴት ማድረግ ይቻላል!

ይሁንና ብዙ ሰዎች ሐሤትን የሚያገኙበት ነገር ከመፈለግ አይቆጠቡም። ስለዚህም ይህን የሐሤት ምንጭ ለማግኘት ከመጣር አለመቆጠብ ይጠቅማል። ቀላሉ መንገድ አስቀድሞ ይህን ሐሤት የማያስገኙ ነገሮችን መዘርዘር ነው።

በመጀመሪያ፣ ሐሤት ከደስታ አይመጣም። እውነቱን ለመናገር ደስታ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አይደለም። በሕይወታችን ከሚከናወኑ ነገሮች ጋር የተቆራኘ ነው። በግልጽ ለመናገር እኛ የሆንነው ወይም በእኛ ላይ የደረሰው ነገር በደስታችን ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ለምሳሌ ነገ ከአንድ የተረሳ አጎታችን ደብዳቤ የምንቀበል ቢሆንና፣ በደብዳቤውም ውስጥ አጎታችን 10,000 ፓውንድ አውርሶን እንደሞተ ቢነገረን፤ ነገ ለእኛ ታላቅ የደስታ ቀን እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። በተመሳሳይ ሁኔታ ነገ በነቀርሳ በሽታ እንደምንሞት ቢነገረን፣ ይኸም በደስታችን ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ያደርጋል። ስለዚህም ደስታችን በእኛ ላይ ከሚሆነው ነገር አንጻር ያቀያየራል። ሐሤት ግን እንደዚህ በመሳሰሉት ነገሮች አይቀየርም፣ ምክንያቱም ምንጩ በአጠቃላይ የተለየ ነውና።

ሁለተኛ፣ ሐሴት ከእኛ ባሕርይ አይመጣም። የሰው ባሕርይ በራሱ ሰውዬውን በሐሤት የተሞላ አያደርገውም። የግሪኩ ሐኪም ሂፖቅራጥስ ከልደተ ክርስቶስ በፊት በሦስተኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ አካባቢ፤ የእያንዳንዱ ሰው ፀባይ የተለያየ መሆኑን የተገነዘበ የመጀመሪያው ሰው ነበረ። ሂፖቅራጥስ የሰውን ፀባያት በአራት መሠረታዊ መደቦች ከፋፍሏቸዋል። በሰውነቱ ውስጥ ካለው ፈሳሽ በመነሳት የሰው ልጅ ፀባይ ሀዘንተኛ፣ ግልፍተኛ፣ ግድየለሽ ወይም ተስፋ የማይቆርጥ ይሆናል። በሰው ስብዕና ውስጥ የሚገኙትን እነዚህን የፀባይ ደረጃዎች ሊያሻሽል የቻለ ማንም ሰው የለም።

ሆኖም የሰው ፀባይ በራሱ ሰውዬውን በሐሴት የተሞላ አያደርገውም። ለሁኔታዎች በቀላሉ እጅ የሚሰጠው ጴጥሮስ ብቻ አይደለም ሐሤትን የሚያውቀው (1ጴጥ 1፥8)፣ እንዲሁም ሐሤት ይልቁን የግትሩና የፅኑው መሪ የጳውሎስ ልምምድም ነበር (ፊል 4፥4)። ፈሪው፣ ተጠራጣሪውና ግዴለሹ አብርሃምም ሀሴትን ደህና አድርጎ ያውቀዋል (ዘፍ 2፥18)። በሁኔታዎች ምክንያት ፀባዩ የሚለዋወጠውና ሀዘንተኛው ሙሴም ሀሴትን የሚያደርግ ሰው ነበር (ዘኁ 1010)። ስለዚህ የሀሴትን ትክክለኛ ምንጭ ማወቅ ከፈለግን አይናችንን ከሰው ፀባይ ምንነት ላይ ማንሳት አለብን። የታሪክ ማስረጃዎችም እንደሚያረጋግጡልን፤ ፀባያችን ምንም ይሁን ምን ሀሴት አድራጊዎች መሆን እንችላለን።



ሦስተኛ፣ ሐሴት ከኃጢአት አይመጣም። መጽሐፍ ቅዱስ ሐቀኛ መጽሐፍ ነው። "ከኃጢአት ከሚገኝ ደስታ" (ዕብ 1፥25) ብሎ ፍርጥ ያለውን ነገር የሚናገረውም ለዚህ ነው። እውነት ነው ለአጭር ጊዜም ቢሆን ያለ ጥርጥር አካላዊና አእምሮአዊ ደስታዎች ከኃጢአት ይገኛሉ። ዘለቄታ ያለው ሐሴት ግን ከኃጢአት አይገኝም።

ይሁንና ደስ የሚያሰኝ ማንኛውም ነገር ሁሉ ከኃጢአት ይገኛል ብለን እንዳናስብ መጠንቀቅ ይኖርብናል። ደስታ የሚለው ቃል ከስሜት ሕዋሳቶቻችን ጋር የሚስማማ ልምድ ነው። ". . .ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ . . ." (1ጢሞ 6፥17)። ስለዚህም በነገሮችና በልምዶች ደስ ቢለንም ዘላቂ ሐሴት ግን ሊያመጡልን አይችሉም።

## የሐሴት ምንጭ

የሐሴት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው። ሐሴት በሁኔታዎችና በእኛ ባሕርይ ላይ አልተመሠረተም፤ ነገር ግን መሠረቱ እግዚአብሔርና እና ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ነው። እርሱ ለወደደንና ስለማይቀየር በችግሮቻችን ሁሉ የእርሱ መሠረታዊ ጥበቃ አለን። የሐሴት ሚስጥሩ ይኸው ነው። በነህምያ መጽሐፍ ያለው ጥቅስ፣ እግዚአብሔርም በታላቅ ሐሴት ደስ አሰኝቶአቸዋልና ይለናል። ለዚህም ነው ጳውሎስ ሐሴትን እንዱ የመንፈስ ፍሬ ነው ያለው። ሐሴትን በሰው ህይወት ውስጥ በምናይበት ጊዜ እግዚአብሔር በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ በሥራ ላይ ለመሆኑ ማስረጃ ነው። ስለዚህ ሐሴት ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣ ነው።

## የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም አይሁን

ጳውሎስ በኤፌሶን 5፥4 ላይ "የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም አይሁን" ሲላ አንዳንድ ክርስቲያኖች ሐሴት ከማድረግ፣ ከመደሰትና ከመሳቅ ይቆጠባሉ። ነገር ግን ጳውሎስ ስለሚያሳፍር ንግግርና ስንፍና ተናገረ እንጂ ስለመሳቅ አልተናገረም። ጂ.ኤስ.ዌል የክርስቲያን መሠረት እምነት በሚለው መጽሐፉ ውስጥ አንዱ የሰው ልዩ ባሕርይ የሚስቅ እንስሳ መሆኑ ነው ብሏል። ስለዚህም ይህ ባሕርይ ልክ እንደ አካላዊና አእምሮአዊ፣ የመንፈሳዊ ተፈጥሮም ባሕርይ ነው። ሄልሙት ቲየሊክ ይህን አመለካከት የሚቃወሙትን ሰዎች እንዲህ በማለት ይነቅፋቸዋል፣ "ሣቅ ስንል በአይኖቻችን አካባቢ የሚፈጠሩ መስመሮች፤ የጠንካራ እምነታችን መግለጫዎች እንደሆኑ በምንቆጥራቸውና ኮስተር ስንል በግንባራችን ላይ እንደሚዘረጉ ሌሎች መስመሮች እኩል ውስጣችንን ለመግለጥ ብቃት እንዳላቸው እንዴት

ተዘነጋን? ቆምጫጫነትን ያጠመቀው (ክርስቲያን ያደረገው) ሣቅን ደግሞ የእህዛብ አድርጎ የፈረጀወ ማነው? ከቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጥሩ ነገሮችን እንዲጠፉ ፈቅደናል፣ እንዲሁም ዕንቆቻችንን በእሪያዎች ፊት ጥለናል። ቤተክርስቲያን ሳቅን ከመቅደሷ አባርራ ለግብዣዎችና ለምሽት ክበቦች ስትሰጥ ያኔ በመጥፎ መንገድ እየተጓዘች መሆንዋን እናውቃለን።"

### የፋሲካ ሳቅ

የምናስተውለው የመጨረሻ ነገር ቢኖር ሐሴት ተቀጣጣይ መሆኑን ነው። በነህምያ ዘመን፣ ሐሴቱ አጠገባቸው ወደ ነበሩት ሕዝብ ተስፋፋ መጽሐፍ ቅዱስ "የኢየሩሳሌምም ሐሴት ከሩቅ ተሰማ ይለናል።" በየትም ወቅት ሐሴት በቤተክርስቲያን በሚጀምርበት ጊዜ ቶሎ ብሎ ይቀጣጠላል። ኢሊኖስ ውስጥ በሚገኘው ዊተን ኮሌጅ፤ ለይተን ፎርድ በተገኙበትና የእግዚአብሔር መንፈስ በተንቀሳቀሰበት ጊዜ ዲሬክተሩ እንዲህ አሉ፣ "እንደዚህ ዓይነት ተቀጣጣይ የፈገግታ ርችት አይተን አናውቅም!"

በመካከለኛው ዘመን የቤተክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ከመቋቋሙ በፊት በፋሲካ ዕለት ካህኑ ይቆምና ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያነባል። ብዙውን ጊዜ ሕዝቡ በሙሉ በትንሣኤው ታሪክ ይነካና ድንገት የፋሲካን ሳቅ ይስቃል። እንዲህ ዓይነቱ ተቀጣጣይ ደስታ በአሁኑ ዘመን በቤተክርቲያን ቢከሰት አስደናቂ ውጤት ያመጣ ነበር። የፋሲካን ሳቅ በጣም እንፈልገዋለን።



# ሰላም . . . የመንፈስ ፍሬ ነው

**ገላትያ 5፥22**

## የሰላምህ መሣሪያ አድርገኝ

ስለሰላም ስንናገር፤ ወደ ሰላም ምንነት ዋና ሃሳብ የሚያመራንን መንገድ የሚያመላክተን የአሲሲ ሰው የሆነው ፍራንሲስ ነው። ፍራንሲስ እንዲህ ብሎ ፀለየ፤ የሰላምህ መሣሪያ አድርገኝ። ከዚህ ሰው ፀሎት የምንረዳው ክርስትና ሰላማዊ ኑሮን የመምራት ሀላፊነት መወጣት ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር የሰላም መሣሪያ ሆኖ ማገልገልን ግድ የሚል መሆኑን ነው። ስለዚህ ነው ጳውሎስ ከመንፈስ ፍሬ አንዱ አድርጎ የፈረጀውን ይህን እውነተኛ ሰላም ተረድተነው ወይም ተስማምደነው ከሆነ፣ ሁከትና አመፅ ከሞላበት የህይወት እውነታ ሸሽተን በራሳችን ጠባብ የህይወት መስመር ብቻ መጓዝ አለመሆኑን የምንገነዘበው። መሆን የሚገባወ ግን፤ ሰላም ይመጣ ዘንድ የሰላም ሰዎች ሰላም በሌሰበት ሁኔታና ሰፍራ መካከል መገኘት ነው። እርግጥ ነው በዚህ ሁኔታ ውስጥ በቀላሉ የሰላም መሣሪያ መሆን አይቻልም፤ ነገር ግን በአንድ ነገር እርግጠኞች መሆን እንችላለን፤ ሰላማችን በፍጹም አይደፈርስም። ሰላም በሌለበት በሰላም መኖር ይህ የህይወት አይአዎ (Paradox) ነው። በዚህ ውስጥ ግን ምን አልባት፤ መጽሐፍ ቅዱሳችን ሰላም ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ እውነተኛ ትርጉሙን እንረዳለን።

### ሰላም እንዲህ አይደለም!

በመጀመሪያ፣ ሰላም ማለት እንዲሁ ከእንቅስቃሴ ውጭ ሆኖ መቀመጥ ማለት አይደለም። አንድ ሰራ በበዛበት ቢሮ ውስጥ የሚሰራ ሰው፤ የሰዎች ጫጫታና የስልክ ድምፅ ባይበዛበት ኖሮ እጥፍ ሥራ ሲሰራ እንደሚችል ሊሰማው ይችል ይሆናል። ደግሞም ድንገት ቢሮው ባዶ ቢሆንና ስልኩም ባልተሰመደ ሁኔታ ፀጥታ ቢሰፍንበት "ምን ዓይነት ሰላም ነው!" ይል ይሆናል። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን የሰላም ትርጉም ይህ አይደለም። ሰላም ግርግርና ጫጫታ ባለመኖሩ ምክንያት የሚፈጠር ክስተት አይደለም። ለዚህም ነው ክርስቲያኖች ፋታ በማይሰጥ ኑሮ ውስጥ እየኖሩ ሰላም የሚሆኑት። በ1964 ኮንጎ ውስጥ በሽፍቶች የተገደሉት ሚስዮናዊው ዶክተር ፖል ካርልሰን ጥሩ ምሳሌ ናቸው። ከ100,000 ሕሙማን በላይ ይከታተሉ ነበር። በየሳምንቱ በመቶዎች የሚቆጠሩትን ይጎበኛሉ፣

ቢያንስ በየቀኑ አንድ ቀዶ ጥገና ይደርጋሉ። በእንዲህ ዓይነት በጣም ትልቅ ሥራ ላይ ተወጥረው እያሉ፣ ከመገደላቸው አንድ ቀን ቀደም ብሎ በአዲስ ኪዳናቸው ውስጥ ሰላም የምትለዋን ቃል ጽፈው ነበር።

በሥራ ተወጥረንም ሰላም መሆን ይቻላል። ከሥራ ርቀን ፀጥታን ብቻ የምናውቅ ከሆነ፣ ይህ በአዲስ ኪዳን የምናገኘው ዓይነት ሰላም አይደለም።

ሁለተኛ፣ ሰላም ማለት ጥላቻ ባለበት ቦታ አለመገኘትም ማለት አይደለም። ብዙ አለመስማማትና ጭቅጭቅ የበዛበት ቤት ብንኀበኝ፣ የተሻለ ሰላም ወዳለው ቦታ ለመሄድ እንናፍቃለን። ወደተሻለ ቦታ መሄዳችንና የሁከቱ መቅረት ግን የአዲስ ኪዳን ዓይነቱን ሰላም አይሰጠንም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ሰላም ምቹ ባልሆነና የጥላቻ ጦርነት ባለበት ወቅትም ቢሆን የምንለማመደው ነገር ነው።

ህንዳዊው ክርስቲያን ሳድሁ ሳንዳር ሲንግ ወንጌልን ለሰበከ ብቻ ተያዘና በገበያ መሃል ራቁቱን በአልቅት እንዲሸፈን ተደረገ። ባለስልጣኖቹ ሳድሁ ሳንዳር ሲንግ ሌሊቱን ያብዳል ወይም በፍርሃት ይሞታል ብለው አስበው ነበር። ሆኖም በነጋታው በሕይወት መኖሩንና በእርጋታ ሆኖ ሲያዩት ባለሥልጣኖቹ በጣም ተገረሙ። ከዚያም በኋላ ሲንግ ስለሁኔታው "ጥልቅ የሆነ የውስጥ ሰላም" እንደነበረው ተናግሯል።

ሦስተኛ፣ ሰላም ማለት ከእውነታ መራቅ ማለት አይደለም። ሁላችንም አንዳንድ ጊዜ ካለንበት ቦታ ቀይረን ወደሌላ ቦታ ብንሄድ ሰላም የምናገኝ ይመስለዋል፣ የከተማው ሰው ደግሞ ከከተማው ጩኸትና ጫጫታ ፀጥ ወዳለወ ገጠር አካባቢ ቢሄድ ሰላም የሚያገኝ ይመስለዋል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ባለንበት ቦታና ሁኔታ ውስጥ ሰላም ልናገኝ እንደምንችል ያረጋግጥልናል እንጂ ከእውነታ ለሸሸን ሰላምን እንደምናገኝ አይናገርም።

የዑመር ኻያምን ሩባያት የተባለ መጽሐፍ የተረጎመው ኤድዋርድ ፊዝጌራልድ የተባለው ሰው የተጋፈጠውን የሕይወት እውነታ፤ ምናባዊና ተምኔታዊ ወደሆነ ሕይወት ቢለውጠው ሰላምን እንደሚያገኝ ወሰነ። ውሣኔውንም ተግባራዊ በማድረግ ሁልጊዜ ሰላሙን የምትነሣውን ሚስቱን ተወ፣ ፀጥታው ፍፁም ወደሆነ ገጠር አመራ፣ ለርሱ ተስማሚ በሆነ ስራ ራሱን ጠመደ፣ የሰላም ምሣሌ የሆኑ እርግቦችን ሁሉ በአካባቢው አደረገ። ይሁን እንጂ ሰላም አጥብቆ በፈለገው ቁጥር ከእርሱ ይሸሽ ነበር። የአዲስ ኪዳን ሰላም እውነታን በመሸሽ አይገኝም። ከእውነት በመራቅና መሆን ይገባናል ብለን ወደምናስበው በማምለጥ የአዕምሮን ሰላም አንቀዳጅም።



## ሰላም - የሚያስፈነጥዝ የውስጣዊ እርካታና ወሰንየለሽ ደስታ ምንጭ ነው

አንዳንድ ጊዜ የሚያስፈነጥዝ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው ሰላም የሚለው ቃል ዛሬ የምንጠቀምበትን የሰላም ትክክለኛ ትርጉም ይይዛል፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ልዩ የሆነ ትርጉም አለው። ይኸውም የመንፈስ እርካታ፣ አካላዊ ደኅንነት፣ የአእምሮ ሰላም ነው። በጦርነት ወቅት ሲፈጠሩ የሚችሉ የመከፋፈልና የጥላቻ ስሜቶችን እንኳን ያስረሳል። እንደዚህ ዓይነቱ ሰላም የሚታየው ግን ሰውዬውን የእግዚአብሔር መንፈስ በጠቅላላ ሲቆጣጠረው ነው። ሰላም በዚህ መልኩ በእግዚአብሔር፣ በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለ ፍጹም የሆነ ግንኙነት ነው። ስለዚህም ሄልሙት ቲየሊክ ሰላም "የረጋና የሚያስለች ሳይሆን፣ የሚያስፈነጥዝ እርካታና ወሰን የሌለው ደስታ ምንጭ ነው" ማለቱ አያስገርምም።

ይህንኑ የሰውን ሁለንተናዊ ህይወት የሚዳስሰውን "ሰላም" የሚለውን ሀሳብ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ በብዙ ልዩ ልዩ ትርጉሞቹ ተጽፎ እናገኘዋለን። ፍጹም ስሆን ድል ይጠቀማል (1ነገሥት 22፥27-28)፣ በአካላዊ ጤና (መዝ 38፥3)፣ ጓደኝነት (ኤር 20፥10)፣ መሲሁ የሚነግስበት ዘመን (ኢሳ 9፥6)፣ ብልፅግና (ኢዮ 15፥21)፣ ደኅንነት (ዘፍ 43፥27) የጸጥታና የመረጋጋት ጊዜ (መሳ 6፥23፣ ኢሳ 32፥17)። የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች ይህን ሰፊ ትርጉም የያዘውን የዕብራይስጥ ቃል ጠቅልለው ሰላም የሚል ቃል የሰጡት ሲሆን፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሙበት ስፍራ ሁሉ የቀደመ ትርጉሙን እንደጠበቀ ቆይቷል።

## ከራስ ጋር ጦርነት

ብዙ ሰዎች ሰላም የላቸውም፤ ምክንያቱ እራሳቸው በውስጣቸው ጦርነትን ተሸክመው ስለሚንቀሳቀሱ ነው። ከሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ ሊመነጩ ከሚችሉ አራት መሠረታዊ ሁኔታዎች የተነሳ፤ ሊኖራቸው የሚገባው ሰላም በውስጣቸው በሚፈጠሩ ቅራኔዎችና ግጭቶች ሳቢያ ያለማቋረጥ ይደፈርሳል።

አንደኛ፤ እረፍት የሌለው መንፈስ። በአራተኛው ክፍለ ዘመን የኖረው ሰሜን አፍሪካዊው ጳጳስ አጉስቲን እንዲህ ይላል። በአንተ ውስጥ እረፍትን እስከታገኝ ድረስ ልብ ሁልጊዜ እረፍተ ቢስ ናት። ዘመናዊው ሰው ተቅበዝባዥ የሆነ መንፈሱን ለማሣረፍ የማይሞክረው ድርጊት የለም። ከግብረስጋ ግንኙነት የሚገኝ የፍትዎት እርካታ

ጀምሮ፤ እይምሮውን በልዩ ልዩ ነገሮች እስከመጠቅጠቅ ባለ ድርጊት ሊረጋጋ ይሞክራል። ይሄው ቅብዝብዝ የሆነ መንፈስ ነው ሰዎች ከንጋት እስከ ውድቅት ራሳቸውን በሥራ እንዲጠምዱ ግድ የሚላቸው። እንዲህ የሚያደርጉት ግን በሥራ መወጣጠሩን ፈቅደው ሳይሆን፤ እግዚአብሔር ብቻ ሊያረካውና እንደረጋ ውቅያኖስ ጸጥ ሊያሰኘው ከሚችለው እስጨናቂና እረፍት የለሽ መንፈሳቸው ለማምለጥ ነው።

ሁለተኛ፣ ራሱን የሚከስ ህሊና። ራሱን የሚከስ ህሊና ዕረፍት ካጣው ልብ ጋር ይመሳሰላል፣ ምክንያቱም ሁለቱም ለማስታገሻ የሚሆን ሰው ሰራሽ መድኃኒት የላቸውምና። ይህን ጉዳይ በምሣሌ ለማብራራት፤ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የኖረውን ለውጥ አራማጅ የቶማስ ቢልኒን ሕይወት ከማየት የተሻለ ምርጫ የለም። ቶማስ በ1519 በካንብሪጅ ዩኒቨርስቲ ውስጥ እያለ ሰላምን ለማግኘት ያልቆፈረው ገደል ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም። በካህናት ፊት በደሉን ቢናዘዝና ብዙ ማስተሰረያ ነገሮች ቢያደርጉለትም፤ ራሱን የሚከስ ህሊና ግን ከቶ ሊፈወስ አልቻለም። ቢልኒ ራሱ እንዲህ ሲል ጉዳዩን ያስቀምጠዋል፤ “ነፍሴ እጅጉን ታማ ነበር፤ የውስጤንም ሰላም አጥብቄ ፈለግሁ፤ ግና የትም ስፍራ አላገኘኋትም”።

የቶማስ የውስጥ ሰላም ጥያቄ መልስ የመጣለት፤ በጊዜው በላቲን ቋንቋ አዲስ በተተረጎመውና በኢራስመስ በታተመው የኢዲስ ኪዳን ቅጂ ውስጥ ነበር። ቶማስ ቢልኒ መጽሐፉን እንብቦ ከጨረሰ በኋላ እንዲህ አለ፣ በእነዚህ ቃላት ውስጥ ተለወጥኩ! ቢልኒን የለወጠው ቃል ደግሞ እንዲህ የሚል ነበር፤ ህጢያተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው። ቶማስ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤ “ይህች አንዲት ዓረፍተ ነገር፤ ልክ የጨለማን ጉልበት ሰብሮ ድንገት ብልጭ እንደሚል የብርሃን ወጋጋን ለተቀጠቀጠው መንፈሴ ትንሳኤን ሰጠው።” ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠው የህጢያት ይቅርታ ብቻ ነው ከውስጥ እየጮኸ የሚከስን ህሊና ፀጥ ሊያሰኝ የሚችለው።

ሦስተኛ፣ ብቸኛ ልብ። ስለ ሐረጉ እንነጋገር ብንል ልክ በቴሌቪዥን የሚተላለፍ የአንድ አስቂኝ ቴያትር (ኮሜዲ) ርዕስን ይመስላል፣ ይኸውም በመሠረቱ በዚህ በወደቀችው ዓለም ውስጥ ማንኛ ውም ሰው ብቸኛ መሆኑ ነው። ብቸኞቹ በዕድሜ የገፉት፣ ያላገቡት፣ ወይም በከተማ የሚኖሩት ብቻ አይደሉም፣ ይህ በማንኛውም የሰው ሕይወት የተከሰተ እውነታ ነው።

እንደዚህ መሆን አልነበረበትም፤ ይሁንና ሰው ራሱን ከእግዚአብሔር በሚያገልበት ጊዜ ከሰዎችም ራሱን ያገላል። ይኸ ደግሞ የውድቀቱ አንዱ ውጤት ነው። አንድ ኅብረተሰብ ከእግዚአብሔር



የመራቁ ጉዳይ እየጨመረ ይሄድና ሰዎች የበለጠ የብቸኝነት ስሜት ይሰማቸዋል። ብቸኝነት ለጊዜው ሊደበቅ ይችላል፣ እንዲያውም ለጊዜው ሊረሳም ይችላል፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ግንኙነት ስንጀምር፣ በእርሱ በኩል ደግሞ ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ይታደስና ብቸኝነቱ በጠቅላላው ይወገዳል። የሰውን ዘር ከሚያስጨንቁ መሠረታዊ ምክንያቶች አንዱ ብቸኝነት ነው።

አራተኛ፣ የተጨነቀ አእምሮ። ለዚህ ውስጣዊ ግጭት አብይ ምክንያት ፍርሃት ነው። ካሁን ቀደም እንደጻፍኩት፤ በጣም የታወቀው የቴሌቪዥን የዳንስ ቡድን “የፓን ሕዝብ” ይባላል። እነርሱን በማየት እነዚህ ልቅና ፍጥረታዊ የሆኑ ሰዎች የውስጥ ሰላም ምን እንደሆነ ሚስጥሩን አግኝተውታል ብለህ በቀላሉ እንድታስብ ያደርጉሃል። ይሁን እንጂ ይህ ከእውነቱ የራቀ ነው። “ፓኒክ” (ሽብር) የሚለው ቃል የመጣው ፓን ከሚባል የግሪክ አምላክ ነው። የፓን ሕዝቦች ደግሞ ፈሪዎች ናቸው። ሰውንም ፈሪ የሚያደርገው ከሕይወት ጫና መራቅ ሳይሆን ከእግዚአብሔር መራቅ ነው። በምድር ወገብ አካባቢ ባለው ጫካ ውስጥ አዲስ ጎሣ ብናገኝ፣ ሕይወታቸው ብዙውን ጊዜ ከሰላም ይልቅ በፍርሃት የተሞላ ነው። ፍርሃት፣ ሽብር፣ ጭንቀት፣ እነዚህ ሁሉ በወደቀው ዓለም ውስጥ የመኖር ውጤቶች ናቸው።

## ሰላማዊ ሕዝብ በክፋው ዓለም መካከል

ጥንታዊው የቻይና ምሳሌ ይህን እንዲህ በማለት ያጠቃልልናል፣ ከመንግሥተ ሰማይ ጋር ሰላም ያላደረገ፣ ከራሱ ጋር ሰላም ሊሆን አይችልም! ስለዚህም ከጎረቤቱ ጋር በጭራሽ ሰላም ሊኖረው አይችልም። ልዩ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱሱ ሰላም የሚገኘው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ስናደርግ ወይም ስንታረቅ ብቻ ነው።

እውነተኛውን የሰላም ሚስጥር ካገኘን፣ ሰዎች በዚች በወደቀችው ዓለም ውስጥ ሰላምን ለማግኘት የሚሮጡት ሩጫ በሰፊው ይቀንሳል። በሦስተኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ክርስቲን ለጓደኛው በጻፈው ደብዳቤ ላይ እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፣ “በጣም መጥፎ ዓለም ነው ዶናተስ። የማይታመን መጥሮ ዓለም። ቢሆንም እንዲህ ባለው ዓለም ውስጥ ትልቅ ሚስጥር የበራላቸው ዝምተኞችና ቅዱሳን ሰዎችን አገኘሁ። እኛ በኃጢአት ሕይወት ውስጥ ከምናገኘው ደስታ ይልቅ እነርሱ ሺ ግዜ የበለጠ ደስታ አግኝተዋል። እነርሱ የተናቁና የሚሰደዱም ናቸው! ባይገርምህ ስለዚህም ግድ የላቸውም። እነርሱ የነፍሳቸው ጌቶች ናቸው፣ እንዲሁም ዓለምንም አሸንፈዋል። ዶናተስ እነዚህ ሰዎች ክርስቲያኖች ናቸው፣ እኔም ከእነርሱ አንዱ ነኝ።”

በክፉው ዓለም ውስጥ ያሉት ዝምተኞቹ ሰዎች እነዚህ ክርስቶስን የተቀበሉት ናቸው። ዳግም ልደት ማለት የሰው ህጢያተኝነት ሲፋቅ፣ ተቅበዝባዥነቱ ከእርሱ ሲወሰድ፣ ለውስጠኛው ፍርሃቱና ብቸኝነቱ ምንክንያት የሆነው ነገር ሲወገድ ነው።

በወደቀው ዓለም ውስጥ አሁንም ክርስቲያኖች ይኖራሉ። እንዲሁም ሰሰው የውድቀቱ ውጤቶች በሆኑት በስቃይ፣ በበሽታና በመሳሰሉት ሁሉ ይሰቃያሉ። ሰላም አለን ማለት በእነዚህ በውስጣዊ ስሜቶች አንታወክም ማለት አይደለም። ነገር ግን ይህን ሁሉ አልፎ የሚወጣ ጥልቀት ያለው ሰላም፤ በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር መስርተናል ማለት ነው። አንድ ጥንታዊው መዝሙር እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፣ "ደመናዎች ይመጣሉም ይሄዳሉ፤ መብረቃማ ነጎድጓዶች ሰማይን ጠርገው የሚወስዱ እስኪመስል ያስገመግማሉ፤ እንዲህም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሰላም እንደፀና ይኖራል"። ክርስቶስ አለህ ማለት የአዲስ ኪዳኑ እርግጠኛ የሆነ ሰላም አለህ ማለት ነው። "አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል" (ፊልጵስዮስ 4፥7)።

## የጠላት ፍላፃ ኢላማዎች

የሰው ኅሊና፣ አእምሮውና ልቡ በቀላሉ በማንነቱ ላይ ተጽእኖ ያሣድራሉ። ስለዚህም ዲያብሎስ እነዚህን የጥቃቱ ኢላማዎች አድርጎ ማጥቃቱ አያስገርምም። ዲያብሎስ ያለማቋረጥ የእማኙን የአእምሮ ሰላም ለመሸርሸር የሚሞክር መሆኑን ሁልጊዜ ልንገምተው የሚገባን ነገር ነው።

ዲያብሎስ ይህንን ከሚያደርግባቸው መንገዶች አንደኛው ደግሞ ስንናደድ ወይንም ሲከፋን፣ ጥፋተኞች እንደሆንን እንዲሰማን በማድረግ ነው። ከዚያም አሁን ሰላምህ የት አለ? ብሎ ያሾፍብናል። ጠላትን አጥብቀን ልንዋጋው የምንችለው ራሳችንን በመኮነን አይደለም፣ በውስጣችን የሰላም ስሜት እንዲፈጠር በመሞከርም አይደለም። ነገር ግን የሰላማችን መሠረት ክርስቶስ መሆኑንና እርሱ ያደረገልንን በማስታወስና ከርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት በማጠንከር ነው።

## የመጨረሻው ኑዛዜና ኪዳን

ኢየሱስ የመንፈስ ፍሬን አስመልክቶ ደቀ መዛሙርቱ ልዩ ልዩ የሆኑ ችግሮች እንደሚገጥማቸው ያውቅ ነበር። ለዚህም ነው ተጠንቅቆ የሰላምን ውርስ የተወላቸው። ከመሞቱ ትንሽ ቀደም ብሎ እንዲህ አለ፣ "ሰላምን እተውላችኋለሁ፣ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም"። ማቲው ሄንሪ እንዲህ አለ "ክርስቶስ



በሞተ ጊዜ ውርስን ተወ፣ ነፍሱን ለአባቱ ሰጠ። ሥጋውን የአርማትያስ ሰው ለሆነው ለዮሴፍ፤ ልብሶቹ በወታደሮች እጅ ወደቁ። እናቱን ለዮሐንስ አስረከባት። ሁሉንም ትተው እርሱን ለተከተሉት ደቀመዛሙርቱ ግን ብር ወይም ወርቅ አልተወላቸውም፤ ያወረሳቸው ነገር ከዚያ በብዙ የሚበልጥና መጨረሻ የሌለውን የከበረ ቅርስ ነበር - ሰላም!

ስለዚህም ሰላም ውርሳችን ነው፣ ህጋዊ የሆነ መብታችንም ነው።

# ትዕግሥት . . . የመንፈስ ፍሬ ነው

**ገላትያ 5፥22**

## የመልካም ስነ ምግባር ቁንጮ

በአዲስ ኪዳናችን ውስጥ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ሲተረጎሙ "ትዕግሥት" ለሚለው ቃል አቻ የሆኑ ሁለት ቃላት አሉ። ጆን ክሪሶስቶም አንደኛውን ቃል፤ "የመልካም ስነምግባር ቁንጮ፣ የእውነተኛ ሥራ መሠረት፣ በተፋፋመ ጦርነት መካከል ያለ ሰላም፣ በፈተና ውስጥ ያለ እርካታ፣ በተከበበ ከተማ መካከል የሚሰማ ደህንነት" ሲል ይተነትነዋል። እርግጥም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ላሉ ለሁለቱም ትርጉሞች አግባብ ያለው ትንተና ነው።

"ትዕግሥት" የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ውስብስብ ያለ ትርጉም ያቀፈ ነው። በ1535 ማይልስ ካቨርዴል መጽሐፍ ቅዱስን ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ በተረጎመበት ወቅት፤ በገላትያ ምዕራፍ አምስት ላለው "ትዕግሥት" ለሚለው ቃል "ረዘም ላለ ጊዜ በችግር ውስጥ ፀንቶ መቆም" (Long Suffering) የሚል አዲስ ቃል ፈጠረ። በ1611 ኦቶራይዝድ ቨርዥን የሚባለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ያሳተሙት ተርጓሚዎች፤ ቃሉ ተስማሚና ወደ እውነታ የተጠጋ የአዲስ ኪዳን ትርጉም ሆኖ ስላገኙት እንዳለ ተቀብለው በመጽሐፋቸው ውስጥ አካተውታል። የማይልስ ትርጉም የሚያተኩረው "ግልፍተኛ" ወይም ፈጥኖ በንዴት ቱግ የሚል ሰው ተቃራኒ (ተነፃፃሪ) የሆነ ባህሪ መግለጫ ሆኖ ነው። የክርስትና ሕይወት መገለጫው ረዘም ላለ ጊዜ በችግርና በመከራ ውስጥ ፀንቶ በመቆም ነው።

ትዕግሥት በዚህ መልኩ "መንፈሳዊ" ቃል ነው። ከአዲስ ኪዳን ውጪ በተራ ሥነ ጽሑፎች ውስጥ አይገኝም፤ ይሁን እንጂ ቃሉ አዲስ ኪዳን ከመጻፉም በፊት ወደኋላ ረዥም ታሪክ እንዳለው ይነገራል። በብሉይ ኪዳን ስለ እግዚአብሔር እንዲህ የሚል ሃሳብ እናገኛለን፣ "አንተ ይቅር ባይ፣ ቸርና መሐሪ አምላክ፣ በቁጣም የምትዘገይ፣ ምሕረትንም የምታበዛ ነህ" (ዘጸ 34፥6፤ ነህ 9፥17፤ መዝ 86፥15፤ 145፥8)። ለቁጣ የዘገየህ የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ በተፃፈው ብሉይ ኪዳን ውስጥ በነጠላ ቃል ማለትም "ትዕግሥት" ተብሎ የተፃፈ ሲሆን ይህም "በችግርና በመከራ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ፀንቶ መቆምን" የሚያመላክት ነው። እንግዲህ ስለ ትዕግሥት ስንነጋገር በእግዚአብሔር ባህሪ ውስጥ ዋነኛ ስለሆነ ጉዳይና በማንኛውም ክርስቲያን ሕይወት



ውስጥ ተገልጦ ሲታይ በሚገባው ነገር ላይ እየተወያየን መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

## በትዕግሥት መጠባበቅ ዋጋ የሚያስከፍል ነው

ትዕግሥት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አራት መሠረታዊ ትርጉሞች አሉት፤ አንደኛ፣ ረዥም ጊዜ የሚቆይ ወይም የማያልቅ ትዕግሥት ማለት ነው። ቶማስ ካርላይል እንዲህ ብሎ ነበር፣ "እምነት ካላችሁ መጠበቅ ትችላላችሁ"። ይህ አባባሉ ከራሱ ሕይወት ጋር በእጅጉ ከተቆራኘ ክስተት ጋር የተዛመደ ነው።

በአንድ ወቅት "የፈረንሳይ አብዮት" የሚለውን መጽሐፉን በመጻፍ ላይ ነበር። የመጀመሪያው ጥራዝ እንዳለቀ ካርላይል የመጽሐፉን ረቂቅ ለአስተያየትና ለምክር ወደ ጓደኛው ወደ ጆን ስትዋርት ሚል ወሰደው። ሚል ደግሞ በተራው ለሚስስ ቻፕማን አዋላትና እርሷም መጋቢት 5 ቀን 1834 ማታ ላይ በእሳቱ አጠገብ ሆና ካነበበችው በኋላ ከእሳት ማንደጃው በላይ ባለው ዕቃ መደርደሪያ ላይ ትታው ለመተኛት ትሄዳለች። በነጋታው እርሷ ከመነሳቷ በፊት አገልጋዮቿ የእንግዳ ማረፊያውን ክፍል አጽድተው እሳት ማቀጣጠል ፈለጉ። አንዲት አገልጋይ ከእሳት ማንደጃው በላይ ባለው ዕቃ መደርደሪያ ላይ ያሉ ወረቀቶች ጥሩ የእሳት ማያያዣ እንደሚሆኑ በማሰብ ተጠቀመችባቸው። በወራቶች ጊዜ ውስጥ በብዙ ድካምና ጥረት የተሠራው ሥራ ከመቅጽበት ወደ አመድ ተቀየረ። ቢሆንም ሰፊው የቶማስ ካርላይል ትዕግስት ወዲያው የእጅ ጽሑፉን ሥራ እንደገና እንዲጀመር አስችሎታል።

በተመሳሳይ መልኩ የታዋቂው የሰር አይዛክ ኒውተንን ታሪክ ማውሳት እንችላለን። ኒውተን ለስምንት ዓመታት ያህል አንድ ታላቅ ጥናት እያከናወነ ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ጠዋት ወደ ጥናት ክፍሉ ሲገባ "ዳይመንድ" የተሰኘች ለማዳ ውሻው የሠራችውን ተመለከተ። ለካስ ውሻይቱ በጠረጴዛው ላይ ይበራ የነበረውን ሻማ ጥላው ኖሮ ለስምንት ዓመት የደከመበት የጥናት ወረቀቶች ሁሉ በእሳት ጋይቶ የአመድ ቁልል ሆኗል። አይዛክ ያለምንም ቁጣና ጥድፊያ ወደ ውሻው ተጠጋና "ዳይመንድ . . . ጌታሽን ምን ወደሚያክል ታላቅ ሥራና ችግር ውስጥ እንደከተትሽው በጥቂቱ እንኳን ተረድተሽ ይሆን?" አለና እረጅሙን ስራ እንደገና ለመጀመር በወንበሩ ላይ ተደላድሎ ተቀመጠ።

ጥልቀት ያለው ትዕግስት ከሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ቢሆንም ለሰዎች ካለን እመለካከት ወይም አስተሳሰብ ጋርም በእጅጉ ይያያዛል። ባንድ ኢትዮጵያዊ ሚሲዮናዊ የተነገረ ግሩም የሆነ ታሪክ አለ። ታሪኩም ስለ አንዲት በባለቤቷ ላይ ትዕግስት ስላጣች አፍሪቃዊት ሴት ያወራል።

የትዳር ኑሮ በጣም ስለአደከማት ባልዋ ይበልጥ እንዲወዳት የሆነ ነገር እንዲሰጣት ዶክተር ድረስ ትሄዳለች:: ዶክተሩም ባሎች አስቸጋሪዎችና መጥፎዎች ስለሆኑ ለእነርሱ የሚሆን መድኃኒት ማዘጋጀት ቀላል አለመሆኑን ያጫውታታል:: ቢሆንም እንደዚህ ዓይነት ኃይለኛ መድኃኒት ለማዘጋጀት፣ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብአቶች ለመሰብሰብ የሴትየዋ እርዳታ እንደሚያስፈልገው ይነግራታል:: ከእነዚህ ግብአቶች አንዱ የሆነውን በሕይወት ካለ አንበሳ ጋማ ላይ ሶስት ፀጉሮችን እንደሚፈልግ ያስረዳታል::

ሴትየዋም ለመድኃኒቱ የሚሆን የአንበሳ ፀጉር እንዴት ማግኘት እንደምትችል እያሰበችና እየተገረመች ወደ ቤቷ ትሄዳለች:: ከዚያም መንደር ውስጥ አንድ አንበሳ ምግቡን ፍለጋ ወዲያና ወዲህ እንደሚል ሰማች፤ እሱን ለማባበል ተስፋ በማድረግ ከመንጋው አንድ ትልቅ ፍየል ወሰደችና ባጠገቡ ባለው ዛፍ ላይ አሰረችለት:: እንደጠበቀችውም አንበሳው መጣና ፍየሉን ወሰደው:: በቀጣዩ ቀንም ሴትየዋ ሌላ ፍየል በዛፉ ላይ አሰረችለት:: ድርጊቱን በመደጋገም አንበሳውን ለማላመድ ስትል በሳምንታት ጊዜ ውስጥ የጋጣዋን ፍየሎች እሟጣ ጨረሰች:: ከዕለት ወደ ዕለት ሴትየዋ አንበሳው ዘንድ እየቀረበች እየቀረበች በመጨረሻም አንበሳውን እስከ ማጫወት ደረሰች:: በመጨረሻም አንበሳውን "ስላስቸገርኩህ ይቅርታ አድርግልኝ፣ ነገር ግን ከጋማህ ሦስት ፀጉሮችን ፈልጌ ነበር" ስትል ጠየቀችው:: "በሚገባ እንጂ" አለ አንበሳው፣ "የፈለግሽውን ውሰጂ፤ ምንክያቱም በሰጠሽኝ ፍየሎች ተደስቻለሁ"::

በሚቀጥለው ቀን በድል አድራጊነት የአንበሳውን የጋማ ፀጉር ይዛ ዶክተሩ ዘንድ ሄደች:: እርሱም እንዲህ አላት፣ "በሕይወት ካለ አንበሳ ጋማ ላይ እንዲህ ፀጉር ለማምጣት የቻልሽ እውነትም በጣም ትዕግሥተኛ ነሽ:: ስለዚህ አሁን ወደ ቤትሽ ሂጂና ይህን የሚያክል ትዕግሥት ስትዳርሽና ስባልሽ አሳይው!" አላት::

ክርስቲያን ከምንም በላይ ለሌሎች ሰዎች ወሰን የሌለው ትዕግሥት ማሳየት ይኖርበታል::

## የመከራ በረከት

ሁለተኛ፣ ትዕግሥት ረዥም ጊዜ የሚቆይ ወይም ወሰን የለሽ ፅናት ማለት ነው:: የእዲስ ኪዳን ምሁር የሆነው አልፍረድ ፕላመር ቃሉን "መከራንና መጥፎ ተግባራትን ሳይቆጣና ሳይበቀል ችሎ የሚያልፍ" ይለዋል:: ይሄ ነገሮችን ከመጋፈጥ በቸልታ የማለፍ ዘይቤ ነው ብለን እናስብ ይሆናል፤ እንደዚያ ለማለት ግን አይደለም::



ትዕግስት የሕይወትን እውነታ በቸልታ ማለፍ ሳይሆን እውነታን ገንቢ በሆነና እንዳመጣጡ የመጋፈጥ ክህሎት ነው::

ጆን ቡንያን የተበየነበትን የ13 ዓመት ፍትህ አልባ የእስራት ጊዜውን እጅና እግሩን አጣጥፎ በወህኒ ቤት አላሳለፈም:: እራሱን እስረኛ እንደሆነ አሳምኖ በጨዋ እስረኛ ደንብ የእስር ጊዜውን አልፈፀመም:: ይልቁንም በእመታቶች መካከል ወደር ያልተገኘለትን "የመናኝ ጉዞ" የተባለውን ልጨኛ (Master-piece) መንፈሳዊ ጽሁፍ ለማዘጋጀት በቃ:: ከዚህ መሰለ ባለ ሁኔታም ራልፍ ቫጋን ዊልያምስ የተባለ ወጣት የሙዚቃ ችሎታው እዚህ ግባ የማይባል በመሆኑ ትምህርቱን እንዲያቋርጥ ተነግሮት ነበር:: ይሁን እንጂ ወጣቱ ባሣየው ከፍተኛ የፈጠራ ፅናት ውጤታማ ለመሆን በቅቷል:: ሎርድ ሞንትጎመሪ በተባለው ሰው ሕይወትም የተፈፀመው አስደናቂ ክስተት ተመሳሳይ ነበር:: ሞንትጎመሪ በሳንድሃርስት ቆይታው ወታደራዊ ብቃት ያልታየበት በመሆኑ በጦር ሠራዊት ውስጥ ስፍራ የማይገኝለት ሰው መሆኑ ተነግሮት ነበር:: በታሪክ አስደናቂ የሆነ ነገር ግን ተፈፀመ:: ከላይ የጠቀስናቸው ሁለት ሰዎች ባሳዩት ወሰን የለሽ ፅናት አስተማሪዎቻቸው በእነርሱ ላይ የሰጡት አስተያየት ሁሉ ውድቅ እንደነበር አስመስከሩ!

በ16ኛው ክፍለ ዘመን ኮትስዎልድስ በተባለ ቦታ በኖረ ሰው መቃብር ላይ "እካሌ ሆይ ፍርሃትን ከልቤ አውጥተህ አባርርልኝ:: በክርስቶስና በእግዚአብሔር ፊት እንደምትቀርብ እምናለሁ፤ ምክንያቱም የደገፌህና ከእርሱ ጋር እንድትኖር የጠራህ እርሱ ነውና:: የሕመም ማስፈራራትን ሣቅበት፣ የመጥፎ ዕድል ጡጫን ናቀው፣ ለጨለማው መቃብር ግድ አይኑርህ እናም በክርስቶስ ጥሪ ወደፊት ገስግስ" ተብሎ የተፃፈ በጣም አስደሳች መታሰቢያ አለ:: እንግዲህ የማያልቅ ትዕግስት ነው የመጥፎ ዕድል ጡጫን የሚንቀው::

## የአጭር ጊዜ ጦርነት አይደለም

ሦስተኛ፣ ትዕግሥት ዘላቂ የሆነ ጀግንነት ማለት ነው:: ቶም ፓይን ነበር በፅናት መቆም ተስኗቸው በመፍገምገም ላይ ያሉትን የዋሽንግተን ወታደሮች ሁኔታ ለመግለጽ ሲል "የበጋ ወታደሮች" የሚለውን ሐረግ የፈጠረው:: ይህ የሆነው በ1776 የአሜሪካ ወታደሮች ከምግብና ከጥይት እጥረት የተነሣ በመጥፎ ሁኔታ ላይ በነበሩበት ጊዜ ነበር:: ቡትቷም ልብሳቸውና በተደጋጋሚ መሸነፋቸው የመጨረሻው ውድቀታቸው እይቀሬ መሆኑ እንዲሰማቸው አደረጋቸው:: ነገር ግን ቶም ፓይን "የአደጋ ጊዜ" በሚል ርዕስ የሰየማትን አነስተኛ መጽሔት በማደል ስድል አነሳሳቸው:: መጽሔቷም እንዲህ በሚሉ ቃላት

ትጀምራለች፣ "እነዚህ የሰዎችን ነፍስ የሚፈታተኑ ቀናት ናቸው። በዚህ ፈታኝ የአደጋ ጊዜ ውስጥ ቁርጠኛ ያልሆኑ ወታደሮችና የድል አጥቢያ አርበኞች ከሀገራቸው ጥሪና አገልግሎት የሚያፈገፍጉበት ጊዜ ነው"። ክርስቲያኑም እንዲሁ ለአጭር ጊዜ ጦርነት የተሰለፈ ሠራዊት ብቻ ላይሆን ሁሉን ነገር መቋቋም የሚችል የማያልቅ ጀግንነትም እንዳለው በዚህ ትዕግሥት ያረጋግጥልናል። ዶክተር ደብልዩ ኢ. ሣንግስተር አዘውትሮ አንድ ታሪክ ይናገራል። ይሄውም "የደህንነት ሠራዊት" የሚል አንድ ታላቅ አገልግሎት በተጀመረበት ወቅት አባቱ ባይናቸው ያዩትን አስደናቂ ነገር ነው። ሰዎች ሁሉ ከየአቅጣጫው አዲሱን የዊልያም ቡዝን መንፈሣዊ ሠራዊት በመቃወም ተነሱበት። ይግረም ብሰው በወጣት ወንዶችና ሴቶች የተገነባውን ያንን መንፈሳዊ ሰራዊት ለመጨፍለቅ የአፅም ሠራዊት ተብሎ በተቋቋመ ግብረ ሃይል ውስጥ ብዙዎች ተመዘገቡ።

ለንደን ከተማ ውስጥ ከአንድ መጠጥ ቤት አጠገብ አንድ ወጣት "የደህንነት ሠራዊት" እባል ትንሽ ሕዝብ ሰብስቦ በመስበክ ላይ እያለ፣ ከመጠጥ ቤቱ አንድ ሰካራም ሰው ይወጣል። ሰካራሙ ሰባኪውን በኃይል መትቶ ይጥለዋል፣ ሰባኪው ሲወድቅ የመንገዱ ጠርዝ ራሱን አግኝቶት ኖሮ ከፍተኛ የሆነ ድምፅ አሰማ። የለውዬው አወዳደቅና ያሰማው ድምፅ ለካራሙን ወዲያውኑ ለካሩ እንዲለቀው አደረገው። በመጨረሻም ወጣቱ ሰባኪ ተነሳ፤ ገና ድንዛዜው ባይለቀውም ፈገግ እያለ የመታውን ሰው "እግዚአብሔር ይባርክህ" አለው። ወዲያው ካቋረጠበት ጀምሮም ስብከቱን ቀጠለ። ትዕግስት ለክርስቲያን የማያልቅ ጀግንነት ይለጠዋል።

## ማንንም አይጠላም

በመጨረሻም፣ ትዕግሥት የማያልቅ ይቅርታ ማለት ነው። ካገኘኋቸው በጣም ጥሩ ሰዎች ዶናልድ ካስኪ አንዱ ነው። እርሱ ፓሪስ ውስጥ የሚገኘው የስኮቲሽ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ሲሆን "ታርታል ፒንፐርነል" በተባለው መጽሐፉ ውስጥ አስደናቂ ታሪክ ተናግሯል። በ1940 ቤተክርስቲያኑን ትቶ ወደ ደቡብ ፍራንስ ይሸሻል። እዚያም የካህን ልብሱን ለፈረንሳይ ተቃዋሚው ካባና ጎራዴ ይቀይረዋል። በመጨረሻም ተይዞ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በነበሩት በጣም አስፈሪ በሆኑት እስር ቤቶች ውስጥ ይታሰራል።

ዶናልድ ካስኪ ከእስሩ ችግርና ሥቃይ ተርፎ ነሐሴ 1944 ወደ ፓሪስ ይመለሳል። ለአራት ዓመት ተዘግቶ የቆየውን ቤተክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲከፍት ቁልፉ በመቆለፊያው ውስጥ ተቀርቅሮ መውጣት እምቢ ብሎ ነበር፣ እንዲሁም በሀንፃው ውስጥ ይህ ነው



የማይባል አቧራ ሞልቶታል። ሰደህንነቱ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን በተንበረከከበት ጊዜም በቀሪው የህይወት ዘመኑ ሁሉ የአብርሃም ሊንከንን አባባሎች መመሪያው ሊያደርጋቸው ቆረጠ።

"ለማንም ምንም ጥላቻ፤ ለሁሉም ግን የተትረፈረፈ ምህረት፤

እግዚአብሔር እንዳበራልኝ፣ መቆምን ፀንቶ በእውነት።

እንዲሆን ለትውልዶች የቁስላቸው ፈውስ

በሉ በርትተን እንስራ የጀመርነውን እንጨርስ"

ለሰው ጥልቅ የልብ ሃዘንና መራራነት ቅርብ የስሜቱ መግለጫዎች ቢመስሉም፤ አሳዳጆቹን ያለጥላቻና ያለበቀል እንዲያልፋቸው የሚያስችለው ኃይል ምንጩ ከትዕግስት ነው።

## ታላላቅ ሥራዎች ጊዜ ይወስዳሉ

ሊዮናርዶ ዳቪንቼ የታዋቂዋን የሞና ሊዛን ፈገግታ ለመሳል አራት ዓመት ፈጅቶበታል። እንደዚሁም ታላቁን የትዕግሥት ሕይወት ለማፍራት ጊዜ ይወስዳል። ለዚህም ነው በየትኛውም የሕይወት ሁናቴ በተደጋጋሚ ትዕግሥት እንድናደርግ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረን። ክርስቲያን ትዕግሥትን መልበስ አለበት (ቆላ 3፥12)፣ እንዲሁም በትዕግሥት መራመድ አለበት (ኤፌ 4፥2)። በችግር ጊዜ ማለትም በመከራ፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በወህኒ፣ በሁከት . . . በመራብ በትዕግሥት ማድረግ ይጠበቅበታል (2ኛቆሮ 6፥5-6)። እውነትም እንደነዚህን የመሳሰሉ ፈተናዎችን በትዕግሥት ስንቀበላቸው ደስታን ይፈጥራሉ፤ በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ . . . ይላልና (ቈላ 1፥11፤ ዕብ 12፥2)። በመጨረሻም ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ተስፋ የሚያገኘው በትዕግሥት ነው። እንዲሁም እርሱ ከታገሠ በኋላ ተስፋውን አገኘ (ዕብ 6፥15)።

## ትዕግሥትን እንዴት አገኛለሁ?

አንድ ጊዜ አንድ ወጣት ሰው በመንፈሳዊ ችግር ምክንያት ወደ ፓስተሩ ወደ ጆርጅ ሙለር ይሄድና "ሚስተር ሙለር የክርስትና ሕይወቴ ትዕግሥትን አጥቷልና እባክህ ይህን ትዕግሥት የሚባል ነገር እንዴት እንደማገኘው ብታሳየኝ?" ይለዋል።

ጆርጅ ሙለርም ችግሩ በጣም ከባድ እስመሆኑንና አብረው ተንበርክከው እንዲጸልዩ ወጣቱን ይጠይቀዋል። ፓስተሩም እንዲህ ሲል ጸለየ፣ "ጌታ ሆይ፣ ይህን ወጣት በሕይወቱ ውስጥ ጥቂት መከራን ትሰጠው ዘንድ እፈልጋለሁ። በላምንታት ለሚቆጠር ጊዜ መከራን

ሰጠው! ይኸው በየቀኑና በየደቂቃው ይሆን ዘንድ እጸልያለሁ” ብሎ ፀሎቱን ይጨርሳል::

ወጣቱ ተነሳና ጆርጅ ሙለርን ሳብ አድርጎ፣ “ይቅርታ አድርግልኝ፣ ያልኩህ አልገባህም፣ እኔ የፈለግኩት ትዕግሥትን እንጂ መከራን አይደለም” አለው::

“እርግጥ ነው” አለ ፓስተሩ:: መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ “. . . መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ እያወቅን” ይል የለ እንዴ! ስለዚህም ከዚህ ውጪ በሌላ መንገድ ትዕግስትን አታገኘውም::



# ቸርነት . . . የመንፈስ ፍሬ ነው

ገላትያ 5፥22

## ቀንበሬ ልዝብ ነው

ኳርዝ ስለተባለው የአለት ዓይነት መረዳት ከፈለግን፤ አስቀድሞ ማወቅ ያለብን ከምን ዓይነት አለት ተፈልፍሎ እንደወጣ ሳይሆን ኳርዝ በውስጡ ያካተታቸውን ንጥረ ነገሮች ምንነት መረዳት ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ፍሬም መንፈሳዊ ሕይወታችን የተገነባበት አንድ ትልቅ አለት እንደሆነ ልንገምት እንችላለን:: በዚህ ክፍል አለቱን አለት ካደረጉት ግብአቶች አንዱን ማለትም “ቸርነትን” ነጥለን እንመለከታለን::

### ፍንጭ ሊሆን የሚችል

ኢየሱስ የተጠቀመበት ሐረግ ትርጉሙን ለማየት ግሩም የሆነ ፍንጭ ነው:: በማቴዎስ 11፥30 ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ “ቀንበሬ ልዝብ ነው” እናም “ልዝብ” የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ቸርነት ማለት ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን አንድ ገበሬ ቀንበር በሚፈልግበት ጊዜ ለማስለካት በሬውን አናጢ ዘንድ ድረስ ይዞት ይሄድ ነበር:: አናጢው ልኩን ከወሰደ በኋላ በሬውን ይዞ እንደገና እንዳይመጣ ሲባል ከሆነ ሻካራና ውልግድግድ እንጨትም ቢሆን ከመከራ የሚሆን ቀንበር ይሰራና በበሬው ጫንቃ ላይ ይገባል:: ይህ ሻካራና ውልግድግድ ደግሞ ገና ያስዘበ ቀንበር ስለሆነ በሬውን ይጎረብጠዋል፣ ያመዋል ምቾትም ይነሳዋል::

ኢየሱስ አገልግሎቱን በይፋ ከመጀመሩ በፊት፤ ምድራዊ የሆነውን የአባቱን የዮሴፍን ሙያ እንደተከተለ ይታወቃል:: ከአፈታሪክ እንዳደመጥነው ኢየሱስ በመላው ገሊላ ምርጥ የተባሉ ቀንበሮችን ይጠርብ ነበር:: አንድ ሰው እንዲህ አለ፤ “በዚያን ዘመን ኢየሱስ ወደሚሠራበት ሄዳችሁ በሱቁ ላይ የተለጠፈውን የንግድ ማስታወቂያ ብትመለከቱ፤ እርግጠኛ ነኝ እንዲህ የሚል ጽሑፍ ታነባላችሁ” ቀንበሬ ምቹና በልክ የተሠራ ነው!”:: ስለዚህ አፈታሪክ እርግጠኞች ባንሆንም ኢየሱስ ግን “ቀንበሬ ልዝብ” ነው ማለቱ እውነት ነው::

የበሬውና የቀንበሩ ስእል እንዲሁም “ቸርነት” በሚለው ቃል መካከል ያለው ግንኙነት የቃሉን ግልጽ የሆነ ትርጉም ይሰጠን ዘንድ ይረዳናል::

## ስመስ ሸጋነት

በመጀመሪያ፣ ቸርነት አንድን ሰው በሕብረተሰቡ መካከል በቀላሉ እንዲኖር ያደርገዋል። ኢየሱስም እንዲህ አለ፣ "ቀንበሬ ልዝብ ነው።" በምንም መንገድ አያሳክክም ወይም አይፋተግም። መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ፤ አማኙ በሕብረተሰቡ መካከል በቀላሉ ተቀላቅሎ የሚኖርበትን ክህሎት ያመጣል። የቀድሞው መራራነትና ባላንጣነት ይወገዱና በቦታው የመንፈስ ቸርነት ይተካል። አልፍረድ ፕላመር እንዳለው "ጣፋጭ በሆነ መንፈስ የተሞላ ልብ ሌሎች በቀላሉ ሕይወትን እንዲኖሯት ያደርጋል።" በመከራቸው ቁስል ላይ እንጨትን አይሰድም።

ይህ እንዴት እንደሚሠራ ለማየት ከፈለግን ሰዎች በተፈጥሮ ለምን ቸሮች እንዳልሆኑ ማወቅ አለብን። ቀደም ብለን የጠቀስነው የቻይናውያን ምሣሌያዊ አነጋገር፣ "ከመንግሥተ ሰማይ ጋር ሰላም ያላደረገ፣ ከራሱም ጋር ሰላም ሊሆን አይችልም፣ ስለዚህም ከጎረቤቱ ጋር በጭራሽ ሰላም የለውም" ሲል በደንብ ይገልጸዋል። በቅደም ተከተል መከተል ያለብን እነሆ!

## የጣር ሸለቆ

በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ወይም ሰላም በማድረግ እንጀምራለን፤ ምክንያቱም መራራነትና ጠብአጫሪነት ሁሉ ከልብ ስለሚመነጩና የሰውን ልብ መቀየር የሚችለው እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው። ኢየሱስ እንዳለው "ከልብ ክፉ አሳብ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በውሸት መመስከር፣ ስድብ ይወጣል።" እንዲሁም ከዓመታት በፊት ኤርሚያስ "የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው" ብሏል።

ከጥቂት ጊዜ በፊት፤ ለተወሰኑ ቀናት ዕረፍት ለማድረግ ወደ ባሕር ዳርቻ ለመሄድ ወሰንን። ልጆቹን የት እንደምንሄድ ነግረናቸዋል፣ ቢሆንም የሆቴሉን ስም አልነገርናቸውም ነበር። መኪናችንን ይዘን ልክ ወደ ሆቴሉ መግቢያ አጥፍ ስንል፣ የመኪናው የፊት መብራት የሆቴሉን ስም በደንብ እንድናይ አደረገን። ልጄ ሄለንም ቶሎ ብላ "አ! ለእረፍት የምንቆይበት "የጣር ሸለቆ" የሚባል ስም ባለው ሆቴል ውስጥ ነው እንዴ?!" ስትል በመደነቅ ጠየቀች። ባለቤቴም ሆቴሉ ይህንን ያገኘው የጣር ሸለቆ በመሆኑ ሳይሆን በባህሩ ዳርቻ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ይህንኑ ለማመልከት ብቻ እንደሆነ ገለጠችላት። በነበሩን ጥቂት የእረፍት ቀናት ውስጥ በ1ኛነገስት 8፥38 ያለውን፣ "ማናቸውም ሰው የልቡን ሕመም አውቆ ጸሎትና ልመና ቢጸልይ . . ." የሚለውን ሳነብ ነበር። እውነትም የሰው ልብ የጣር ሸለቆ ነው አልኩኝ።

ደቡብ አፍሪቃ ውስጥ ዶክተር ክርስቲአን ባርናርድ የመጀመሪያውን የተሳካ የሰው ልብ የመለወጥ ቀዶ ጥገና ያደረገ ሰው ነው። አንድ ቀን አዲስ ልብ ከተቀየረለት ከፊሊፕ ብለይበርግ ጋር እየተነጋገሩ እያሉ፤ ዶክተሩ ለውዬውን የተቀየረውን የቀድሞ ልቡን ማየት ይፈልግ እንደሆነ ጠየቀው። ሕመምተኛው በአምንታ ከመለሰ በኋላ፣ ዶክተሩ ከዕቃ መደርደሪያው ላይ አንድ በጠርሙስ ውስጥ የተቀመጠ ልብ አንስቶ በእጁ ላይ አስረከበው። በታሪክ የመጀመሪያው ሰው የገዛ ራሱን ልብ አተኩሮ ከተመለከተ በኋላ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አለ። ከዚያ በኋላም ሁለቱ ሰዎች ስለ ልቡ ተነጋገሩ። በመጨረሻ ፊሊፕ ብለይበርግ፣ "ለካ ይኸው አሮጌ ልብ ነበር ይህን ሁሉ ችግር የፈጠረብኝ" አለና ልቡን ለዶክተሩ አስረክቦ ለዘላለም ትቶት ሄደ።

እኛም ልክ እንደርሱ ማድረግ እንችላለን፤ ለአሮጌው ልባችን ጀርባችንን እንስጥ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲህ ብሏልና፣ "አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ" (ሕዝ 36፥26)።

## ሰላም ከራሳችን ጋር

ሁለተኛው ደረጃ ከራሳችን ጋር ሰላምን መፍጠር ነው፣ ይኸው እንዴ አዲሱን ልብ ካገኘን ከዚያ ውስጥ ሰላምን ፈልገን እናገኛለን። ዶክተር ፖል ሪስ ስለ እንዲት ቤተሰቦቿን በሙሉ ከሥልጣንዋ ቁጥጥር ስር ልታውል የምትፈልግ ለራሷ ግን ሰላምን ስላጣች ሴት ተናግሯል። ምንም እንኳን የሪህ በሽታ ቁራኛ ብትሆንም ፍላጎቷን ልትገታ አልቻለችም። ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቀች በኋላ ግን ራስ ወዳድነትዋን እግዚአብሔር እግር ሥር መጣል እንዳለባት አወቀች። ይኸንን ባደረገች ጊዜ ወዲያው ከበሽታዋ ተፈወሰች። የሪህ በሽታ ሁሉ በራስ ወዳድነት እንደማይመጣ ግልጽ ነው፣ ነገር ግን ሁሉም ራስ ወዳድነት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ቁራኛ ያደረገናል። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ካለን፣ ከራሳችንም ጋር ሰላም ይኖረናል፤ ስለዚህም ራስ ወዳድነቱ ከእኛ ይወሰዳል።

## በሣል ግን ጣፋጭ

ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሲኖረን፣ ከራሳችን ጋር ስላም እንሆናለን፣ ስለዚህም ከጎረቤቶቻችን ጋር ስላም ይኖረናል፤ ይህን ያክል ቀላል ነው። ይህ ማለት ግን ጎረቤታችን ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ስላም

ማድረግ ይፈልጋል ማለት አይደለም፤ ቢሆንም እኛ በእርሱ ላይ ያለንን ግንኙነት ወይም አስተሳሰብ አይቀይረውም።

በሉቃስ 5፥39 "ቸርነት" የሚለው ቃል ለወይን ጠጅ ሲጠቀምበት እርጌውና (በሣል) ጣፋጩ ብሎታል። እርጌው ወይን ጠጅ ለስላሳና ጣፋጭ እንደሆነ ሁሉ እንዲሁ ቸርነት፤ ሻካራነትንና መራራነትን ከሰው ልብ እስኪጠፋ ድረስ ጠርጎ ይወስደዋል። ስለዚህም ቸርነት ኅብረተሰቡን በቀላሉ እንድንቀላቀል ይረዳናል።

## የፍቅር ልብ መንገድ

ሁለተኛ፣ ቸርነት ኅብረተሰቡን በቀላሉ ለመቀላቀል ብቻ ሳይሆን ሰው ኅብረተሰቡን እንዲያገለግል ይረዳል። ኢየሱስ "ቀንበሬ ልዝብ ነው" አለ። ቀንበሩ ምንም ባይስማማው እንኳን፣ እንስሳው አገልጋይ መሆኑን ይናገራል። ቸርነት ሰውን ለስላሳ አያደርገውም፣ ነገር ግን በእርግጥ ተወዳጅ (ጣፋጭ) ያደርገዋል። መንፈስ ቅዱስ ቸርነትን ወደ ሰው ሕይወት በሚያመጣበት ጊዜ ለአገልግሎት ያዘጋጀዋል፣ ይህም በሚኖርበት ኅብረተሰብ ውስጥ በይፋ የተገለጠ ይሆናል።

ሮበርት ሉዊስ ስቴቨንሰን ሰማዋ በተባለች ደሴት ሲኖር ታሞ ነበር፣ ነገር ግን ለደሴቲቱ ነዋሪዎች ትልቅ የሆነ ቸርነቱን ማሳየት አላቋረጠም። ሕመሙ ባሰበትና በጎጆው መግቢያ በር ላይ ቁጭ ብሎ የጫካውን ዛፎች እያየ እንዲውል ተገደደ። አንድ ቀን ጫካው ድንገት ግማሽ ሰውነታቸው ራቁታቸውን በሆኑ ያገሬው ሰዎች ተሞልቶ ዛፎቹን ሲቆርጡ በማየቱ በጣም ተገረመ። ሰዎቹ፣ ስቴቨንሰን ማዕበሉ እየተጠቀለለ ወደ ባሕር ዳርቻው ሲመጣና ሲሄድ ማየት እንደሚፈልግ ሰምተው ኖሮ፣ ከጎጆው ወደ ባሕር ዳርቻው የሚያሳይ ቀጥተኛና ገላጣ መንገድ ይሰሩ የነበሩት ለእርሱ ነበር። ይህንንም ያደረጉት ስቴቨንሰን ላደረገላቸው ብዙ ቸርነት ባለውለታዎች መሆናቸውን ለማሳየት ነበር። ስቴቨንስን ሊከፍላቸው ፈለገ፣ ነገር ግን እነርሱ አልተቀበሉትም፤ ቢሆንም የሰሩት በዛፎቹ መካከል ያለውን መንገድ ራሳቸው እንዲሰይሙት እንዲፈቅድላቸው ጠየቁት። በመሆኑም "የፍቅር ልብ መንገድ" ብለውም ሰየሙት። ማንኛውም ክርስቲያን ኅብረተሰቡን እንዲህ ካገለገለ ከጎረቤቶቹ ዘንድ መልካም ስምና ዝናን ያተርፋል።

## ፀሐይ ሳትጠልቅ ለአንድ አፍታ

ቸርነት እንደዚህ ተግባራዊ ሆኖ ኅብረተሰቡን ማገልገል ካስቻለን፣ በክርስትና ህይወታችን መሠረታዊ በሆኑ በሶስት ጉዳዮች ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል።



ሀ. ጊዜአችንን መስጠት። ጊዜ የሚለውን ቃል ለመግለጽ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ቃላት አሉ። አንደኛው እንዲሁ የተወሰነ ጊዜን ሲገልፅ ሁለተኛው ግን አስጊ ወይም መልካም ጊዜ ማለት ነው። ጳውሎስ በኤፌሶን 5፥16 "ቀኖቹ ክፉዎች ናቸው ዘመኑን ዋጁ" ሲል የተጠቀመበት ቃል "አስጨናቂ ጊዜ" ማለቱ ነው። ለክርስቲያኖች ሁሉም ጊዜ አስጨናቂ ወይም አስጊ ነው። ለዚህም ነው ሮበርት ሞፋት እንዲህ ያለው፣ "የድሎቻችንን በዓል ለማክበር ዘላለም በፊታችን አለ፣ ነገር ግን እነርሱን ልናሸንፋቸው (ወደ ጌታ ልናመጣቸው) ያለን ጊዜ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት የአንድ አፍታ ጊዜ ብቻ ነው"።

ለ. እውቀታችንን መስጠት። ፒተር ክላቨር በ1581 በቨርዱ ስፔይን ተወለደ። ወላጆቹ በጣም ሃብታሞችና ጉድለት ከሌለበት ትውልድ የመጡ ነበሩ። ባርሴሎና በሚገኘው የትምህርት ተቋም ከጨረሰ በኋላ ወላጆቹ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲሄድ ፈልገው ነበር። ምክንያቱም ባለው የቤተሰብ ግንኙነትና ተፈጥሮአዊ ችሎታ በቤተክርስቲያን ውስጥ ቶሎ ብሎ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ይደርሳል ብለው አስበው ስለነበረ ነው። ፒተር ክላቨር ግን በምትኩ ከአፍሪቃ በባሪያ ፈንጋዮች መርከብ ተጭነው ለሚመጡት ባሪያዎች ያገለግል ዘንድ ወደ ካርታጄና ሄደ።

የባሮቹ መርከብ ወደ ማራገፊያው በተጠጋች ጊዜ በዚያ የሚፈጸመው ሂደት ጠንካራና በሳል ሰዎችንም ቢሆን እንኳ ትዕግሥት ያሳጣቸዋል። የግማቱ ነገር አይወራም። በመቶዎች የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች ረዥሙን የባሕር ጉዞ መንቀሳቀስ እስከማይችሉበት ድረስ በሰንሰለት ታስረው ነበር የሚመጡት። ግማሾቹ ሞተዋል፣ ግማሾቹ እየሞቱ ናቸው፣ ብዙዎቹ ታመዋል፣ ሁሉም ግን እጅጉን ንጽህና የጎደላቸው ናቸው።

ፒተር ክላቨር ተፈጥሮአዊ እውቀቱንና ሕይወቱን በባሪያ ፈንጋይ መርከብ ለሚመጡት ሰዎች ሰጠ። በሕይወት ያሉትን ይንከባከባል፣ የሞቱትን ደግሞ ይቀብራል። ስለዚህም ነው ጎቴ የተባለው ሰው "ቸርነት ኅብረተሰቡ እርስ በእርሱ የተሳሰረበት ወርቃማ ሰንሰለት ነው" ያለው።

ሐ. ገንዘባችንን መስጠት። የሚያሳዝነው ነገር ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች ይሰጡ ዘንድ ግፊት ማስፈለጉ ነው። ቸርነት ያለምንም ግፊት ለኅብረተሰቡ አገልግሎት ጊዜያችንን፣ እውቀታችንንና ገንዘባችንን እንድንሰጥ ያስችለናል።

## ዓለም የሚያስፈልጋት ይህ ብቻ ነው

ሦስተኛ፤ ቸርነት አንድ ሰው ኅብረተሰቡን በነፃነት ተቀላቅሎ በቀላሉ እንዲኖር ያስችለዋል። ኢየሱስ "ቀንበሬ ልዝብ ነው" አለ። የምንሸከመው ቀንበር አገልጋዮች መሆናችንን ብቻ ሳይሆን ገገርእችን ማን መሆኑንም ይናገራል። ቸርነትን መልበስ "የእግዚአብሔር ምርጦች" (ቈላ 3፥12) መሆናችንን ያሳያል። ከዚህ ውጪ ከሆንን ግን የአዲስ ኪዳንን ቸርነት አልፈጸምንም ማለት ነው። ኢላ ዊህለር ዊልኮክስ የተባለችው ባለቅኔ ይህንን እውነት እንዲህ ተቃኝታዋለች፦

"ብዙ አማልክት ደግሞም ብዙ እምነቶች፣
ነፋስ በነፈሰበት አቅጣጫ ብዙ ብዙ መንገዶች
ህዘንተኛዋ አለም ግን የምትሻው አንድ ነገር፣
ጥበብ የሞላበትን የቸርነት ትንሽ ተግባር"።

ኅብተሰባችን በቸርነት ተሞልተው ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታቸው መሆኑን በግልጽ የሚያውጁ ወንዶችና ሴቶችን ይፈልጋል።

ድንገት ብልጭ ብሎ ወዲያው ድርግም እንደምትል የእሳት ትንታግ፤ አጅግ አጭር በሆነች የሕይወት ዘመን እማኙ ቸርነትን በተሞላ ቅን ልቡና ተነሳስቶ፤ በተቃውሞ መካከልም እንኳን ቢሆን ኢየሱስን በማህበረሰቡ መካከል ሊመስክረው ግድ ይላል።

## ቸርነት ድል ነሽ ነው

የቺካጎው ሙዲ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ጆርጅ ስዊቲንግ ስለ አንድ ፓስተር የተናገረው ታሪክ አለ። ይህ ፓስተር በፔንስልቫኒያ የሚኖሩ ሁለት ብቸኛ ምስኪን ሴቶችን ያያል። ከቤተክርስቲያኑ አባላት አንዲቷን ሴት እንድትጠይቃቸው ወደ እነዚህ ምስኪን ሴቶች ይልካል። ይህችም ሴት ሁለቱን ሴቶች ለመጎብኘት ቆሻሻማ በሆነ የአትክልት ሥፍራ አቋርጣ ወደ ሴቶቹ ቤት አመራች። ሁለቱ ምስኪንና ጎስቋላ ሴቶች በሩን ከፈቱላት። ቤታቸው በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ነበር። ምንም እንኳን ሴቶቹ በጣም ቆሻሻዎችና ራሳቸውን ያልጠበቁ ቢሆኑም ያች የቤተክርስቲያንዋ ጎብኚ ግን እቅፍ አድርጋ "እግዚአብሔር ይወዳችኋል፣ እኔም ደግሞ እወዳችኋለሁ" ልትላቸው ቻለች።

ከዚያም በኋላ ብዙ የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ምግብ በማምጣትና ቤቱን በደንብ በማጽዳት ረዷቸው። ጓደኝነትም ተጀመረ። እንዲያውም ትንሽ የጸሎት ጊዜም ጀመሩ። በመጨረሻም ሴቶቹ ክርስቶስን ለመቀበል ወሰኑ። በዚያ ጊዜ ግን ቤታቸው የፀዳና የተስተካከለ፣ እነርሱም ተገቢና የፀዳ ልብስ ለመልበስ የበቁ የከተማዋ ዜጎች ሆነው ነበር። ጆርጅ ስዊቲንግ ይኸን ታሪክ ሲናገር ቸርነት ንቁ የሆነ አገልግሎት ማድረግ



አለበት ብሏል። በተጨማሪም፣ "በሕይወት በሚገለጥ ንቁ ተሳትፎአችን የኢየሱስን ባህሪ ማለትም የሞቀ ፍቅሩንና ቸርነቱን ለሌሎች ስንገልጽ ጌታ በእኛ ለመኖሩ ፅኑ ምስክሩ ይህ ነው" ብሏል። ሴቶቹ ክርስቶስን በማግኘታቸው መደነቅ የለብንም። ነገሩ ማርከስ አውሬሊየስ እንዳለው ነው፣ "ከልብ የመነጨ ቸርነት ሁልጊዜም ድል ነሽ ነው።"

## ቸር ለመሆን መጨከን

ፓምቦ ስለተባለ አንድ ሰው የተነገረ ታሪክ አለ። እርሱም መዝሙረ ዳዊትን ሊያጠና ወደ አንድ አዋቂ ሰው ይሄዳል። አዋቂውም ሰው አሰበና በመዝሙር 39 ብንጀመር ጥሩ ነው ብሎ "ከእኔ በኋላ በል" አለና እንዲህ ሲል ጀመረ "በአንደበቴ እንዳልስት መንገዴን እጠብቃለሁ"። ፓምቦ ይህን መስመር ብዙ ጊዜ ደጋገመው። አዋቂውም ሰው የሚቀጥለውን መስመር ሊያስተምረው ሲል ፓምቦም አንዴ ቆይ፣ እነዚህን ቃላት በደንብና በእውነት ከተማርኳቸው በኋላ፣ ሌላ መስመር ለመማር እመለሳለሁ ብሎ ሄደ።

እንደገና ከመገናኘታቸው በፊት ብዙ ወራት አለፉ፣ ከተገናኙም በኋላ ለመማር ዝግጁ እንደሆነ ሲጠየቅ ፓምቦ የቀድሞውን ዓይነት መልስ መለሰ፣ ከ40 ዓመትም በኋላ እንደገና ሲገናኙም አሁንም ተመሳሳይ መልስ መለሰ።

አንዳንድ ሰዎች የዊልያም ሼክስፒርን ሃምሌት በመጥቀስ "ቸር ለመሆን" ጨካኝ መሆን የሚያስፈልግበት ጊዜ እንዳለ ይናገራሉ። በእርግጥ ክርስቲያኖች ፈፅሞ ጨካኝ መሆን የለባቸውም። በምንም መልኩ ይሄ ሁልጊዜ ስሕተት ነው። ቸርነትን ሊያስተምረን መንፈስ ቅዱስ ጥቂት ጊዜ ሳይፈጅበት አይቀርም፣ እናም እኛ እያንዳንዷን ነገር በደንብ መማራችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

# በጎነት . . . የመንፈስ ፍሬ ነው

**ገላትያ 5፥22**

## ኢ-ተለማኒያዊ በጎ ተግባር

"ኢ-ተለማኒያዊ በጎ ምግባር"፤ ይህ በፀሐፊ ተውኔት በርናድ ሾው ለተፃፈ ተውኔት የተሰጠ ርዕስ ነው። ደራሲው ዋናውን ገጸ ባህሪ "ትሁት በራሱ" የሚል ስያሜ የሰጠው ሲሆን ይህን ያደረገው ደግሞ በአረቢያዊው ላውረንስ ታሪክና የግል ባህሪ እውነታ ላይ ተመስርቶ ነበር። የላውረንስ እጅግ ምናባዊ የሆነ አስተሳሰብ ፍጥረታዊ ከሆነ የሰው ባህሪ ጋር ሊጣጣም የሚችል ባለመሆኑ፤ የመልካምነቱ ፍጹምነት ኢ-ተለማኒያዊ ወደመሆን የተጠጋ ነበር። እንዲሁ ደግሞ ብዙዎች በክርስትና ሕይወት የሚታየው ፍጹም የሆነ መልካም ኑሮን አሰልቺና ድብርታም ያደርገዋል ይላሉ።

የስኮትላንዱ ዶክተር ጆን ጎሲብ እንዲህ ብሏል፤ "ብዙዎች እንደ ዋና መፈክር እውነት ነው ብለው የሚቀበሉት ነገር ቢኖር ቅድስና የማይስብ መሆኑን ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረገው ግንኙነት ደግሞ የማይቻልና የሚያሰለች ስለሆነ ሰዎች ደማቅ፣ ደስ የሚያሰኝና የሚስብ ሕይወት ፍለጋ ሌላ ሥፍራ መሄድ አለባቸው"።

ሌሎቹ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ የሆነ ነገርን ይናገራሉ፤ እንከን የሌለውን የአዲስ ኪዳን ሕይወት መኖር ሊታመን የማይችል ጥሩ ነገር ነው። አዲስ ኪዳን የሚያቀርብልን ነገር ሁሉ ከመታመን የሚያልፍና ሰው በሕይወቱ ሊተገብረው ከሚችለው ልምምድ በላይ ነው። እውነት ነው በዓለማዊ ሕይወት የተጠመዱ ሰዎች፣ የመንፈስ ፍሬን መለማመድ ፍፁም የማይሞከሩት ነገር ሆኖ ይታያቸዋል። ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ የሰውን ሕይወት ሲቆጣጠረው፣ በመለኮታዊ መንገድ ሕይወቱ የማያብብበትና ፍሬ የማያፈራበት ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖርም።

### ሊነገር የማይችል ቁንጅና

በጎነት መለኮታዊ እውነታ ነው። አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ መጣና እንዲህ አለው፤ "የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ?" ማቴዎስ እንደሚነግረን ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰለት፣ "ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው።" ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መናገሩ ግልጽ ነው፣ እና



እርሱ ራሱ መልካም (በጎ) መሆኑን እየገለጸ ነበር። የበጎነት መሠረታዊ ትርጉሙ ከልብ የሚፈልቅ ልግስና ማለት ነው። ኢየሱስ "መልካም" ብሎ የገለጸውን አምላክ ጠባብና የማይስብ ነው ብሎ ማሰቡ ከሞራልም አኳያ ቢሆን ትክክል አይደለም። እግዚአብሔር ከመልካምነቱ ወይም ከበጎነቱ የተነሳ ዓለምን በማራኪነቱ ሞላት ብንል የተሻለ ነው።

ዶክተር ፖል ሪስ በአርክቲክ ስለሚገኘው ናንሰን ትንግርታዊ ትእይንቶችና ክስተቶች ይልቁንም ስለ አውሮራ ቦሪያ... ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ "ተገልለውና ርቀው ያሉ እነኝህ የትንሽዋ አለማችን ድንቅ ለፍራዎች፤ በሰው እግር ያልተረገጠ፣ በሰው እጅ ያልቆነጀ ውበታቸውን ማየት ለሚሻ ሁሉ ማንም ሊገምተው ከሚችለው በላይ አስደናቂና ሊነገር በማይችል ቁንጅና የተሞሉ ናቸው"።

ታዋቂው ወንጀል ነክ ልብ ወለድ ፀሐፊ ሸርሎክ ሆልመስ፣ በክርስትና ላይ ያለው አመለካከት ምን እንደሆነ አልተነገረንም። ነገር ግን ምናባዊ የማገናዘብ ብቃቱ እንደ ዶክተር ሪስ ሁሉ ወደ አንድ ዓይነት ድምዳሜ አምጥቶታል። ሆልመስ በእጁ ላይ የጽጌረዳ አበባ ይዞ እንዲህ አለ፣ በአንድ ነገር ላይ እርግጠኛ ወደሆነ ድምዳሜ ለመድረስ እንደ ሀይማኖት አመች ሁኔታ የለም። ልክ በሣይንስ ዘርፍ ያለ ተመራማሪ ወደ እውነት ለመድረስ የሚከተላቸው ደረጃዎች እንዳሉ ሁሉ በእምነትም እንዲሁ ነው።

"ለእኔ ስለ መልካም መግብአ (providence) እርግጠኝነት አንድ አበባ ማስተዋሉ በቂ ነው። ለመኖር የሚያስፈልጉን ምግብን የመሳሰሉ ነገሮች ሁሉ የግድ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ግንኮ ይህች የጽጌረዳ አበባ ትርፍ ነገር ነች። መአዛዋና ውብ ቀለማቶቿ የህይወት ውበት እንጂ ወሳኝ ነገሮች አይደሉም። ትርፍን ነገር የሚሰግስ ቸርነት ያለው ደግሞ በመልካምነት ውስጥ ብቻ ነው። ለዚህ ነው አበቦችን ተመለክተን መልካምን ነገር ተስፋ ማድረግ እንችላለን የምለው"።

የእግዚአብሔርን መልካምነት የምንረዳው አበቦች ብቻ በትርፍነት ጨምሮ ስለሰጠን ነው ብሎ ቢሆን፤ ከሸርሎክ ሀሳብ ጋር አልስማማም ነበር። እርግጥ ነው እነርሱ ትንግርታዊ የሆነ ፍጥረታዊ ውበት ከተገሰጠባቸው ነገሮች አንድ ለበዝ ብቻ ናቸው። ስለዚህም በጎነት የመንፈሳዊ ሕይወት መለኮታዊ እውነታ ነው። ይኸም ማለት የመንፈሳዊውን ሕይወት ለጀመረ ለማንኛውም ሰው በጎ መሆን የሚቻል ነው።

## በጎነት የተሞላ ሰው

በጎነትን በሰው ሕይወት ለማየት ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ "ደግ ሰው" ያለውን የበርናባስን ሕይወት እንመልከት:: የበርናባስን በጎነት የሚያሳዩ ተግባራዊ ነገሮችን ካወቅን፣ ምናልባት በፊታችን ያሉት እኛም ልንሆናቸው የምንችላቸውን መንፈሳዊ መንገዶች መመርመር መጀመር እንችላለን::

በተግባር የሚገለጽ የበጎነትን ትርጉም ለማወቃችን እርግጠኞች መሆን ጠቃሚነት አለው:: ምክንያቱም ዊልያም ብሌክ እንዳለው "ለሌላው ሰው በጎ የሚያደርግ ዘርዘር ባለ መልኩ ግልጽ የሆነ በጎ ማድረግ ይጠበቅበታል፤ ዝም ብሎ ጠቅለል ባለ መልኩ በጎነት ብሎ መጮህ ግን የወሮበላው፣ የግብዙና የሽንጋዩ አስመሳይነት ነው::" ሉቃስ በአዲስ ኪዳን የጻፈው የበርናባለ በጎነት ግን ዘርዘር ባለ መልኩ ተገልጿል::

የመጀመሪያው የበርናባስ በተግባር የተገለጸ በጎነት፤ ለእርሱ ንብረት ማለት የሞግዚትነት አደራ የያዘው ነገር እንጂ የግሉ መጠቀሚያ አይደለም::

ስለ በርናባስ እንዲህ እናነባለን "እርሻም ነበረውና ሸጦ ገንዘቡን አምጥቶ ከሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው"(ሐዋ. ሥራ 4፥37)::

ይህ መግለጫ ቀጥሎ ካለው ጥቅስ ጋር በተጻራሪነት የቆመ ነው:: ሐናንያና ሰጲራ መሬታቸውን ሸጠው የተወሰነውን ለራሳቸው አስቀሩና፣ ሐናንያ ሽያጩን ሁሉ እንዳመጣ ሆኖ በሐዋርያት እግር አጠገብ አስቀመጠው:: እውነተኛ መልካምነት በሕይወታችን ለመገለጡ የማረጋገጫው አንዱ መንገድ የአሰጣጥ ሁኔታችን ነው:: በዚህ ረገድ የራሳችንንም ማንነት መፈተን እንችላለን:: እግዚአብሔር የሰጠንን ነገር ሙጥኝ ብለን በግላችን እንቀን ይዘናል ወይስ እንደ መልካም መጋቢዎች በሞግዚትነት እየጠበቅነው ነው:: ሌሎችም በእኛ ውስጥ ያለውን መልካምነት በአሰጣጣችን ዘይቤ ይመዝኑታል:: ለሰዎች የምንሰጠው እንደ ፍላጎታቸው መጠን ነው ወይም በእኛ አሰጣጥ ልክ ሰዎች ፍላጎታቸውን እንዲመጥኑ በማድረግ ነው?

የጄ.ኤም.ባሪ ተቀጣሪ ስለነበረች ስለአንዲት ታታሪ ጸሐፊ አስደናቂ የሆነ ታሪክ አለ:: እርሷም የአሠሪዋ ቴአትሮች የመክፈቻ ምሽት ላይ ለመገኘት ዕድል ገጥሟት አያውቅም:: አሠሪዋም እርሷን ጋብዟት አያውቅም ነበር:: ነገር ግን እርሷ በቦታው መገኘት እንደምትፈልግ ያስተዋለ የቴአትሩ ዝግጅት መሪ በመክፈቻው ምሽት እንድትገኝና በመድረኩ አጠገብ ባሉት የአንደኛ መዓረግ መቀመጫዎች ትቀመጥ ዘንድ ሁለት ቲኬቶችን ላከላት:: ጸሐፊዋ በደስታ ተዋጠች፣ ነገር ግን ለዚህ ልዩ የሆነ ጊዜ የሚሆን ተስማሚ ልብስ ስለሌላት



ትኬቶቹን መመለስ እንዳለባት ተሰማት:: በመጨረሻው የልምምድ ጊዜ የጸሐፊዋን ችግር ለባሪ ነገሩት:: እርሱም እንዲህ አለ "ችግሩ ቀላል ነው፣ ትኬቶቿን ወደ ዝቅተኛው መዓረግ በሚያስገቡ በሌሎች ሁለት ትኬቶች እቀይርላታለሁ"::

በርናባስ ሰጠ፤ ይህም ነው አንደኛው የበጎነት ተግባራዊ መግለጫው:: መስጠት ሁልጊዜ ፍላጎትን የሚያረካ መሆን አለበት:: እኛ በሰጠነው ልክ ብቻ የሰዎች ፍላጎት እንዲረካ መሞከር የለብንም::

## ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል

ሁለተኛው የበርናባስ ተግባራዊ በጎነቱ ደግሞ ጠላቶቹን ማበሳጨት ወይም መጥላት ሳይሆን መውደድ ነው:: ጳውሎስ ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ደቀመዛሙርቱን ለመቀላቀል ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣ እናነባለን:: ደቀመዛሙርቱ ግን ስለ ጳውሎስ መለወጥ እርግጠኞች ስላልነበሩ ፈሩ:: ከዚያም በኋላ እንዲህ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፣ "በርናባስ ግን ወስዶ ወደ ሐዋርያት አመጣው":: ፍጹም ፍቅር ፍርሃትንና ጥርጣሬን አውጥቶ በመጣል ለወዳጆችና ለጠላቶች ፍቅርን ማሳየት ይፈልጋል:: የበርናባስ የተገለጠ በጎነት ማለትም የተቃውሞን መሰናክሎች ሁሉ አልፎ ወደ ጳውሎስ የደረሰው ፍቅር፤ ሐዋርያው ቀስ በቀስ በሌሎች ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው አስችሎታል::

ቶማስ በስተን የተባለ ሰው ተቃውሞ ባለበት ትልቅ የፍቅር አገልግሎት የተለማመደ ሰው ነበር:: ከሱ ውጭ እንደርሱ ዓይነት አገልግሎት የተለማመዱት ሰዎች ጥቂቶች ናቸው:: በስተን ሰው በሌለበት የስኮትላንድ ክፍል ውስጥ በስልከርክሻየር ኢትሪክ በሚባል ቦታ ውስጥ የአንዲት ትንሽ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ነበር::

ቶማስ በስተን የኢትሪክ አገልጋይ ሆኖ በ1707 በሜይ.ዴይ. ቀን እቦታው ደረሰ:: በዚሁ ቀን ኢንግላንድና ስኮትላንድ በአንድ የዘውድ አገዛዝ ሥር አንድ የሆኑበት ጊዜ ነበር:: መጀመሪያ የኢትሪክ ሕዝብ የወጣቱን አገልጋይ ልብ ተስፋ አስቆርጠውት ነበር:: በዚያን ጊዜ የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ጥቂት ብቻ ነበሩ:: አብዛኞቹ ግን ወራዳዎችና አምላክ የሌላቸው ከመሆናቸው የተነሳ ብዙውን ጊዜ አገልግሎቶች እየተካሄዱ እያለ በቤተክርስቲያኒቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ እየጮኹ ይጣላሉ:: ቢሆንም ቶማስ በስተን ሰዎቹን ይወዳቸዋል፤ እየሄደም ይጎበኛቸዋል፣ በሚስጢርም ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ይመክራቸዋል:: ከዚያም በፍጥነት የኢትሪክ ሕዝብና በአካባቢው ያሉት ሰዎች እሁድ እሁድ ወደ ቤተክርስቲያኒቱ መጉረፍ ጀመሩ:: እንዲሁም ለምክር ወደ

አገልጋዩ ቤት ይመጡ ጀመር፡፡ በቶማስ ቦስተን ሕይወትም ተቃውሞን የሚያልፍ ተግባራዊ በጎነት ያለውን ፍቅር እናያለን፡፡

የቶማስ ቦስተን ስብከት ሁልጊዜ ወንጌልን ያማከለ ነበር፡፡ በመጨረሻም ታሞ በተኛበት ስፍራ ሆኖ የሰንበት አገልግሎቱን ለመቀጠል ወሰነ፡፡ "እጀብ! እንዴት ፀጥ ያለ የሰንበት አምልኮ ቀን ነው፡፡ ፕሮግራሙን በጊዜው አለመጀመሬ ግን ደግ አይደለም . . ." እያለ ወደ መልዕክቱ ክፍል ገባ፡፡ እግሮቹን አጥፎ ወደ አባቶቹ ሊሰበሰብ የተኛበት የሞት አልጋው ወደ ወንጌል መስበኪያ መድረክነት ተቀየረ፡፡ በአቅረቢያ ካሉ ኮረብቶችና ሸለቆዎች የተሰበሰቡት ምእመን ሁሉ ወደ መስኮቶቹ ተጠጉ፡፡ አቅም አጥቶ አልጋውን ተደግፎ ቀና ባለበት ቅጽበት እንኳን ደግነቱ የተቃውሞን መሰናክሎች እንደገና እየዘለለ ሰዎቹ ከእግዚአብሔር ጋር በእውነት እንዲታረቁ ይለምናቸው ነበር፡፡

በቀረችው ኃይል ሁሉ እነሆ የእግዚአብሔር በግ የሚለውን ሐረግ ይሰብክበት ነበር፡፡ በኃይል የሚተነፍስ የደከመ ሰውነት እንጂ አሁን ምንም ኃይል አልቀረውም፡፡ በመጨረሻም እነዚያ ብዛት ያላቸው ሰዎች ቶማስ ቦስተን ሞተ ብለው እርስ በርስ እየተነጋገሩ ቀስ እያሉ ሄዱ፣ እናም በጎ ሰው መሞቱን አምነው ተቀበሉ፡፡

## በጎ ተግባር

ሦስተኛው የበርናባስ ተግባራዊ በጎነቱ ደግሞ በእምነት እንጂ በማየት አለመመላለሱ ነው፡፡ በኢየሩሳሌም ካሉት ደቀ መዛሙርት ከተዋወቀ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ጳውሎስ (በዚህ ጊዜ ገና ሳውል ነበር የሚባለው) ራሱን ለእግዚአብሔር ሥራ እንዲያዘጋጅ ለዘጠኝ ዓመት ወደ ዓረብ አገር ሄደ፡፡ በነዚያ ዘጠኝ ዓመታት መጨረሻ ላይ በርናባስን በአንጾኪያ አገኘው፡፡ በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በኃይል ይንቀሳቀስ ስለነበረ "ብዙ ሕዝብም ወደ ጌታ ተጨመሩ"፡፡ የሚቀጥሉት ጥቂት ቃላት ጠቃሚ ናቸው፣ "በርናባስም ሳውልን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ ወጣ"፡፡ ጳውሎስ በዚህ ጊዜ እንደ ክርስቲያን ሠራተኛ ገና አልተፈተነም፡፡ በርናባስ ገና በማደግ ላይ ያለች ቤተክርስቲያን በእጁ ይዟል፡፡ የሰውዬውን ተግባራዊ የተፈጥሮ በጎነት የምናየው ለያዘው ስራ እሱ ራሱ መሪ ሊሆን እንደማይችል ማስተዋሉ ነበር፣ ስለዚህም ለዚህ ነበር የእግዚአብሔር ምርጥ የሆነውን መሪ ሊፈልግ የወጣው፡፡ በጎነት ሁልጊዜ በእምነት እንጂ በማየት አይመላለስም፡፡ ፍላጎቱ በእግዚአብሔር የተሾመን ማየት እንጂ ራስን በራስ መሾም አይደለም፡፡ ስለዚህ ሉቃስ "በርናባስ ደግ ሰውና መንፈስ ቅዱስም እምነትም የሞላበት ነበር ማለቱ" እያስገርምም፡፡



## ለምንድን ነው በጎዎች የማንሆነው?

ዶክተር ፖል ሪስ አንድ ጊዜ በሕዝቡ ቤተመጻሕፍት ውስጥ ገብቶ በመጻሕፍት መደርደሪያው ላይ የሥነ ልቡና መጽሐፍ ሲያፈላልግ፣ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዓይኑ በአንድ መጽሐፍ ርዕስ ላይ አረፈ፡፡ መጽሐፉም፣ "ለምንድን ነው በጎዎች የማንሆነው?" የሚል ነበር፡፡ ዶክተር ሪስ መጽሐፉን ሲገልጠው በመጽሐፉ የመጀመሪያ ገጽ ባለው ባዶ ወረቀት ላይ እንዲህ የሚል ጥቅስ ያገኛል፣ "ኃጢአት ታሪክን ይጽፋል፤ በጎነት ግን ዝምታ ነው"፡፡ በጎነትን በዓለማዊ መነፅር በሆነ ትርጉሙ ተመልክተነው ከሆነ፣ የጥቅሱ ጸሐፊ ትክክል ነው፡፡ ከበጎነት በላይ ዝምታ ያለው የለምና፡፡ ነገር ግን ፀሐፊው የሚያወራው ስለ አዲስ ኪዳኑ ተግባራዊ በጎነት ከሆነ ግን ተሳስቷል፡፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰው ሕይወት የሚያመጣው በጎነት ታሪክን ይጽፋል፣ እንዲያውም ኃጢአትን ፀጥ ያሰኛል፡፡

### አስተውል!

ታሪክ የሚሰራውን ዓይነት በጎነት ለመኖር ቀላል አይደለም፣ ተቃውሞንና ቁጣን ይቀሰቅሳል፡፡ ይህም ባለፈው ምዕተ-ዓመት በኢድንበርግ ውስጥ ግሬይፍሪያርስ በተባለ ቦታ ላይ በሁለት ሰባኪዎች ታይቷል፡፡ የቀኑ የስብከቱ ዋና ሐሳብ በጎነት የሚል ነበር፡፡ የጥዋቱ ሰባኪ በጎነት መልካም ከመሆኑ የተነሳ ኢየሱስ ለዓለም እውነተኛውን በጎነት ሲያሳያት፣ ወዲያው ሁሉም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ ብሎ ሰበከ፡፡ የማታው ሰባኪ ደግሞ ኢየሱስ እውነተኛ በጎነትን ካደረገ በኋላ፣ ዓለምም ይህን እውነተኛ በጎነት አይታ ልትሰቅለው ፈለገች አለ፡፡

ሁለተኛው ሰባኪ በትክክል እንደገለጸው እውነተኛ በጎነት ወዲያው ተቃውሞን ይቀሰቅሳል፡፡

# ታማኝነት . . . የመንፈስ ፍሬ ነው

**ገላትያ 5፥22**

## ለደጉም ሆነ ለክፉ

ኢየሱስ ተከታዮቹን ብልሆችና ውጤታማ እንዲሆኑ አልጠየቃቸውም፣ ነገር ግን ሁነኞችና ታማኞች ይሆኑ ዘንድ ይፈልጋል። ስለዚህም ታማኝነት በመንፈስ ፍሬ ዝርዝር ውስጥ መገኘቱ አያስገርምም።

### ራስን ከ . . . ጋር ማጣመር

እውነቱን ለመናገር በገላትያ 5፥22 ያለው ቃል "እምነት" የሚል ሲሆን፣ ይኸም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉት እውቅ ቃላት አንዱ ነው። ቢሆንም ዘመናዊ ትርጉሞች "ታማኝነት" ብለው መተርጎማቸው ትክክል ነው። ምክንያቱም የግሪኩ ቃል "ታማኝነት" የሚለው ሐሳብን ስለሚይዝ ነው። "እምነት" የሚለው የእንግሊዝኛው ቃል በመጀመሪያው ሐሳቡ የግል ተአመኔታ ከሚለው ጋር ግንኙነት እንዳለው ማስረጃ አለ። ቃሉ ምናልባትም "ፈይዝ" ከሚለው ከአንግሎ ሳክሶን የመጣ ሆኖ ትርጉሙም "ራስን ከሆነ ነገር ጋር ማጣመር" ማለት ነው። እኛ ራሳችንን ከኢየሱስ ጋር ማጣመር አለብን፤ ይኸም ከቀላል የእምነት እርምጃ ይጀመርና እስከ ዕድሜ ልክ ለእርሱ ታማኞች ሆነን እንቀጥላለን።

የዚህ ቃል አንዱ ዋና ምሣሌያዊ መግለጫ ከብሉይ ኪዳን የመጣ ሆኖ ኢታይ ለንጉሡ ባሳየበት ሁኔታ ላይ ይመሠረታል። ይህም የሆነው የዳዊት ልጅ አቤሴሎም የአባቱን ዙፋን ለመቀማት ባደረገው የመንግሥት ግልበጣ ጊዜ ነበር። አቤሴሎም በተራው ሕዝብ ተወዳጅነትን አትርፎ ስለነበረ፣ ዳዊት ማድረግ የነበረው አማራጭ ወደ ግዞት መሸሽ ብቻ ነበር።

ከኢየሩሳሌም ለዳዊት ማምለጫ የሚሆኑ ብዙ መንገዶች አልተከፈቱም፤ አስተማማኙ መንገድ በስሜን ምሥራቅ ወደ ገለዓድ የሚወስደው ብቻ ነበር። ሆኖም ግን ቀላል ጉዞ አልነበረም፣ ምክንያቱም ሸለቆን መውረድ፣ ዮርዳኖስን የከበቡትን ቁጥቋጦዎች ማለፍና ራሱ ዮርዳኖስን መሻገር ነበረበት። ንጉሡ ለማምለጥና በተቃዋሚዎቹ እጁ እንዳይወድቅ ከተፈለገ ይህ ሁሉ በፍጥነት መደረግ ነበረበት።



ወደ ግዞተ የሚሸሹትን የንጉሣዊ ቤተሰቦች ቁጥር በትክክል መገመት አይቻልም። የ?ዊት ቤተሰብ ታማኝ አባላትና (አገልጋዮች) የዳዊት የግል ጠባቂዎች መኖራቸው ግልጽ ነው። አብዛኞቹ የውጭ ሃገር ወታደሮች የዳዊትን የግል ጥበቃ ግብረ ኃይል ጨምሮ ምናልባትም ወደ አንድ ሺ ይሆናሉ። ዳዊት እነዚህን ሰዎች ከፈለጉ ትተውት ሊሄዱ እንደሚችሉ ፈቃድ ሰጥቷቸው ነበር፤ ኢታይ ግን በዓለም ላይ ያልታየ አስደናቂ የእምነት ቃል በመናገር ታማኝነቱን አስረገጠ። እንዲህም አለ፣ "ሕያው እግዚአብሔርን! በጌታዬም በንጉሡ ሕይወት እምላለሁ! በእውነት ጌታዬ ባለበት ሥፍራ ሁሉ፣ በሞትም ቢሆን በሕይወትም፣ በዚያ ደግሞ እኔ ባሪያህ እሆናለሁ" (2ሳሙ 15፥21)።

እነዚህን ቃላት በጥንቃቄ ስናስተውላቸው፣ በንጉሡ ፊት የታማኝነትን መሐላ እንደሚያደርግ አንድ ወታደር፣ ለኢየሱስ መታመን ማለት ምን እንደሆነ ያሳዩናል።

### ከዙፋኑ የወረደ ንጉሥ

አንደኛ፣ ታማኝነት ማለት ንጉሥ ከዙፋኑ የወረደና ዘውዱንም የተቀማ ቢሆን እንኳን ያለዙፋኑና ያለዘውዱ ንጉሥን እንደንጉሥ ማወቅና መቀበል ነው። በነበረበት ሁኔታ ውስጥ ዳዊት ቤተመንግሥቱን መተው ነበረበት፣ በዙፋንም ላይ አልተቀመጠም፣ እንዲሁም ዘውዱንና ልብሰ መንግስቱን እንዳልለበሰ መገመት እንችላለን። ከፊት ለፊቱ ያለውን አደገኛ ጉዞ ካወቀ፣ ማንኛውንም ዓይነት ተራ ልብስ መልበስ ነበረበት። ኢታይ ግን እሁንም ዳዊትን እንደ ንጉሥ ስላወቀው ነበር ያለምንም ጥርጥር "በጌታዬም በንጉሡ ሕይወት እምላለሁ!" ያለው።

ዘውዱ የሌለው ንጉሣችንን ለማወቅ፣ ከእኛም እንደዚህ ዓይነቱ ታማኝነት ይጠበቃል። ኢየሱስ ወደዚች ዓለም በመጣ ጊዜ፣ የመንግስተ ሰማይ ልብሰ መንግስቱን አስቀምጦ፣ አልባሌ የሆነ የሰውን ልጅ ልብስ መልበስ ነበረበት። ኢየሱስን መጀመሪያ በወንጌል ታሪኮች ውስጥ አቧራማና ፀሐይ ያቃጠለው ሰው ሆኖ እናየዋለን።

ከኢየሱስ ጋር ከተሰቀሉ ሁለት ሌቦች መካከል፣ አንደኛው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እያለ የኢየሱስ ተከታይ ሆነ፣ ይህም የሆነው ኢየሱስ ከተናገራቸው ነገሮችና መስቀል ላይ ሆኖ ካሳየው ባህሪ የተነሳ ነበር። መጀመሪያ ግን ሌባው ኢየሱስን እንዲሁ እንደማንኛውም እስራኤላዊ ከከፋ ቅጣት የተነሳ በአዝጋሚ ሁኔታ ውስጥ በስቃይ እየሞተ መሆኑን ነበር የሚመለከተው።

ጆን ካልቪን ስለ ሌባው መዳን ሲናገር እንዲህ በማለት አስቀምጦታል፣ "በሞት ውስጥ ሕይወትን፣ በጭንጋፍነት ውስጥ ግርማ ሞገስን፣ በውርደት ውስጥ ክብርን፣ በሽንፈት ውስጥ ድል አድራጊነትን፣ በባርነትም ውስጥ ግርማዊነትን ያስተውል ዘንድ እንደምን ያሉ ፈጣን አይኖች ነበሩት?!"

ኢየሱስን እንደዚያ አድርጎ ለማየት ከሁሉም አስቀድሞ ታማኝነት ያስፈልጋል።

*የሚመጣውን ሁሉ ለመቀበል መዘጋጀት*

በቀድሞዎቹ የሮም ሣንቲሞች ላይ የበሬ ስዕል አለ። በሬውም በማረሻና በመሰዊያ መሃል ቁሟል፤ ከሥሩም "ለየትኛውም ዝግጁ" የሚል ጽሑፍ አለው። ይህ የኢታይን ዓይነት ታማኝነት ይገልጻል፣ ጌታው ለመረጠለት ለማንኛውም ነገር ዝግጁ ነበር። እንዲህም አለ፣ "በእውነት ጌታዬ ባለበት ሥፍራ ሁሉ፣ በሞትም ቢሆን በሕይወትም፣ በዚያ ደግሞ እኔ ባሪያህ እሆናለሁ።"

ሁለተኛ፣ ታማኝነት ማለት አገር የሌለውን ንጉሥ ማገልገል ማለት ነው። ይህ አሁን ላለንበት ሁኔታ ጥሩ ምሣሌ ነው። ይህች አሁን የምንኖርባት ዓለም ሁሉን የሚገዛው የእግዚአብሔር መንግስት አንድ ግዛት ነች። ይሁንና በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ በተፈጸመ አመፅ ሳቢያ አሁን ለጊዜውም ቢሆን በዚህ ዓለም ገዥ ክፉ እጆች ላይ ወድቃለች። እርግጥ ነው ዳዊት እንደሆነው ሁሉ ጌታችን በስደት አልተንከራተተም። ክፉው ዓለምን ቢቆጣጠርም፤ ዛሬም ቢሆን ኢየሱስ በሉአላዊ ግርማው፣ በስልጣኑና በሀይሉ ብርታት እንደፀና አለ። የክፉው ወረራ ስላለ የኢየሱስ ተከታዮች ሁልጊዜ በረከትን ብቻ አይጠብቁም፣ አስቸጋሪ ጊዜያትም ይኖራሉ። ስለዚህም ለየትኛውም ሁኔታ ዝግጁዎች መሆን አለብን።

በካምፓላ መንገድ ዳር አንድ መስቀል አለ። ይህም ባለፈው ክፍለ ዘመን ለሞቱት "የካምፓላ ሰማዕታት" የማስታወሻ ምልክት ነው። ሰማዕታቱ ጠማማና ብልሹ ለነበረው የምሥራቅ አፍሪቃው ንጉሥ ሙዋንጋ በተላላኪነት የሚሠሩ ወጣት ወንዶች ነበሩ። እርሱ ወጣት ወንዶቹን ለግብረ ሰዶማዊ ርካታው ፈልጓቸው ነበር፣ ሆኖም እነርሱ ክርስቲያኖች ስለነበሩ አልተቀበሉትም።

"እምቢ ብትሉ፣ በሕይወት ሳላችሁ በእሳት ትቃጠላላችሁ" ተብለው ነበር።

በዚህ ሁሉ ማስፈራራት ግን ለሙዋንጋ አልተበገሩም። ስለዚህ 39 ወጣት ወንዶች ባንድነት በሰንሰለት ታስረው ለመሞት ወደ



ናሙጎንጎ ተነዱ። ለሞት በሚነዱበት ጎዳና ላይ ሲያመሩ በፍጹም ደስታ ውስጥ ሆነው ይዘምሩ ነበር። እንዲያውም በጉዞው ወቅት በአንደኛው ወጣት ቁርጭምጭሚት ላይ የታሰረው ሰንሰለት አደናቅፎት በመውደቁ ሌሎችም እደናቅፏቸው ተከታትለው ወደቁ፤ ሁኔታው በፈጠረው ከስተትም ሁሉም ተንከትክተው ይስቁ ነበር።

በመቃ ስሌን ተጠቅልለው፣ አንዱ ሌላውን እየተከተለ ወደ ሞታቸው አመሩ። አንዱ ወደ እሳቱ ለመግባት በሚሄድበተ ጊዜ ሌሎቹ "ትንሽ ደቂቃዎች ብቻ፣ ከዚያም በኋላ ከጌታ ጋር ትሆናላችሁ። ይህን ልናደርግ ያበቃን ምክንያት ቢኖር፣ ያ የተከተልነው እርሱ ለእኛ ብሎ መስቀል ስለተሸከመ ነው" እያሉ ያበረታቱት ነበር።

የልጆቹ ታማኝነት፤ ለጊዜው አገር የሌለውን ንጉሥ ለማገልገል አስችሎአቸዋል። አንድ ቅጽበት መዝሙር ሲዘምሩ ቆይተው በሌላው ቅጽበት ደግሞ ሞትን መጋፈጣቸው ለእነርሱ ምንም አይደለም፤ ምክንያቱም ለየትኛውም ነገር ዝግጁ ነበሩና ነው።

## ስንብት

ሦስተኛ፣ ታማኝነት ማለት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ንጉሡን መከተል ማለት ነው። ኢታይ እንዲህ አለ፣ በእውነት ጌታዬ ባለበት ስፍራ ሁሉ፣ በሞትም ቢሆን በሕይወትም፣ በዚያ ደግሞ እኔ ባሪያህ እሆናለሁ። ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኞች ከሆንን፣ ለእርሱ የምንቆጥበው ምንም ዓይነት የሕይወት ክፍል አይኖረንም። በዚህ ረገድ በ1666 ከኖረውና ስኮትላንድ ውስጥ "ቃል ኪዳን" በሚባል ሀብረት ውስጥ አባል ከነበረው ሀዩ መስካይል ጋር የሚወዳደር አስገራሚ ታማኝነት ሊያሳዩ የሚችሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው። መስካይል ለክርስቶስ በነበረው ታማኝነት ምክንያት ወደ ፔንትላንድ ኮረብቶች መኮብለል ነበረበት። ከተያዘም በኋላ ተፈርዶበት እንደ አመፀኛ ከመገደሉ በፊት በሕዝብ ፊት አሰቃዩት። በኢድንበርግ ሲሰቅሉት ወደ መስቀያው እንጨት ከወሰዱ በኋላ የተናገራቸው የመጨረሻ ቃላቶቹ ለክርስቶስ ያለውን ታማኝነት ያሳያሉ። "ጌታ ሆይ፣ አሁን ለፍጥረታት መናገር ትቼ ከአንተ ጋር አወጋለሁ። አሁን ፍጻሜ የሌለውን ዘላለማዊ የሆነው የሕይወት ጉዞ ከአንተ ጋር እጀምራለሁ። ደህና ሁኑ አባቴና እናቴ፣ ጓደኞቼና ዘመዶቼ። ዓለምና ደስታዋ ሁሉ ደህና ሁኑ። ደህና ሁኑ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋከብት። እንኳን ደህና መጣህ አምላኬና አባቴ።"

ዛሬ ለእምነታችን መሞት ይቅርና መኖርም ከብዶናል! በየቀኑ ባሉት ፈተናዎችና አስቸጋሪ ሁኔታዎች የምናሳየው ታማኝነት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል። መጋፈጥ ካለብን ብዙ ነገሮች አንዱ መከራ ነው።

## ኑሮ በሣር ቤት ውስጥ

የጥንቷ ቤተክርስቲያን አሁን በምዕራቡ ዓለም ያለውን ዓይነት የምቾት ኑሮ አታውቅም ነበር። ባለፉት ትውልዶች የነበሩት ሚስዮናውያን መከራ ለመቀበል ፍቃደኞች ባይሆኑ ኖሮ፣ አሁን ያለው ክርስትና ጠፍቶ በጠቅላላው አረመኔ በሆነ ዓለም ውስጥ እንኖር ነበር።

በሰሜን አሜሪካ ይኖሩ ለነበሩት ሕንዶች የወንጌልን መልእክት የሰበከው የመጀመሪያው ሰው ዴቪድ ብረይነርድ ነበር። ስለገጠመውም መከራና አስቸጋሪ ሁኔታ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "ሽከሜን የማራግፍበት ወይንም መንፈሳዊ ሐዘኔን ገልጬ የማሳየው ክርስቲያን ጓደኛ የለኝም። ከዚህ ዓለም ምቾት ጋር ሳወዳድረው፣ በድህነት የመጨረሻው አረንቋ ውስጥ ተዘፍቄያለሁ። ምግቤ አብዛኛውን ጊዜ የተቀቀለ በቆሎና ቂጣ ነው። የምኖረው በሣር በተሰራ ቤት ውስጥ ነው። *ሥራዬ* በጣም ከባድና አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን፣ በአገልግሎቴም የማየው ልፅናናበት የምችል ስኬታማ ፍሬ የለም"።

በዘመናችን ያለው የሚስዮናዊ ጥሪ ቀለል ያለ ነው። እንደነ ዴቪድ ብረይነርድ ወደ ሌላኛው የዓለም ክፍል እንድትሄድ የሚጠይቅም አይደለም። ነገር ግን ጥቂት አካላዊ ምቾትን ትተው በቀላል መንገድ ማለትም፣ ምግብ እርካታ አለመሆኑን፣ ትምህርት ጥበብ አለመሆኑን፣ ገንዘብ ሃብት አለመሆኑን፣ ወይም የቅንጦት ሕይወት ደስታ አለመሆኑን የሚሰብከውን የክርስትና መልእክት ለኅብረተሰቡ የሚያደርሱ ሰዎች ይፈለጋሉ።

## በሕይወት መወራረድ

ጳውሎስ አብሮት ስለሚሰራው ስለ አፍሮዲጡ ሲናገር ሕይወቱን ለክርስቶስ *ሥራ* ብሎ እስኪ ሁኔታ ላይ ጣለ ብሏል። "እስኪ" የሚለው ቃል ግሩም የሆነ ታሪክ አለው። በሮማውያን የነበረ በጣም ተወዳጅ የሆነ የቁማር ዓይነትን የሚገልፅ ቃል ነው። አንድ ምሁር አፍሮዲጡ በሕይወቱ ቁማር ተጫወተ ሲል ተርጉሞታል፣ ነገር ግን ጳውሎስ ክተጠቀመበት ቃል ስናስተያየው በጣም ቀለል ያለ ትርጉም ይዟል። ስለዚህ የአፍሮዲጡ ታማኝነት ለክርስቶስ *ሥራ* ብሎ ሕይወቱን እንደ "ቢንጎ" ተጫወተበት፤ "በነፍሱ ተወራርዶ ከጌታ *ሥራ* የተነሳ እስከ ሞት ቀርቦአልና" (ፊል 2፥30)።

ይኸው ቃል በጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ተላላፊ በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ለመጠየቅ ሕይወታቸውን አደጋ ላይ ጥለው ይሄዱ የነበሩትን ክርስቲያኖች ለመግለፅ አገልግሏል። በሦስተኛው ክፍለ ዘመን ካርቴጅ ውስጥ ወረርሽኝ በሽታ በመግባቱ ነዋሪዎቹ ከዚያ ቢሸሹም፣



ክርስቲያኖቹ ግን በሽተኞቹን ለመንከባከብና የሞቱትን ለመቅበር እዚያው ቀሩ። ሳይፕሪያን የተባለ ሰው የቤተክርስቲያኑ ምዕመናን በከተማው ቆይተው የሚሞቱትን እንዲያጽናኑና በበሽታው ተለክፈው የሞቱትን እንዲቀብሩ፣ ሕይወታቸውንም በእስኪ ሁኔታ ላይ ጥለው እንዲያገለግሉ ለምኗቸው ነበር።

ኢየሱስ ተከታዮቹን፣ በአደጋዎችም ውስጥ ቢሆን፣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲያገለግሉት ይፈልጋል።

## ከዳመናት በላይ

"የደህንነት ሠራዊት" የተባለውን ግብረሃይል የመሠረተው ሰው ባለቤት የሆነችው ካተሪን ቡዝ፣ ለክርስቶስ ባላት ታማኝነት በብዙ የሕይወት ዘርፎች ድል ነሺ ነበረች። ለግላጋ ወጣት በነበረችብት በ14 ዓመቷ በአከርካሪዋ ችግር ምክንያት ያልጋ ቁራኛ ሆና ነበር። በ17 ዓመቷ ደግሞ በሣንባ ምች ታማ ነበር። እንደዚህም ሆኖ ግን የስምንት ልጆች እናት ሆናለች፤ ባላትና በሌላት ጉልበት ሁሉ የመጀመሪያዎቹን 25 ዓመታት "በደህንነት ሠራዊት" አገልግሎት ውስጥ ባለቤትዋን ትረዳ ነበር። በባሕርይዋ ዓይነ ዓፋር ስትሆን በተጨማሪም ያልተማረች ነበረች፣ እንደዚህም ሆኖ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም ካፈራቻቸው ታላላቅ ሰባኪዎች አንዷ ለመሆን በቃች። በጊዜው በነበሩት ታዋቂ ምስባኮች ላይ ካትሪን አንፀባራቂ ኮከብ ነበረች።

ዕድሜዋ 60 ዓመት ሲሞላ ጡቷ ሲመረመር ነቀርሳ ተገኘበት። ምንም እንኳን ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የጤንነትዋ ጉዳይ እያሰጋ ቢሄድም፣ መንፈሷ እንደነበር በከፍታ ይበር ነበር። ከመሞቷ ከጥቂት ጊዜ በፊት በዓለም ዙሪያ ለሚገኙት የደህንነት ሠራዊት አባላት እንዲህ ስትል መልእክት ላከች፣ "ውሃ ያዘሉ ደመናዎች ሽቅብ እየተምዘገዘጉ ነው፤ እኔ ግን ከእነርሱ በላይ እየተንሳፈፍኩ ነኝ። በከፍታቸው ላይ እንጂ በጭራሽ ከበታቻቸው አልወርድም"።

በሕይወት ማዕበል ሳንወሰድ በማዕበሉ ላይ እንድንጋልብ የሚያስችለን ለክርስቶስ ያለን ታማኝነታችን ነው።

# የውሃት . . . የመንፈስ ፍሬ ነው

ገላትያ 5፥22

## ዝቅ ባለ ክብር

በቋንቋ ትምህርታችን ውስጥ ቅጽል የስም ገላጭ መሆኑን ብንማርም ብዙ ጊዜ በተቃራኒው ስም የቅጽል ገላጭ ሊሆን እንደሚችል ልብ አንልም። "ኢየሱስ" የሚለው ስም ግን ሁልጊዜም "የዋህ" የሚለውን ቅጽል በእርግጠኝነት ገላጭ ነው።

## የዋህነት ደካማነት አይደለም

ለኢየሱስ የባህሪ መግለጫነት ከተሰጠው የቃሉ ትርጉም አግባብ ውጭ "የዋሃት" የሚለውን ቃል ካየነው፤ ደካማ፣ ጽናት የለሽና ሆሞተቢስ ለሆነ ባህሪ ገላጭ ሆኖ እናገኘዋለን። ነገር ግን "የዋሃትን" ከኢየሱስ የባህሪ ማንነት መግለጫ አንጻር ስንቃኘው በጌታ ሕይወት ደካማነትና ሆሞተቢስነትን እንመለከትም።

በእርግጥም ኢየሱስ ክርስቶስ ካለፈበት እስቸጋሪና ፈታኝ የሕይወት መንገድ የበለጠ ጎዳና ሊጓዙ የሚችሉ ጥቂቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ልዩ ልዩ ትምህርቶቹ ለብዙዎቹ ቀደምት ምሁራን ሞጋች ነበሩ። በግልጽ እንደታየውም ጊዜውን ተአምራቶች በማድረግ ያሳልፍ ነበር። ለወፎች ጎጆ ሳላቸው ማረፊያ የሌለው ሆኖ፣ ረጃጅም ርቀቶችን በእግሩ እየተጓዘ፣ በሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሳይሟሉለት ያሳለፈውን ሕይወት እናስብ። እንዲህ ባለ ፈታኝ ጎዳና እየተጓዙም እንኳን ጌታችን የዋህ ተብሎ ለመጠራት አላፈረም። በአህያ ጀርባ ወደ ኢየሩሳሌም ሊገባ ክብሩ ዝቅ እንዳለበት አልቆጠረም። ዝቅ ያደረገውን ነገር በየዋህነት ተቀበለው።

## የለዘበ ኃይል

የቃሉን ትክክለኛ ትርጉም ካጤንን ኢየሱስ ባንድ ጊዜ ኃያልና የዋህ መሆኑ ብዙ አያስደንቀንም። የግሪኩ ቃል በአዲስ ኪዳን አጠቃቀሙ የሚሰጠው ትርጉም "አንድ እንስሳን ለማልመድ ኃይሉን በቁጥጥር ሥር ማድረግ" የሚለውን ነው። ለምሳሌ አንድ ያልተገራ ፈረስ ብንወስድና ብናለምደው የእንስሳው ግሩም የሆነ ባሕርይው አይጠፋም፣ ይልቁንም አሁን ኃይለኛና ጠንካራ ሆኖ ነገር ግን ለጥቅም መዋሉን እናያለን። ይኸው ነው የ"የዋህነት" ዋናው ሐሳብ። የዋህ ሰው ከስብዕናው የሚጠፋ ነገር የለም፣ ሆኖም የተገራ ጠቃሚ ሰው መሆኑን



እንገነዘባለን። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚለው "ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ የዋህ ሰው ነበረ"። ሙሴ በጣም ጠንካራ ሰው ሆኖ ግን እንደተገራ ፈረስ ዓይነት ግርማ ያለው ነው፤ ከቁጥጥር ውጪ ያልሆነ፣ የታመቀና የተገራ፣ በጥቅም የዋለ ጉልበት አለው።

ስለዚህም የዋህነት ማለት የተገዛ ኃይል ማለት ነው። የዋህ ሰው ኃይለኛነቱን በሦስት መንገዶች የገዛ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሙሴን የየዋህነት ምሳሌ አድርጎ ስለሚጠቅስ፣ በቁጥጥር ሥር የዋለውን የሙሴን ኃይል በሦስት አቅጣጫ ማየቱ ይበልጥ ለመረዳት ይጠቅመናል።

## ዝቅ ካሉት በታች

አንደኛ፣ የየዋህ ሰው ጠንካራነት የሚታየው ስለ ራሱ ባለው ትክክለኛ ግንዛቤ ነው። የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ሙሴ ሲናገር እንዲህ ይላል፣ "ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ"። በሌላ አነጋገር የሙሴ ጠንካራነት እውነተኛውን የትውልድ ምንጩን ማወቁ ነበር። ምንም እንኳን ማንኛውም ሰው ሙሴ የፈርኦን የልጅ ልጅ እንደሆነ፣ ባማሩት የግብጽ ህንጻዎች ውስጥ መንቀባረር መብቱ እንደሆነ እንዲሁም የግብጽ ምድር ልዑልና ገዥ እንደሚሆን ቢያውቅም፤ ሙሴ ግን ለእንዲህ ዓይነቱ ፈር የሚያስለቀቅ ምኞት ስፍራ አልሰጠውም። የዋህነቱ "እኔ የአንድ እስራኤላዊ ልጅ ነኝ" ብሎ እርግጡን ለመግለጽ ረዳው።

እኛም የዋህነታችን ዝቅተኛውን አመጣጣችንን እንድንቀበል ያስችለናል። በኢየሱስ ከመዋጀታችን በፊት የኃጢአት ባሪያዎች እንደነበርን በግልጽ ለመናገር ያስችለናል። የዋህነት እውነተኛውን ምንጫችንን እንድናውጅ ካደረገን፣ ስለተሰጠንም ሕይወት እውነተኛ ባሕርይ እንድናስተውል ያደርገናል። አሁን ያለንበት የሕይወት ሥፍራ ራሳችን ያገኘነው ነው ብለን እንዳንላሳት ያስፈልጋል። ሙሴ እንዲህ በነፃ ሊያገኘው የነበረውን ክብርና ሥፍራ አልፈልግም አለ እንጂ፣ "ባሪያ ነበርኩ፣ አሁን ግን ልዑል ነኝ! ሕይወትን እንዴት እንደተጠቀምኩበት ተመልከቱ" አላለም።

ስለዚህ የየዋህነት ጠንካራ ጎን ምን እንደነበርን ብቻ የሚቀበል ሳይሆን፣ አሁንም ምን እንደሆንን እንድናስብ የሚያስችል ነው። ስለዚህም የዋህ ሰው በእውነትም ትሑት ሰው ነው። ትሕትናው በተደበቀ ትዕቢት ላይ የቆመ ወይም በዝቅተኛነት ስሜት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን፣ ራስን በእውነተኛው ሚዛን ላይ አስቀምጦ በማየት

ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰው ከጳውሎስ ጋር "ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለኔ" ማለት ይችላል፡፡

## ባልተመቸ ጊዜም ራስን መካድ

ሁለተኛ፣ የየዋህ ሰው ሌላው ጠንካራ ጎን፣ ሌሎች ሰዎች ስለሚያስፈልጋቸው ነገር እውነተኛ እመለካከት አለው፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ እንዳለው፣ "ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ" በእንፃሩ፣ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፡፡

የየዋህ ሰው ጥንካሬ ከራሹ ምኞት ይልቅ የሌሎችን ፍላጎት ማስቀደሙ ነው፡፡ ይህ ከቶማስ ኬን የሕይወት ሕግ ጋር የሚስማማ ነው፣ "መምረጥ አቅቶህ ልብህ መዋለል ሲጀምር ደካማ መስሎ ወደሚታየው ምርጫ አዘንብል፡፡ ወደ ብልጽግናና ወደ ክብር በሚወስደው መንገድ አትጓዝ፣ ይልቁን ወደከስረት እሣር ወደሞላበትና አሣፋሪ ውርደት የምትጠግብበትን አቅጣጫ ያዝ"፡፡ ሙሴም በትክክል ያደረገው እንደዚህ ነበር፡፡ በግብጽ ምድር በባርነት አገር ይሰቃዩ የነበሩትን እስራኤላውያን ወገኖቹን ሲረዳ ከክብር ይልቅ ውርደትን መርጦ ተቀላቀለ፡፡

ትህትና ለሌሎች ጥቅም በመቆም ራስን ዝቅ ማድረግ መሆኑን፤ ከሙሴ ሕይወት በተሻለ መንገድ ምሣሌ መስጠት ቢያስፈልግ ወደኋላ መለስ ብለን ማየት እንችላለን፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወቱ ተግብሮ ያሳየንም በትክክል ይህንን ነበር፡፡ ተሸንፈው የወደቁትን አሸናፊ እድርጎ ከፍ ሊያደርግ የመጣው ወደ ተሸናፊዎቹ ነበር፡፡ በእውነት ትሁት የሆነ ሰው መለያው በሌሎች ችግርና ጭንቀት ውስጥ ራሱን አስገብቶ ሲረዳቸው መሞከሩ ነው፡፡

የዋሆች እንድንሆን የሚያስጨክነን ኢየሱስን ስናይ ነው፡፡ በሩሲያውያኑ መንፈሳዊ ትምህርት ጳጳስ የነበረው ታይከን፣ በሩሳያዊያን አገልጋዮችና በሚያስተምራቸው ተማሪዎች ዘንድ የኢየሰስ ክርስቶስን የሕይወት ስልት ይዞ ነበር የሚመላለሰው፡፡

"የእግዚአብሔር ልጅ ለእናንተ ሲል ትሑት ሆነ፣ እናንተ ትዕቢተኞች መሆን ትችላላችሁን? እርሱ ድሀ ሆነ፣ እናንተ ግን ሃብትን ተከትላችሁ ትሮጣላችሁን? እርሱ ራሱን የሚያስገባበት የወፍ ጎጆ ታክል ቦታ አላገኘም፣ እናንተ ግን ድንቅ የሆኑ ሕንፃዎችን ትፈልጋላችሁን? እርሱ ውርደትን ተቀበለ፣ እናንተ ግን ክብርን ለማግኘ ት ትደክማላችሁን? እርሱ የደቀመዛሙርቱን እግር አጠበ፣ እናንተ ግን ወንድሞቻችሁን ለማገልገል ታፍራላችሁን?"



## ጌታ ከእኛ ጋር ስለመሆኑ እርግጠኞች ነን?

ሶስተኛ፣ የዋህ ሰው ስለእግዚአብሔር ትክክለኛና የጠራ እይታ እንዲኖረው ጥንካሬን የተላበሰ ነው፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ሙሴ እንዲህ ይለናል፣ "የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና"፡፡ እውነተኛ የዋህ ሰው እግዚአብሔርን በየትኛውም ሁናቴ በግልጽ ያየዋል፤ የዋህነት የሌለው ሰው ግን ገና ሕይወት መክበድ ስትጀምር፣ የእግዚአብሔርን ትክክለኛነት መጠራጠር ይጀምራል፡፡ ልክ በምድረበዳ እንደነበሩት እስራኤላውያንም እንዲህ ማለት ይጀምራል፣ "ለመሆኑ ጌታ ከእኛ ጋር ነው ወይንስ አይደለም?" የዋህ ሰው ግን እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ አይጠይቅም፤ ምክንያቱም በሥፍራው ላይ ሆኖ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን የማየት ጥንካሬ አለውና ነው፡፡

## መማር የሚችል የተከፈተ አእምሮ

ሁልጊዜ እግዚአብሔርን የሚያስብ በመሆኑ የየዋህ ሰው አእምሮ በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ለመማር የተከፈተ ነው፡፡ ዳዊት እንዳለው፣ "ለገሮችም መንገዱን ያስተምራቸዋል፡፡" እግዚአብሔር ገሩን ሰው እንዲከተለው የሚያስተምረው የኑሮ መንገድ፣ ዓለም ከምትከተለው የሕይወት መንገድ በጣም ይለያል፡፡ "የኢየሱስ ኃይል" በሚለው መጽሐፉ ዶክተር ሺርውድ ዊርት፣ ሰው በሕይወት ዘመኑ ሁለት ዓይነት አማራጮች እንዳሉት ይነግረናል፡፡ የመጀመሪያው ምርጫ በአስገራሚ ፍጥነት ወደ ነገሮች ሁሉ ከፍታ ላይ መውጣትና በመጨረሻው ግን ከምድር ወርዶ መከስከስ ነው፡፡ ሁለተኛው ምርጫ ደግሞ የኢየሱስ መንገድ ነው፡፡ ይህንን ምርጫ የሚከተል ስለራሱ ማንነት ከእውነታ ጋር የተገናዘበ እይታ በመያዝ ይጀምራል፣ ሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለማሟላት ግድ ይለዋል፣ ስለ እግዚአብሔር ማንነት ሙሉ ግንዛቤን ይጨብጣል፡፡ ስለዚህም በግርግር አይመላለስም፡፡ ወደና ፈቅዶ ዝቅ ያለውን ነገር ይመርጣል ይሁን እንጂ በመጨረሻው በከበረ ስረገላ ላይ ይቀመጣል፡፡ ለዚህ ነው መጽሐፉ "የዋሆች ምድርን ይወርሳሉ" የሚለን፡፡

## ስም አፈር

የዝቅተኛነትን መንገድ መከተል ቀላል ይመስላል፤ አንዳንድ ሰዎች እንዲያውም ጥረትን ማቆም ይመስላቸዋል፡፡ ይልቁንም በተቃራኒው የዋህና ትሑት ለመሆን ብርቱ ጥረት ያስፈልጋል፡፡ በእውነት ትሑት መሆን ማለት ከዓለም የአስተሳሰብና የሥራ አካሄድ በተቃራኒ መጓዝ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን የእውነተኛ ትሕትና ሚስጢር ምን መሆኑን ስናውቅ እግዚአብሔርን መምሰልና እምነታችን እየጨመረ

መሆኑን እንረዳለን፡፤ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ህዩሚሊቲ (ትሕትና) የሚለው ቃል "ህዩመስ" ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "ለም አፈር" ማለት ነው። እንቶኒ ብሉም የተባለው ሰው እንዳለው "ይህን አፈር ልብ ብለን እናስተውለውም። ሁልጊዜ ስለምንጠቀምበት ለእኛ ተራ ነገር ነው። የስባና ቀለሙም ጥቁር ከመሆኑም በላይ እንደዘበት በላዩ ላይ የምንከምራቸውን ውዳቂዎች ወደሃብትነት ይለውጣቸዋል። ማንኛውንም የዘር ዓይነት ተቀብሎ አካል ሕይወትና እድገት ይሰጣቸዋል።"

ይህ ለለም አፈር የተሰጠው መግለጫ የዋህን ሰው በሚገባ ይገልጸዋል። የዋህን ሰው ሌሎች ላያስተውሉት ይችላሉ፣ ነገር ግን ማንኛውንም ነገር ይለወጣል። የዋህ ሰው ለሚሠራው ነገር ሁሉ አካል፣ ሕይወትና እድገት ይሰጣል። የዋሁ ሰው ራሱን ዝቅ በማድረግ እውነተኛውን የሕይወት መንገድ ያሳያል።



# ራስን መግዛት . . . የመንፈስ ፍሬ ነው

ገላትያ 5፥22

## ራስን መግዛት

ለዚህ መጽሐፍ መነሻ የሆነው አሳብ የመነጨው ከጥቂት ጊዜ በፊት በምስራቅ እንጆሲያ ለመጽሐፍ ቅዱስ ሕብረት (ስክሪፕቸር ዩኒየን) በምሰራበት ጊዜ ነበር። በሳምንት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ቤቴ የምጓዘው በጨለማ ሌሊት ነበር። አንድ ጊዜ እንዲሁ እምሽቼ ወደ ቤቴ ስመለስ፣ የመኪናዬ የፊት መብራቶች በአንድ ሆቴል ቤት የንግድ ማስታወቂያ ላይ አበሩ፣ የሆቴሉም ስም ቴምፐርአንስ "ራስን መግዛት" የሚል መሆኑን አስተዋልኩ። ቴምፐርአንስ "እራስን መግዛት" የሚለው ቃል በዚህ ሆቴል በር ላይ፤ ከያዘው እውነተኛ ትርጉም ውጭ መደንቀሩ እንድ ነገር አሳሰበኝ። በዚህ መልኩ ሰዎች ያለስፍራቸውና በተዛባ ትርጉማቸው ከሚጠቀሙባቸው ቃሎች አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ጭምር ነው። ከዚህም በኋላ የመጽሀፉ ሐሳብ በአእምሮዬ መቀረጽ ጀመረ። ስለዚህ ወደ መጨረሻው የመጽሐፉ ምዕራፍ በቀረብንበት ጊዜ፣ የመጽሐፉ እውደ አሳብ በውስጤ መስረጽ ወደ ጀመረበት ክፍልም መምጣታችን ተገቢ ነው።

ቴምፐርአንስ "ራስን መግዛት" የሚለው ቃል ስትሬንግዝ "ጥንካሬ" ከሚለው ቃል የመጣ ነው። ራስን መግዛት የሚለው ቃል በእያንዳንዷ የአዲስ ኪዳን ክፍል ውስጥ ስናየው ስለ እግዚአብሔር ከተገኘ መረዳት ጋር እየተጣመረ የተነገረ ቃል ነው። የጳውሎስ ከፊሊክስ ጋር ያደረገውን ውይይት አስመልክቶ፣ ሉቃስ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፣ "እርሱም ስለ ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት ስለሚመጣውም ኩነኔ ሲነጋገር ሳለ . . . " (የሐ. ሥራ 24፥25)። የዚህ አባባል እንድምታ የሚያመለክተው ሰው የሕይወቱን አቅጣጫ አጥብቆ መያዝ እንደሚገባው ነው።

ምክንያቱም በዘመን መጨረሻ የእግዚአብሔር ፍርድ ማንኛውንም ሰው እንደሚጠብቀው ሁሉ እግዚአብሔር፤ ሰው በሕይወት ዘመኑ ሲያሳየው የሚገባውን ግብረገባዊ ስነምግባር አሁን ይጠብቀዋል። ጴጥሮስ እንዲህ ብሏል፣ "የመለኮቱ ኃይል . . . ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለሰጠን . . . ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፣ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን"። በመቀጠልም ይህን

እውቀት ስንይዝ ራስን በመግዛት መሆን እንዳለበት ይነግረናል (2ጴጥ 1፥3፣4፣6)። ጳውሎስም ስለመንፈስ ፍሬ በሚናገርበት ክፍል ላይ ሰው ራሱን የሚገዛው፣ በእርሱ ውስጥ በሚኖረው መንፈስ አማካኝነት መሆኑን ይገልጽልናል።

## እውነታና ሕይወት

ራስን መግዛት በተመለከተ በዝርዝር ከመመልከታችን በፊት “ክርትማንትል” በሚሰው ቴአትር ውስጥ ክሪስቶፈር ፍራይ በሄንሪ 2ኛ አፍ ውስጥ ስሜትን በሚነካ መልኩ ያስቀመጠውን ማስጠንቀቂያ እንመለከታለን። ሄንሪ እንዲህ አለ፣ “አንድ ሰው መሰጋት ያለበት ሕይወትና ሰው በሚለያዩበት ቀን ነው።” የክርስትና ሕይወት በጭራሽ ከእውነታ ጋር ሊነጣጠል አይገባውም። እውነተኛ መንፈሳዊነት ለተፈጥሮ እውነታ እጅጉን የቀረበ ከመሆኑ የተነሳ፤ ምናልባትም ትክክለኛ ትርጉሙን ለመግለጽ “ልእለ ተፈጥሮ” የሚለውን ቃል ልንጠቀም ግድ ይሆናል። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ሰራሽ፣ የተዛባ ወይም በማስገደድ የሆነ ነገር ሁሉ በፍጹም የአዲስ ኪዳን ክርስትና አይደለም።

መንፈሳዊ ሕይወትን ጳውሎስ እንዲህ ሲል ገልፆታል፣ “ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን” (2ቆሮ 4፥7)። ይህ አባባል ፈተናዎቻችን የሚመጡበትን ሁለቱን ዋና ሥፍራዎች ያሳየናል። ልቡናችን ቁሳዊ በሆኑ ነገሮች ላይ በመንጠልጠሉ፤ ራሳችን የከበርን ሃብቶች ሳንሆን የክብሩ ቁሳዊ ሃብቶች ማከማቻ ቋት ለመሆን በሚኖረን ከፍተኛ ቁሳዊ ምኞት እንፈተናለን።

ሌላው ከዚህ በተቃራኒው በቀላሉ የሚከሰት ሲሆን፤ ይህም ራስን እንደከበረ ሃብት ብቻ እንጂ የዚህ የከበረ ሃብት ማከማቻ ቋት መሆንን ያለመቀበል የመንፈሣዊነት ፈተና ነው።

ከሌላው ሰው የተለየ የመጠቀ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖረን የምንሻ ከሆነ፣ ይህ ልክ ከመጠን ያለፈ ቁሳዊ ሃብት ለማከማቸት እንደምናደርገው ጥረት ፍጹም ስህተት ነው። ምክንያቱም ይህ ከእውነታ ጋር ያቆራኘንን ገመድ ይበጥሰዋል። እንዲህም በመሆኑ ደግሞ ሕይወት ከሰው ትነጠላለች።

## በሁሉም ሁኔታዎች ወስጥ

ክርስትና ማለት የእግዚአብሔር የሕይወት ሚዛን በሰው ውስጥ ማለት ስለሆነ ራስን መግዛት በየትኛውም የሕይወት ሁኔታ አስፈላጊ ነው። ስለዚህም ነው ቢ.ኤፍ.ዌልትኮት እንዲህ ያለው፣ “በሥራ ላይ



ሳለን ወይም በጨዋታ ጊዜ፣ በሃይልም ይሁን በድካም፣ በጥልቅ ሃሳብ ተይዘንም ይሁን ቦዝነን ራስን የመግዛት አቅም ሲያጥረን ይታያል”። ጳውሎስ በሁለተኛው ጢሞቴዎስ ምዕራፍ ሁለት ላይ ይህን አሳብ በጥሩ መልኩ አስቀምጦታል። በተሰይ የመጀመሪያዎቹ ሰባት ቁጥሮች ራሱን ስለገዛ ሰው አጠር ያለ ጥሩ መግለጫዎች ሆነው እናገኛቸዋለን። እስኪ በዝርዝር እንያቸው።

## ሁሉን እሰዋሃለሁ

አንደኛ፣ በግል ሕይወታችን ውስጥ ልክ በወታደር ስርዓት ራስን መግዛት ይኖርብናል። ጠቅላላው የሕይወታችን ዓላማ አዛዣችንን መታዘዝና ደስ ማሰኘት መሆን አለበት፣ “የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ” (ቁጥር 4)። ጆን ካልቪን ያነገበው አርማ የሚቀጣጠል ልብ ሲሆን መመሪያው ደግሞ “ሁሉን እሰጥሃለሁ ካንተ የማስቀረው ምንም ነገር አይኖርም” የሚል ነበር። በርግጥ ይህ ጠቅለል ያለ አባባል የአዲስ ኪዳን ደቀመዝሙር ሊያደርገው የሚጠበቅበትና በማንኛውም አማኝ ሕይወት ውስጥ መታየት ያለበት ነው።

እንደዚህ ዓይነት ሕይወት ያለ ምንም ችግር ልንኖረው አንችልም። በእርግጥ ጳውሎስም እንዲህ ብሏል፣ “እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፣ አብረኸኝ መከራ ተቀበል” (ቁጥር 3)። አስደናቂው ነገር በሙላት ራሳችንን ለኢየሱስ ፈቃድ ማስገዛት፣ በራሱ ፍሬያማ ባርኮት ነው።

በአሚ ካርማይክል መጻሕፍት በአንደኛው ውስጥ ስለ አንዲት ልጅ የተነገረ ታሪክ አለ። ይህች አንድ ስለ አትክልት አያያዝ የሚናገር መጽሐፍ ገለጥ ገለጥ እያደረገች ስታይ “ፍሬ አልባው የፖም ዛፍ” የሚል ርዕስ ሐሳቧን ሳበው፤ ምክንያቱም ይኸው ችግር በወላጆቿ የአትክልት ሥፍራም ስለነበረ ነው። የጽሑፉ ደራሲ መፍትሔው ጥቂት ምስማሮች በግንዱ ላይ መምታት ነው ብሎ ጽፏል። ትንሽዬዋ ልጅ መጽሐፉን ለአባቷ አሳየችው፤ አባቷም ማንኛውም ሙከራ አሁን ዛፉ ካለበት ሁኔታ አያብስበትም በማለት ጥቂት ምስማሮች በግንዱ ላይ ቀበቀበ። በዓመቱ ዛፉ በሚያስገርም አኳኋን በጣም በብዛት ፍሬ አፈራ።

ሬጂናልድ ዋሊስ በኬስዊክ ይህን ታሪክ በተናገረበት ጊዜ እንዲህ ብሏል፣ “ጌታ ሆይ በሕይወቴ ፍሬ አልባ የሆንኩበት ምክንያት ይህ ነውን? በተፈተንኩ ጊዜስ ፈጥኜ የምወድቅበት ምስጢር? መከራስ በቀላሉ የሚያንበረክከኝ ለምንድነው? በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው አዲስ ሕይወት ተካፋይ ልሆን ብቁ አይደለሁም ብዬ እስካስብ የተጠቃሁት ለምንድነው? ለክብርህ ምስጋና የሚሆን ፍሬ እንዳላፈራ ያመከነኝስ ምን

ይሆን? ጌታ ሆይ ፍሬ አፈራልህ ዘንድ በስጋየ ላይ፣ በጎስቋላው እኔነቴ ላይ፣ በተረገመው ማንነቴ ላይ ስለመታኸው ምስማር ስላትረመረምኩና ስለተቃወምኩህ ይሆን?”

ራስን መግዛት ማለት የራሳችንን ፍላጎቶች እርግፍ አድርገን ትተን፣ እዛዣችን በየትኛውም የሕይወታችን ክልል ውስጥ ምን እንደሚፈልግ ማወቅ ማለት ነው፡፡ በቤተክርስቲያንም ይሁን በውጭ ባለው ሕይወታችን፣ ወደ እኔነት ወይም ሥጋዊ የሆነ ሕይወት እስማዘንበላችንን እርግጠኞች መሆን አለብን፤ ወይም ጳውሎስ እንዳለው “ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን እያጠላልፍም” (ቁጥር 4)፡፡ ወጣቱ በማያመልጥበትና ሽማግሌው ጡረታ በማይወጣበት መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ እንገኛለን፡፡ ስለዚህ በግል ሕይወታችን ራስን መግዛት ማለት የክርስቶስን ስም የሚያስነቅፍ ማንኛውንም ነገር ላለማድረግ ራሳችንን መቆጣጠር መቻል ማለት ነው፡፡

## በመድፍ ከወደሙት መርከቦች ይልቅ በትል የጠፉት በዙ

ሁለተኛ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና በጸሎት ሕይወታችን እንደ እንድ ሯጭ ዓይነት ራስን መግዛት ሊኖረን ይገባል፡፡ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲህ ሲል ያስታውሰዋል፣ “በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን፣ እንደሚገባ እድርጎ (በሕጉ) ባይታገል፣ የድሉን አክሊል እያገኝም፡፡” እነዚህ ሕጎች ደግሞ በቂ የሆነ ልምምድ ያስፈልጋቸዋል (ቁጥር 5)፡፡ የመጀመሪያው የክርስቲያን ደቀመዝሙር ምልክት ኢየሱስን መታዘዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከስፖርተኛ ሕይወት ጋር የሚመሳሰል የግል ሥነ ሥርዓት ነው፡፡ ስፖርተኛው በሚወዳደርበት ጊዜ ማታለል የለም፣ ተከታታይ የሆነ ልምምድ ሳያደርግ ደግሞ ለድል ሊያበቃው የሚችል በቂ የለውነት አቋም ሊኖረው አይችልም፡፡ እንዴ ወደ ሩጫው መስመር የገባ ስፖርተኛ፣ በተለማመደው ልምምድና ችሎታ በመተማመን ፈንታ፣ እንዲሁ ዝም ብሎ ስለ ሽልማቱ ብቻ በምኞት እያሰበ የሚሮጥ ከሆነ መሳቂያና መቀለጃ ሆኖ ነው የሚቀረው፡፡ ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች በየቀኑ ወደ እግዚአብሔር በመቅረብና በእውነት በመታዘዝ ወደሚገኘው እውነተኛው የመንፈሳዊ እድገት በመድረስ ፈንታ ሃይማኖታዊ በሆነ መንፈሳዊ ቅዠት ጊዜያቸውን ያጠፋሉ፡፡

ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ታላላቅ መንፈሳውያን አንዱ የሆነው ጆን ፍሌቸር እንዲህ ሲል ጽፏል፣ “ከጠላት በሚተኮሰው ጥይት ከጠፉት ይልቅ በትል የጠፉት መርከቦች ይበዛሉ”፡፡ መግለጫው የሚገርም ነው፣ ምክንያቱም ሳሙኤል ፔፒስ የፈጠረው የባሕር ኃይል በዚያ ሰዓት በኃይሉ የስማይን እምብርት ሊደርስ ምንም አልቀረውም ነበር፡፡



እያንዳንዱ የመርከቡ ዕቃ ክፍ ያለ የውጊያ መሣሪያ ከመሆኑ የተነሳ እውነተኛው ጠላት፣ የጠላት መድፍ ሳይሆን ትል መሆኑን ማሰብ ዘበት ነው ሊያስብል ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ትሉ የማጥፋት ኃይሉ እዚህ ግባ የማይባል ቢመስልም፣ በግልጽ ኃይሉ አውዳሚ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ጆን ፍሌቸር ይህንን ምሳሌ በተጠቀመበት ጊዜ የባሕር ኃይሉን በማሰብ አልነበረም፣ ነገር ግን መንፈሳዊ ሕይወትን ስለሚጎዱ ነገሮች ለማሳየት እንጂ፡፡ እውነተኛው የክርስቲያን ጠላት ክፉው የሚተኩሳቸው ትላልቅ የሚንበለበሉት ፍላጻዎች ወይንም የሚያስነሳቸው መጠነ ሰፊ የሆኑ ፈተናዎች ሳይሆኑ፣ ክፉው የሚበላብን ጠቃሚ የሆኑ መንፈሳዊ ነገሮቻችንን መሆኑ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የጠበቀ የክርስትና ሕይወታችን ላይ ጥቂትና በጣም ትናንሽ የሚመስሉ ነገር ግን በደንብ የታቀዱ ቀዳዳዎችን በመስራት፣ ያለምንም ተኩስ መንፈሳዊነታችንን ያደክመዋል፡፡

ልክ እንደ አንድ ስፖርተኛ፣ የልምምድ ጊዜአችንን ራሳችንን በመግዛት መጠቀም አለብን፡፡ ምክንያቱም በሕጉ መሠረት መወዳደር የምንችለው መንፈሳዊ ሕይወታችን በጤናማ ሁኔታ ላይ በሆነበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የመንፈሳዊ ልምምድ ጊዜያችንን ብናሰርቅ ግን፣ እውነተኛው መንፈሳዊ ሕይወታችንና እድገታችን በአደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ የግል የጥሞና ጊዜያችንን ራስን በመግዛትና በታማኝነት የምናደርግ ከሆነ ሁልጊዜ የውድድሩ ተስማሚዎች እንሆናለን፡፡

## አፈር፣ ዘርና ካፊያ

ሦስተኛ፣ በቤተክርስቲያን ሕይወታችን በገበሬ የሥራ ስነምግባር ራስን መግዛት ሊኖረን ይገባል፡፡ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዳለው “የሚደክመው ገበሬ ፍሬውን ከሚበሉት መጀመሪያ እንዲሆን ይገባዋል” (ቁጥር 6)፡፡ እንዲሁ በቀላሉ ቁልፍን በመንካት ወይም ማብሪያና ማጥፊያን በማዞር ብቻ ነገሮች በሚሆኑበት በዚህ ዘመን፣ ሚዛናዊ የሆነ የቤተክርስቲያን ሕይወት ይኖረን ዘንድ ወደ ገበሬ ሕይወት እንመለከታለን፡፡ ሁልጊዜ ከሁለቱ ተቃራኒዎች ወደ አንዱ ስንሳብ እንገኛለን፡፡ በአንድ በኩል የቤተክርስቲያን ሥራ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ሊያልቅ አይችልም በማለት እንፈተናለን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ማረሱን፣ መዝራቱንና ማጨዱን በአንድ ቀን ለመጨረስ እንፈልጋለን፡፡ ሚዛናዊ የሆነው አምላካዊው ሥርዓት ወቅቶችን የጠበቀ ነው፤ ይኸውም ጠንክሮ በመሥራት ማረስ፣ መዝራትና ማጨድ ሲሆን ይህንኑ ደግሞ በጊዜው መተግበር ነው፡፡

ልክ እንደ ገበሬው እኛም የእግዚአብሔርን አሠራር እንቀበላለን፡፡ እኛ የመንፈሳዊ ሕይወት ፈጣሪዎች ነን ብለን አናስብም፤ ይህም ቢሆን

መፍጠር አለመቻላችንን ለስንፍናችን ምክንያት አድርገን አናቀርብም:: የወንጌል እርሻዎች ሳይታረሱ ወይንም የቃሉ ዘር ሳይዘራ መተው የለብንም:: እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠራል፣ ቤተክርስቲያን ደግሞ ባለአደራ እንደመሆንዋ መጠን መሬቱን ለማለስለስና ዘሩን ለመዝራት ከባድ የሆነ ሥነ ይጠበቅባታል:: የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና የሰው ኃላፊነት ቅንጅት በግልፅ ሁኔታ ይበልጡኑ ከቤተክርስቲያን ሥራ ውጪ አይታይም:: ራስን መግዛት ልክ በግላዊና በፀሎት ሕይወታችን ላይ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ወንጌልን ስንሰብክም አስፈላጊ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል::

ቤተክርስቲያን የለማችውን የማታስተላልፍ ከሆነ (ቁጥር 3)፣ የምታጭደውም ሰብል እዚህ ግባ የማይባል ይሆናል፤ ይህም የሚያሳየው የአዲሱ ኪዳን ራስን መግዛት እጥረት እንዳለባት ነው::

*መሬቱን ማለስለስ-* መሬቱ ዓለም ሲሆን፣ መታረስና መዳበር ይፈልጋል:: ጠንካራ የሆነውን ማለስለስ ይቻላል፣ ማስተካከል የማይቻለውን ደግሞ መሰባበር ያስፈልጋል:: አንድ በእርግጠኛነት ልናውቀው የሚገባ ጉዳይ አለ፤ ይሄውም ቤተክርስቲያን ወደ ዓለም ልትወጣ ይገባታል እንጂ አለም ወደ እርሷ እንድትመጣላት መጠበቅ የለባትም:: እስቲ ማነው ገበሬ እርሻውን ወደ ትራክተሩ እንዲሄድ ሲጋብዝ የሰማ? እኛ ግን ወደ ዓለም ተራምደን በመካከልም ከመግባት ይልቅ እጆቻችንን ዘርግተን ወደ እኛ እንድትመጣ እንጋብዛታለን:: አፈሩ እንዲለሰልስ ካስፈለገ ገብተን ልንራመድበት ግድ ነው:: እርምጃው መጀመር ያለበት ደግሞ አስቀድሞ ከቤታችን ቀጥሎ ወደ ጎረቤታችን ከዚያም በኋላ በሥራ ቦታችን ሁሉ ነው::

*ዘሩን መዝራት-* አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች አበጅተው የሚሠማሩበት ትልም ውብና ቀጥተኛ የሆነ፣ ጓሉ የፈራረሰለትና የለሰለሰ፣ በመንገዱ ላይ ያለች አነስተኛ ጠጠር እንኳን ተለቅማ የተነሳችለት አመቺነት ያለው ነው:: ሕይወትንም እጅግ በተዋበ ግርማ እየኖርናት ነው:: መብታችንን በአደባባይ እናስጠብቃለን፤ የህጉ የትኛ ውም አንቀጽ ይጠበቅልናል:: ይሁንና የቃሉን ዘር የመዝራት ሥራ ግን የለም:: አንድ ገበሬ በዘመናዊ መሣሪያ ከፍተኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የእርሻውን ማሳ ሊያዘጋጅ ይችላል፣ ሆኖም ዘር ካልዘራ ምርት አያገኝም:: ይህ ለክርስቲያኑም እውነት ነው፤ ዘሩ መዘራት አለበት:: እሁድ እሁድ የምንሰማው ወይም በየቀኑ ከእግዚአብሔር ቃል የምናገኘ ው እውነት፣ ምርት ከተፈለገ የግድ በዓለም ላይ መዘራት አለበት::

*ካፊያውን ፈልጉ-* ዲ.ኤል.ሙዲ "የተላካ ጸሎት" በሚለው መጽሐፉ ስለተሃድሶ ሲናገር፣ "ሉተርና ጓደኞቹ እግዚአብሔርን የተማጸኑ ፅኑእን ሰዎች ሲሆኑ፣ የዘመኑን መርገም በመሰባበር አገሮች



ተሸንፈው በመስቀሉ እግር ሥር እንዲወድቁ አደረጉ":: በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ ሪቻርድ ባክስተርም እንዲህ ተናግሯል፣ "የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ክፍሉን ግድግዳዎች፤ ከፀሎት እስትንፋሱ በሚወጣ ላቦት እወየባቸው:: ይህንን ያደረገው ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በኪደርሚኒስተር በኩል የሕይወትን ውሃ ወንዝ ለቆ እስኪቀባው ድረስ ነበር":: ያለምንም ጥርጥር በዘመናት መካከል ተንሰራፍቶ የቆየው የመርገም ቀንበር ዳግም መሰበር አለበት:: ይህ የሚሆነው ደግሞ ክርስቲያኖች ሁሉ ፀንተው በመቆም "የሰማያት ፍሬ!" እያሉ መጮህ ሲጀምሩ ነው::